ኢትዮጵያ፡ታበጽሕ፡እደዊሃ፡ኀበ፡እግዚአብሔር።

ኢ ሀ ሥ አ

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

Ethiopians' Citizen Democratic Union | Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

# ሥልጡንሕዝብና ።

Democracy | 民主 | জনত | д е м о к р а т и я | Δημοκρατία | דמוקרטיה | دِمُقْراطِي

http://www.slttunhzb.net    ቍ.2011-003 ፥ ነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ (August |août 2019 A.D.) ።    እ-ጦማር ፦ sh1@ttomar.net

ሥልጡንሕዝብና ፡ የተሠኘው ፡ መዜንው ፥ የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ (ኢ.ሀ.ሥ.አ.)ን ፡ ተግባር ፡ ለማግራት ፣ ለማረማመድና ፡ ለማስለጥ ፡ የቆመ ፤

• አንድነቱ ፥ ባሕርዩን ፣ ዐላማውን ፣ ፍልስፍናውን ፣ አሠራሩንና ፡ ውጤቱን ፡ ለይፋው ፡ የሚያሳውቅበት ፤

• ይፋው ፥ ሰው ፡ ሊሰማው ፣ ሊያውቀው ፡ ይገባል ፡ የሚለውን ፡ ማንኛውንም ፡ ሐሳብ ፣ ዜናና ፡ ድርስ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚገልጽበት ፥

ያንድነቱ ፡ ወቅታዊ ፡ መንግር ፥ የሕዝብ ፡ ምንባብ ፡ ነው ። መስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፹፫ ፡ ዓ.ም. ፡ ባተ ።

---

## ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

### ፋሺዝም ፡ አልሞተም ።

———

ሚያዝያ ፡ 27 ፡ አደባባይ ፡ እቆመው ፡ ያርበኞች ፡ መታሰቢያ ፡ ሐውልት ፡ ላይ ፡ ተቀርጾ ፡ እንደምናነበው ፦

*"... ፡ ቢነገር ፣ ቢወራ ፥ ቢተረክ ፣ ቢጻፍ ፥*

*ፍጻሜ ፡ የለውም ፡ የፋሺስቶች ፡ ግፍ ። "*

ሲል ፡ ደራሲ ፡ የነገረው ፡ እውነት ፥ ከ 79 ፡ ዓመት ፡ በኋላም ፡ እውነትነቱ ፡ ሳያከትም ፥ ሕያው ፡ ምስክር ፡ ኾኖ ፥ ዘመናችንን ፡ የሚገልጽ ፡ ቃለ ፡ ምዕዳንን ፡ ያሰማል ።

ሕዝብን ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ከፋፍሎ ፡ የሚያባላ ፡ የስግብግብነት ፡ ርኩስ ፡ መንፈስ ፥ እንደ ፡ አዶ ፡ ከበሬ ፡ ድንገት ፡ እየሰፈነ ፥ መርዶን ፡ በየቤቱ ፡ ሲያረዳ ፡ እንሆ ፡ 45 ፡ ዓመታት ፡ ዐለፉን ።

ዘንድሮ ፡ ደግሞ ፥ ፋሺዝም ፡ መልኩን ፡ ለውጦ ፥ ዐቅዳዊ ፡ ወገዳ ፡ በሚመስል ፡ ድርጊያ ፡ የገዛ ፡ ልጆቹን ፡ *"የክልል ፡ አመራር ፡ አባላቱን"* ፡ እና ፡ የጦር ፡ አበጋዞቹን ፡ እሚበላበት ፡ ረድፍ ፡ ላይ ፡ ደርሶ ፥ በሠኔ ፡ ወር ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ አሠቃቂ ፡ መጠፋፋትን ፡ አስፈጸመ ። ድርሱንም ፡ በዘር ፡ ማደራጃ ፡ ምክንያት ፡ አድርጎታል ።

የቀደሙት ፡ ትውልዶች ፡ የቀድሞውን ፡ ፋሺዝም ፡ በመሸሸ ፡ ወይ ፡ በመታገሥ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ በማስታመም ፡ ድል ፡ አልነሡትም ። ምንነቱን ፡ ካወቁ ፡ በኋላ ፥ በመሥዋዕት ፡ ብቻ ፡ መሸነፉን ፡ ባስረገጡ ፡ ጊዜ ፥ ውዱን ፡ የሕይወት ፡ ዋጋ ፡ ከፍለው ፡ ድል ፡ ነሥተውታል ። የዛሬውን ፡ ፋሺዝም ፡ ከቀድሞው ፡ የሚለየው ፥ የኛኑ ፡ አካል ፡ ለብሶ ፡ መምጣቱ ፡ ነውና ፥ እያንዳንዳችን ፡ ራሳችንን ፡ ገዝተን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችንን ፡ በሥልጡንሕዝብናችን ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ በማጽናት ፥ ለዚህ ፡ ዲያብሎሳዊ ፡ የከፋፍለኽ ፡ ግዛ ፡ ኀይል ፡ መግቢያ ፡ ቀዳዳን ፡ ልናሳጣውና ፡ ድል ፡ ልንነሣው ፡ እንችላለን ። ይህም ፡ ሕዝባዊ ፡ እግዚእናን ፡ ማስከበር ፡ ይባላል ፨

---

## ልዩ ፡ ማስታወቂያ

special announcement | annonce spéciale | إعلان خاص

ለንደን ፥ ነሐሴ ፡ 30 ፡ ቀን ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

### የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድ ፡ ጸድቋል ።

———

የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፥ ደንቡ ፡ በሚፈቅድለት ፡ አገባብ ፥ መክሮና ፡ ዘክሮ ፡ በወሰነው ፡ መሠረት ፥ ቍ.1 ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነዱን ፡ በጉባኤ ፡ አሻሽሎ ፥ ረቂቅ ፡ ሰነዱን ፡ ለመሳ ፡ አባላቱና ፡ ዐባሪዎቹ ፡ አስተያየትና ፡ ትችት ፡ ማቅረቡ ፡ ይታወሳል ። ከቀረቡት ፡ የማሻሻያ ፡ ሐሳቦች ፡ ውስጥ ፡ በቂ ፡ ድጋፍ ፡ ያገኙቱ ፡ ከረቂቅ ፡ መሠረታዊው ፡ ደንብ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕደው ፥ የተሻሻለውን ፡ የመጨረሻ ፡ ረቂቅ ፡ <u>መሠረታዊ ፡ ሰነድ</u> ፡ ነሐሴ ፡ 30 ፡ ቀን ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ በጉባኤ ፡ ማጽደቁን ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክሩ ፡ ያስታውቃል ።

በማሻሻሉ ፡ ሥራ ፡ በትጋት ፡ የተባበሩትን ፡ ኹሉ ፡ ከልብ ፡ እያመሰገነ ፥ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፥ አባላቱ ፣ ዐባሪዎቹና ፡ ደጋፊዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድ ፡ በማጥናትና ፡ በማስጠናት ፥ በያሉበት ፥ ዐላማውንና ፡ ዐቅዱን ፡ እንዲያስተዋውቁና ፡ ሰላማዊ ፡ ትግሉን ፡ አጠናክረው ፡ እንዲቀጥሉ ፡ ጥሪውን ፡ ያስተላልፋል ።

ይህ ፡ የጸደቀው ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድና ፡ ማንኛውም ፡ ተጨማሪ ፡ መረጃ ፡ ከመርበቢያችን ፡ ከ ፦

http://www.slttunhzb.net

ይገኛል ፨

*የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ።*


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

# የተሻሻለው ፡ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድ ።

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

ነሐሴ ፡ 30 ፡ ቀን ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

# መሠረታዊ ፡ ሰነድ ።

(ቍ. ፡ 1 ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድን ፡ ዐድሶና ፡ አጽንቶ ፡ የተካ ። )

እኛ ፥ ከኢትዮጵያ ፥ ከእየኅብረተሰቡ ፡ መወለዳችን ፥ ከምድሯ ፥ ከእየግዛቱ ፣ ከእየከተማውና ፡ ከእየቀበሌው ፡ መምጣታችን ፥ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያን ፥ መላዋን ፡ ለመሠየምና ፡ አንድነቷን ፡ ለመመሰል ፡ የፈቀደልን ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፤

- ነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ባሕርያዊ ፡ መብታችንንና ፡ ሕዝባዊ ፡ የገዢነት ፡ ሥልጣናችንን ፡ ለሚጠብቅልን ፡ ርትዓዊ ፡ ኹነቷ ፡ (የርትዕ ፡ መንግሥቷ) ፡ በመቆም ፥ በኢትዮጵያ ፡ ሥልጣን ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ አላግባብ ፡ የወጣን ፡ ኀይል ፡ ኹሉ ፡ በመቃወም ፥ ያልተጨቈነ ፡ ኀሊናዋን ፡ ምርጫ ፡ ለመናገር ፥ ያልተገደደ ፡ ፈቃዷን ፡ ለመከተል ፡ ወደን ፤
- ሀገራዊ ፡ አንድነቷን ፡ የማጽናት ፥ ሐራነቷን ፡ የመጠበቅ ፥ እግዚእናዋን ፡ የማስከበርና ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ ኹነቷን ፡ (የርትዕ ፡ መንግሥቷን) ፡ የማቆም ፡ ሀገራዊ ፡ ተግባራችንን ፡ ለመፈጸም ፡ ቈርጠን ፡ መነሣታችን ፥

በስሟ ፡ ለመወከልና ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣኗ ፡ ለመሥራት ፡ መብት ፡ የሚሰጠን ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ በቍ. ፡ 1 ፡ መሠረታዊ ፡ ሰነድ ፡ የተመለከተውን ፡ ዐድሰንና ፡ አጽንተን ፥ የሚከተለውን ፡ ወስነን ፥ በስሟ ፡ ዐውጀናል ።

## ዐዋጅ ።

### አንቀጽ ፡ 1 ፤

### የኢትዮጵያ ፡ ኹነትና ፡ አገዛዛዊ ፡ ፍልስፍና ።

1.1 ፤ በታሪኳ ፡ እንደተጻፈው ፥ ኢትዮጵያ ፥ በ1260 ፡ ዓ.ም. ፡ ላይ ፥ መላው ፡ ሕዝቧ ፥ በሕገኛዎቹ ፡ ወኪሎቹ ፡ ሰውነት ፥ በውዴታው ፡ ተሰብስቦ ፥ በነጻነት ፡ መክሮና ፡ ዘክሮ ፣ ወስኖ ፥ በቃል ፡ ኪዳኑ ፡ አጽንቶ ፥ በገቢር ፡ ባቈየው ፡ ደኅኛ ፡ ዐፄ ፡ ሥሩ ፡ (ሥርዐተ ፡ መንግሥቱ) ፡ መሠረት ፥ እያንዳንዱ ፡ ሀገራዊ ፥ የብጤውን ፡ ባሕርያዊ ፡ መብት ፡ በማክበር ፡ ወንፈል ፥ በኅብረቱ ፡ የሠራት ፥ በፈቃዱ ፡ የከወናት ፥ አንዲት ፣ የማትከፋፈልና ፡ ሥልጡንሕዝባዊት ፡ ሐራ ፡ የርትዕ ፡ ኹነት ፡ ናት ።

1.2 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእ ፡ (ገዥ) ፡ ነው ። ኢትዮጵያን ፡ አኳኚው ፡ ሥልጣን ፥ ኳኚው ፡ ፈቃድና ፡ ኹኑ ፡ አካል ፥ ወይ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፥ ምኳኑ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እና ፡ የሰፈረበት ፡ ብሔር ፡ [ምድር] ፡ አንድነት ፡ ነው ። በሌላ ፡ አነጋገር ፥ አንጋሹ ፣ ነጋሹና ፡ መንግሥቱ ፥ ወይም ፡ ገዢው ፣ ተገዢውና ፡ ግዛቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እና ፡ የብሔሩ ፡ [የምድሩ] ፡ አንድነት ፡ ነው ።

1.3 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ብሔር ፥ በሦስቱም ፡ አኳያዎቹ ፥ በየብስም ፡ በባሕርም ፡ ባየርም ፥ በርትዓዊ ፡ መዋሐድ ፡ ከመስፋት ፡ በቀር ፥ የማይሸረፍ ፣ የማይቀነስ ፣ የማይጠብ ፡ ሙሉ ፡ ነው ።

1.4 ፤ ኢትዮጵያ ፡ አንዲትና ፡ የማትከፋፈል ፡ ሀገር ፡ ናት ።

### አንቀጽ ፡ 2 ፤

### የሥልጣን ፡ ተገቢነትን ፡ ስለ ፡ ማረጋገጥ ።

2.1 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ከማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ ባስተባበረውና ፡ ባስፋፋው ፡ የየካቲት ፡ ወር ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ ሀገራዊ ፡ ንቅናቄው ፡ ኀይል ፥ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ የያዙበትን ፡ የግዛት ፡ መብቱን ፡ በሰላም ፡ ሲያስመልስ ፥ ላዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ሰጥታ ፡ የተሰማሩትን ፡ ሰራዊቶች ፡ ለማስተባበር ፡ የተመደበው ፡ ወቷደራዊ ፡ ደርግ ፤

2.1.1 ፤ ሊጠብቀው ፡ የቆመለትን ፡ ሕዝብ ፡ ከድቶ ፥


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

የተውጣጣባቸውን ፡ ደንቦች ፡ አታሎ ፥ ከርክክቡ ፡ መኻከል ፡ ሥልጣኑን ፡ በውንብድና ፡ አስጥሎ ፥ የትግሉን ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ አጨናግፏል ፥ የንቅናቄውንም ፡ ደገኛ ፡ ጒዞ ፡ አቋርጧል ፤

2.1.2 ፤ ለፍትሕ ፡ ችሎትና ፡ ለሀገራዊ ፡ ሥልጣን ፡ የሚውለውን ፡ የመንግሥት ፡ ኀይል ፥ በእጁ ፡ መናኛ ፡ ይዞ ፥ የግፍ ፡ መኪናው ፣ የግል ፡ መሣሪያው ፡ አድርጎ ፥ በምቀኝነት ፡ በቀል ፣ በእብሪት ፡ ሰውን ፡ በመፍጀት ፥ የመላውን ፡ ሕዝብ ፡ ሰላምና ፡ ሰጥታ ፡ አደፍርሶ ፥ ኢትዮጵያን ፡ እሥልጣን ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ዶሏል ።

2.2 ፤ የሥልጣን ፡ ጦርነቱ ፡ ተቀጣጥሎ ፥ በግንቦት ፡ ወር ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፥ በኢ.ሕ.ዴ.ሪ.[1] ፡ ይዘት ፡ መፍረስ ፡ ዋዜማ ፥ የተባበሩት ፡ ያሜሪካ ፡ ኹነቶች ፡ (ዩውናይትድ ፡ ስቴይትስ ፡ ኦፍ ፡ አሜሪካ) ፡ መንግሥት ፥ በኢ.ሕ.ዴ.ሪ ፡ ይዘት ፡ ተወካዮችና ፡ በተቀናቃኞቹ ፡ መኻከል ፥ በብሪታንያ ፡ መዲና ፡ ለንደን ፥ በሽምጋይነት ፡ የቀጠረው ፡ የዕርቅ ፡ ጉባኤ ፤

2.2.1 ፤ ገና ፡ ከመዠመሩ ፥ በሽምጋዩ ፡ መንግሥት ፡ ክዳት ፡ ተጨንግፏል ፤

2.2.2 ፤ ዕርቅ ፡ ሳይወርድም ፥ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ.[2] ፡ እና ፡ ሕ.ግ.ሐ.ኤ.[3] ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ገብተው ፡ ሀገሪቱን ፡ እንዲቈጣጠሩና ፥ የ"ሽግግር ፡ መንግሥት"ን ፡ እንዲመሠርቱ ፤ ቀጥሎም ፥ የክፍለ ፡ ሀገር ፡ ኤርትራን ፡ መገንጠል ፡ እዳር ፡ እንዲያደርሱ ፡ ሽምጋዩ ፡ መንግሥት ፡ አላግባብ ፡ በማዘዙ ፥ የተባበሩት ፡ መንግሥታትን ፡ ሥምረት ፡ ረምርሟል ፥ ባንዲት ፡ እግዝእት ፡ ሀገር ፡ የውስጥ ፡ ጒዳይ ፡ ጣልቃ ፡ ገብቷል ፤ የጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ውሳኔውንም ፡ አስፈጽሟል ፤

2.2.3 ፤ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሕገ ፡ ወጥነትንና ፡ ውንብድናን ፡ አጽንቷል ፤

2.2.4 ፤ ዕርቅ ፡ ባልወረደበት ፡ ቀውጢ ፡ ኹኔታም ፥ የሕገ ፡ መንግሥት ፡ ማርቀቅ ፡ ኺደትን ፡ አስዠምሯል ፥ የማርቀቁንም ፡ ኺደት ፡ በመቀየስ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ "ሕዝቦች" ፡ በማለት ፡ ህልውናውን ፡ የካደ ፣ ፀረ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የ"አፓርትሀይድ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት"ን ፡ በሀገሪቱ ፡ ላይ ፡ በእጁ ፡ መናኛ ፡ ጭኗል ፤

2.2.5 ፤ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ ለዕልቂት ፣ ለጭቈናና ፡ ለስደት ፥ ሀገሪቱንም ፡ ለብዝበዛ ፡ ዳርጓል ።

2.3 ፤ ከ 2007 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 2010 ፡ ዓ.ም. ፡ ተጠናክሮ ፡ በቀጠለው ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚእናን ፡ የማስመለስ ፡ ሕዝባዊ ፡ እንቅስቃሴ ፡ ምክንያት ፥ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ.[4] ፡ ይዘት ፡ ለ"ሥር ፡ ነቀል" ፡ ለውጥ ፡ ዝግጁ ፡ መኾኑን ፡ አስታውቋል ፤ በተግባርም ፡ ምልክቶችን ፡ አሳይቷል ።

2.4 ፤ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእና ፡ በማክበር ፥ በሕጋዊ ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ሊሠራበት ፡ የሚገባውን ፡ መንግሥታዊ ፡ ኀይል ፥ የሕዝብ ፡ ይኹንታን ፡ ላገኘ ፡ ለባለዐደራ ፡ የሽግግር ፡ መንግሥት ፡ በማስረከብ ፥ ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ተረቆ ፡ የሚጸድቅበትንና ፡ ዘላቂው ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥት ፡ የሚቋቋምበትን ፡ ሕጋዊ ፡ አገባብ ፡ በጋራ ፡ ለማስለጥ ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ይተጋል ።

2.5 ፤ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ በነጻና ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ ምርጫ ፡ ሠይሞ ፡ የሚያቋቁመው ፡ ሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፦

2.5.1 ፤ በተወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፥ በሙሉ ፡ ነጻነት ፡ መክሮና ፡ ዘክሮ ፡ የሚያረቀውን ፡ ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለሕዝብ ፡ አቅርቦ ፡ በማስጸደቅ ፥

2.5.2 ፤ በሕገ ፡ መንግሥቱም ፡ መሠረት ፡ ዐዲሱን ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ ኹነት ፡ (የርትዕ ፡ መንግሥት) ፡ በማቋቋም ፥

የሥልጣን ፡ ተገቢነትን ፡ በሀገሪቱ ፡ መልሶ ፡ ማስፈን ፡ የዚህ ፡ ሀገራዊ ፡ ሱታፌ ፡ አንድያ ፡ ዐላማ ፡ ይኾናል ።

2.6 ፤ ይህም ፡ ዐላማ ፡ እዳር ፡ እስካልደረሰና ፡

1 ኢ.ሕ.ዴ.ሪ. ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝባዊ ፡ ዴሞክራስያዊ ፡ ሪፓብሊክ ፥ (የደርግ ፡ ይዘት) ።

2 ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝቦች ፡ አብዮታዊ ፡ ዴሞክራስያዊ ፡ ግንባር ።

3 ሕ.ግ.ሐ.ኤ. ፤ ሕዝባዊ ፡ ግንባር ፡ ሐርነት ፡ ኤርትራ ።

4 ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ፌዴራላዊ ፡ ዴሞክራስያዊ ፡ ሪፓብሊክ ፡ (የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ ይዘት) ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ በሀገሪቱ ፡ እስካልሰፈነ ፡ ድረስ ፥ አንዳች ፡ ደኀኛም ፡ ኾነ ፡ ክፉኛ ፡ ለውጥ ፡ በሀገሪቱ ፡ ቢከታተል ፥ የሕዝብን ፡ እግዚእና ፡ ለዘለቄታው ፡ የማስከበሩ ፡ ሰላማዊው ፡ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ትግል ፡ እስከ ፡ ሙሉ ፡ ክንዋኔው ፡ ድረስ ፡ ሳይቋረጥ ፡ ይቀጥላል ።

## አንቀጽ ፡ 3 ፤

## የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሕጋዊ ፡ ትግል ።

3.1 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ያገሩን ፡ ርትዓዊ ፡ ኹነት ፣ የግዛቱን ፡ ሥልጡንሕዝባዊነትና ፡ ነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ነጻነቱን ፡ የሚጠብቅበትን ፡ የገዢነት ፡ መብቱን ፡ ለማስከበር ፥ በተናጠልም ፡ ኾነ ፡ በኅብረት ፥ ወይ ፡ በሀገር ፡ ደረጃ ፥ በየጊዜው ፡ የሚፈጽማቸው ፡ የፍትሕ ፡ ክርክሮች ፥ ወይም ፡ የመሣሪያ ፡ ትግሎች ፥ የጭቈና ፡ ተቃውሞ ፡ መብቱ ፡ የሚፈቅድለት ፡ ተገቢዎች ፡ ተግባሮች ፡ ናቸው ።

3.2 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ማንኛውንም ፡ ዐምባ ፡ ገነንነት ፡ ለመቃወም ፡ የሚያነሣው ፡ ጠቅላላ ፡ ትግል ፥ ያልሞት ፡ ባይ ፡ ተጋዳይነት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ ነፍስ ፡ ወከፋዊና ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚእናውን ፡ የመከላከልም ፡ የተቀደሰ ፡ መብቱ ፡ ነው ።

3.3 ፤ ለግል ፡ ጥቅም ፥ ወይም ፡ ለውጭ ፡ ኀይል ፡ መሣሪያ ፡ በመኾን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመቍረስ ፣ ለመከፈል ፣ ለማጥፋት ፣ በከፊል ፡ ወይ ፡ በመላዋ ፡ ለባዕድ ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፥ በነፍስ ፡ ወከፍም ፡ ኾነ ፡ ባንዳች ፡ ኅብረት ፡ የሚሠራ ፡ ኹሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠላት ፡ ነው ።

## አንቀጽ ፡ 4 ፤

## ቍርጥ ፡ ሐሳብ ።

4.1 ፤ ኢትዮጵያን ፥ ከወደቀባት ፡ ጥፋት ፡ አኹን ፡ የሚያድናትና ፡ ርትዓዊ ፡ ኹነቷን ፡ መልሶ ፡ የሚሠራላት ፡ ችሎት ፥ የሕዝቧ ፡ አንድነት ፡ የሚያለማላት ፡ ሀገራዊ ፡ እግዚእናዋ ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝበን ፤

4.1.1 ፤ ተወላጇ ፡ የሚመኘውን ፡ የባለቤትነትና ፡ የነጻ ፡ ኅብረ ፡ ሰብእ ፡ ኑሮን ፡ የሚያገኘው ፥ ሕዝቧ ፥ ራሱን ፣ በራሱ ፣ ለራሱ ፡ ሲገዛ ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ ተረድተን ፤

4.1.2 ፤ እነዚህንም ፡ መሠረታውያን ፡ ጸጋዎች ፡ የሚያገናጽፋት ፡ ችሎት ፥ የተወላጇ ፡ ባሕርያዊ ፡ ሥልጡንሕዝብና ፡ መኾኑን ፡ አምነን ፤

4.1.2.1 ፤ የሕዝቧን ፡ አንድነት ፡ በመሥራት ፥ ሀገራዊ ፡ እግዚእናዋን ፡ ለማልማት ፤

4.1.2.2 ፤ ሰራዊቶቿን ፡ እትእዛዟ ፡ ሥር ፡ በመመለስ ፥ የለውጡን ፡ ሰላማዊ ፡ ንቅናቄ ፡ ለማስለጥ ፤

4.1.2.3 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ በጠቅላላ ፡ ንቅናቄው ፡ በባሕርያዊ ፡ ባለመብትነት ፡ የሚጠይቀውን ፡ የግዛት ፡ ሥልጣን ፡ ለማስከበርና ፥ ሥልጡንሕዝብናን ፡ በኢትዮጵያ ፡ መልሶ ፡ ለማስፈን ፥ ቅዱስ ፡ ለገቻ ፡ ገብተናል ፤ ለገቻችንንም ፡ እፍጻሜ ፡ ሳናደርስ ፡ ላናርፍ ፥ ላንመለስ ፡ ቈርጠናል ።

4.2 ፤ ቍርጥ ፡ ሐሳባችንን ፡ እመልካም ፡ ፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፦

*"የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት — ኢ.ሀ.ሥ.አ."*

በተሠኘ ፡ መጠሪያ ፥ አንድነታዊ ፡ አካላችንን ፡ አቁመን ፥ ግብሩን ፡ ያከናውንልን ፡ ዘንድ ፥ ባምስተኛው ፡ አንቀጽ ፡ የተመለከተውን ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ሠርተን ፥ ሕዝባዊ ፡ ሥልጣናችንን ፡ ሠይመነዋል ።

## አንቀጽ ፡ 5 ፤

## የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ።

5.1 ፤ የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፥ በአንቀጽ ፡ 4 ፡ የተመለከተውን ፡ ቍርጥ ፡ ሐሳባችንን ፡ በገቢር ፡ ያከናውንልን ፡ ዘንድ ፥ አንድ ፡ ሀገራዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ይኖረዋል ።

5.2 ፤ ፈጻሚ ፡ ምክሩ ፦

አንድ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፤

አንድ ፡ ምክትል ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፤



©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ሦስት ፡ አባሎች ፤

አንድ ፡ በኾሮንድ ፤

አንድ ፡ ጠቅላይ ፡ ጸሓፊ ፤

በድምሩ ፡ ሰባት ፡ በስም ፡ የመረጥንለት ፡ መማክርት ፡ ይኖሩታል ።

5.3 ፤ በየኀላፊነቱ ፡ የሚያስቀምጣቸውን ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ፈጻሚ ፡ ምክሩ ፡ ይሠይማል ።

5.4 ፤ ፈጻሚ ፡ ምክሩ ፡ ሥራውን ፡ የሚያከናውንበት ፡ አንድ ፡ ሀገራዊ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ይኖረዋል ። መንበሩን ፡ እተመቸው ፡ ቦታ ፡ የማድረጉ ፡ ምርጫ ፡ የርሱ ፡ ነው ።

5.5 ፤ ፈጻሚ ፡ ምክሩ ፡ የውስጥ ፡ ደንቡን ፣ የዘርፍ ፡ ጉባኤዎቹን ፣ የክፍል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶቹን ፡ ደረጃና ፡ ብዛት ፣ የሠራተኞቹን ፡ ዐይነትና ፡ መጠን ፣ የሥራ ፡ ማስኬጃውን ፡ ራሱ ፡ ይወስናል ።

## አንቀጽ ፡ 6 ፤

## የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ግብር ።

6.1 ፤ የውንብድና ፡ ይዘትን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አስወግዶ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእና ፡ መልሶ ፡ ማስከበር ፤

6.2 ፤ እግዚእናውን ፡ ተረክቦ ፡ ከለበሰበት ፥ ማለት ፥ የውንብድና ፡ ይዘት ፡ ከተወገደበት ፡ ዕለት ፡ አንሥቶ ፥ ከስድስት ፡ ወር ፡ በማያልፍ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሀገራዊ ፡ ኹነቱን ፡ በውዴታው ፡ እንዲከውን ፥ ባልተጨቈነ ፡ ኅሊናው ፥ ባልተጨነቀ ፡ ልቦናውና ፡ ባልተገደደ ፡ ፈቃዱ ፡ ዐዲስ ፡ ክዋኔን ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ መንግሥትን ፡ የሚሠራለትን ፡ ሀገራዊ ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤውን ፡ በሙሉ ፡ ነጻነትና ፡ በብሔራዊ ፡ መረጣ [5] ፡ ለማቋቋም ፡ የሚያሻውን ፡ ሰጥታና ፡ ምቹት ፡ ማረጋገጥ ፤ የሚፈለገውንም ፡ ሙሉ ፡ አገልግሎት ፡ ማበርከት ፤

6.3 ፤ ሀገራዊው ፡ ከዋኝ ፡ ጉባኤ ፡ ዐዲሱን ፡ ክዋኔ ፡ ከወሰነበት ፡ ዕለት ፡ አንሥቶ ፥ መንፈቅ ፡ በማያልፍ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፥ በዚሁ ፡ ክዋኔ ፡ መሠረት ፥ ግዛቱን ፡ በሙሉ ፡ ነጻነት ፡ የሚያቋቁምበትን ፡ ምቹት ፡ ማረጋገጥ ፤

6.4 ፤ ዐዲሱ ፡ ግዛት ፡ እስከሚቋቋምበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፥ ታሪካዊውን ፡ የሀገሪቱን ፡ ሥርዐተ ፡ መንግሥት ፡ (ወይም ፡ ዐፄ ፡ ሥር) ፡ ፍልስፍናን ፡ ጠንቅቆ ፡ በማወቅና ፡ በማክበር ፣ አሠራሩንም ፡ በማዘመን ፥ አስቀድሞ ፡ በዝርዝር ፡ በተደነገገለት ፡ መመሪያ ፡ መሠረት ፥ የሀገሪቱን ፡ ጠቅላላ ፡ አስተዳደር ፡ ማከናወን ፤

6.5 ፤ ያዲሱ ፡ ግዛት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሥራ ፡ መንበራቸውን ፡ በወግ ፡ በተረከቡበት ፡ ዕለት ፥ ፈጻሚ ፡ ምክሩ ፡ ሥራውን ፡ ፈቶ ፣ ስፍራውን ፡ ለቆ ፡ መበተን ፡ ይኾናል ።

## አንቀጽ ፡ 7 ፤

## የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ኀላፊነት ፣ መብት ፣ ሥልጣንና ፡ ዕድሜ ።

7.1 ፤ የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፥ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ መብት ፥ ኀላፊነትና ፡ ሥልጣን ፡ ይሠራል ።

7.2 ፤ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ የሥልጣን ፡ ዕድሜ ፥ በዚህ ፡ ጠቅላላ ፡ ውሳኔ ፡ የተነገረውን ፡ መልእክቱን ፡ በገቢር ፡ ከጀመረበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፥ በንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ 6.5 ፡ የተወሰነው ፡ እሚፈጸምበት ፡ ዕለት ፡ የሚደርስ ፥ ከዚያ ፡ በፊት ፡ የማይመለስ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የማይታደስ ፡ ነው ፨

| ሙሉ ፡ ስም | ዘንዳ | ሞያ |
| --- | --- | --- |
| ____________ | __________ | ___________ |

5 <u>ብሔራዊ ፡ መረጣ</u> ፤ እመምረጥ ፡ ዕድሜ ፡ የደረሱና ፡ ሕጋዊ ፡ እገዳ ፡ ያልተጣለባቸው ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ኹሉ ፥ ምንም ፡ ዐይነት ፡ የጾታ ፡ የሃይማኖት ፡ የሀብት ፡ የሌላም ፡ ልዩነት ፡ ሳይደረግባቸው ፥ ሀገራውያኑ ፡ የምርጫ ፡ ድምፃቸውን ፡ የሚሰጡበት ፡ ብሔራዊ ፡ ምርጫ ፡ (universal suffrage) ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

# መሠሩቻ ፡ ጽሑፍ ።

founding article | article fondateur | مَقالة تاسيسى

# የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡— ሥልጡንሕዝብና ።

## ሥልጡንሕዝብና ፥ የአቢሳን ፡ ቤዛ ።

ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ።

---

*(ሠልጡንሕዝብና ፥ ፬ኛ ፡ ዓመት ፥ ቍ.007 ፥ ጥር ፡ 1986 ፡ ዓ.ም. ። )*

ቀጥሎም ፥ በየዘመኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ተከሥቶ ፤ ጐልቶ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በምናገኘው ፡ ድርሱ ፡ እንደምንረዳው ፥ ሥልጡንሕዝብና ፡ ለአቢሳን ፥ የሕዝብነታቸው ፡ ዐብሮ ፡ በቀል ፡ ባሕርይ ፡ ኾኖ ፥ ከውስጥ ፡ የተነሣ ፡ ዐማጭን ፡ ሲዳኙበት ፥ ከውጭ ፡ የመጣ ፡ ጠላትን ፡ ሲመክሩበትና ፥ ጊዜን ፡ ለመከተል ፥ ዐዳራቸውን ፡ ሲያዘምኑበት ፡ ዐብሯቸው ፡ ሊኖር ፡ ነው ።

ይህውም ፡ ሊታመን ፥ ሕዝብ ፡ አቢስ ፡ በነገሥተ ፡ አቢሳን ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥት ፡ ለረዥም ፡ ዘመን ፡ በነጻነትና ፡ በሰላም ፡ ዘንተው ፡ እንደ ፡ ኖሩ ፥ የቅንጦታቸው ፡ ብዛት ፡ ከባድ ፡ ቅልጣንን ፡ አምጥቶባቸው ፥ አንድ ፡ የሚያደርጋቸውን ፡ አንዱን ፡ ፈጣሪ ፡ አምላካቸውን ፡ ክደው ፥ በብዙው ፡ ፍጡሩ ፡ (ማለት ፥ በሰማዩ ፤ ምድሩ ፤ ባሕሩ ፤ ደፈሩ ፤ ዘንዶው ፤ እባቡ) ፡ አምልኮት ፡ ተለያይተው ፥ "ለየብቻችን ፡ እንደር" ፡ በማለት ፥ የማትከፋፈለውን ፡ አገራቸውን ፡ "እንከፋፍል" ፡ ሲሉ ፥ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተጣልተው ፥ ለረዥም ፡ ዘመን ፡ ሲተላለቁ ፥ ከቶ ፡ የሚያድናቸው ፡ አንዳች ፡ ኀይል ፡ ወይም ፡ ሥልጣን ፡ አልተገኘም ፡ ነበር ።

ፍንጭ ፡ በሌለው ፡ ጦርነት ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተጨራርሰው ፥ ከመጠን ፡ አንሰው ፥ በግብር ፡ ታጥተው ፥ በነገድነት ፡ ሲጠፉ ፥ ርዝራዣቸው ፡ ጦር ፡ ለማንሣትና ፡ ግንባር ፡ ለመሥራት ፡ ለቻሉት ፡ ነገዶች ፥ አቢስ ፤ በለው ፤ ሳባ ፤ ኖባ ፥ እንደያቀረባቸው ፡ በምንዝርነት ፡ (ተዳባይነት) ፡ ዐደሩ ። ይህውም ፡ ለኹሉም ፡ በጃቸው ። ከሽማግሌዎቻቸው ፡ ይልቅ ፡ መከራው ፡ መከራቸው ። ጦርነት ፡ ከሚፈጃቸው ፡ በፊት ፥ እንርሱ ፡ ጦርነቱን ፡ ፈጁት ። በመብትና ፡ በግዴታ ፡ በማስተካከል ፡ አፋቅሮ ፡ በሰላም ፡ ያስተዳድረናል ፡ የሚሉት ፡ ከኹላቸው ፡ እኩል ፡ የሚወለድና ፡ በኹላቸው ፡ እኩል ፡ የሚወደድ ፡ ሰው ፡ ከመኻከላቸው ፡ ቢያጡ ፥ ለኹላቸው ፡ እኩል ፡ ባዕድ ፡ የኾነውን ፥ ነገር ፡ ግን ፡ ኹላቸውም ፡ እኩል ፡ ፈርተው ፡ የሚያመልኩትን ፡ አርዌን ፡ ለማንገሥ ፡ ተስማሙ ። በስምምነታቸውም ፡ አንድነታቸውን ፡ እንደገና ፡ አጸኑ ። ባንድነታቸውም ፡ እግዚአናቸውን ፡ ተጐናጸፉ ። ክሂላቸው ፡ ሞልቶላቸው ፥ አርዌን ፡ በፈቃዳቸው ፡ አንግሠው ፥ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥታቸውን ፡ መልሰው ፡ አቁመን ፥ በሰላምና ፡ በፍትሕ ፡ ዐደሩ ።

ሕዝብ ፡ አቢስ ፥ በዚህ ፡ ድንቅ ፡ ድርስ ፥ የግለኛ ፡ ብጤን ፡ መብትና ፡ ግዴታ ፡ በማክበር ፡ ወንፈል ፥ መኣው ፡ ተወላጁ ፡ ሲተባበር ፥ ከተፈጥሮ ፡ የታደለውን ፥ የራሱ ፡ ጌታ ፡ የሚያደርገውን ፡ ሰብኣዊ ፡ መብት ፡ አስከብሮ ፡ ለመኖር ፡ የሚያስችለው ፡ ካንድነቱ ፡ ሲሰፍንለት ፥ በሌላ ፡ አነጋገር ፥ ሕዝባዊ ፡ እግዚአናው ፡ ካንድነቱ ፡ ሲሠርጽለት ፡ ተመልክቷል ። ሞላው ፡ ተወላጁ ፡ ሲተባበር ፥ ካንድነቱ ፡ የሚሠጽርው ፡ እግዚአናም ፥ ተወላጁ ፡ ሲበታተን ፡ ከመኻከሉ ፡ የሚጠፋና ፥ ባዶው ፡ ሞላውን ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ የሚያጣፋ ፡ የችሎት ፡ ሕጸጽ ፤ ፍጹም ፡ ስእነት ፤ ወይም ፡ የቅዱስ ፡ ፍላጎት ፡ ዕጦት ፤ ምቀኝነት ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝቦ ፥ ድኅነቱ ፡ በየግንባሩ ፡ እኩል ፡ የግለኛውም ፡ የማኅበሩም ፡ ገንዘብ ፡ የኾነው ፡ እግዚአናው ፡ መኾኑን ፡ ዐውቋል ። እግዚአናውም ፡ ከባለቤቱ ፡ አንድነቱ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ማን ፡ ሊያሠርጸው ፡ የማይቻለው ፤ የማይገባው ፤ ያልታደለው ፡ ዕርሙ ፡ ሲኾን ፥ አንድነቱ ፡ ግን ፥ ለፈቀደው ፤ በፈቀደው ፤ እንደፈቀደው ፡ ሊያውለው ፡ የተገባው ፤ ሲሻውም ፡ ስንኳን ፡ ለራሱ ፤ ለመሰሉ ፡ ለሰው ፥ ላውሬው ፡ እንኳ ፡ ቢሰጠው ፥ ተቈጭ ፤ ቈራጭ ፤ ፈላጭ ፡ የሌለበት ፥ የፈለገውን ፡ ጕዳይ ፡ የሚፈጽምበትና ፡ የተመኘውን ፡ ውጤት ፡ የሚያገኝበት ፥ ከባሕርዩ ፡ ያሠረጸው ፡ ጌትነቱ ፥ የማይዳሰስ ፤ የማይገሰስ ፡ ሥልጣኑ ፡ መኾኑን ፡ በደረሰበት ፤ ባየውና ፡ ባደረገውም ፡ ተረድቶ ፥ ተከታይ ፡ ትውልዱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለዘለቄታው ፡ ያስረዳ ፡ ይመስላል ። እንሆ ፥ ወደ ፡ ፊት ፡ እንደምናየው ፥ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥት ፡ ለመቼውም ፡ ሊኖር ፡ ነው ።

በውኑ ፥ ያርዌ ፡ መንግሥት ፥ መኣው ፡ አቢሳን ፡ የወደደው ፥ ልጁ ፡ የሚሠዋለት ፡ ምልክና ፡ ነበር ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ግዛቱም ፥ ሕጋጊውን ፣ ፈጻሚውንና ፡ ፈታሒውን ፡ ሥልጣን ፡ ያዋሐደ ፡ ችሎት ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፥ መላኪዎቹ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ መኾናቸው ፥ እየቈየ ፡ አድሎኛ ፡ ኾነ ፤ ግፍን ፡ አዘወተረ ። ግፉም ፥ ከታች ፡ ከደካማው ፡ አንሥቶ ፥ እያደር ፡ ወደ ላይ ፣ ወደ ፡ ኀያላኑ ፡ እየተረማመደ ፡ ወጥቶ ፥ ኹሉን ፡ እኩል ፡ የሚያጠፋቸው ፡ መኾኑ ፡ ለኹሉም ፡ እኩል ፡ ሲሰማቸው ፥ የጭንቃቸው ፡ አንድ ፡ መኾን ፡ አንድ ፡ አድርጓቸው ፥ የወል ፡ ዠግናቸውን ፡ አጋቦስን ፡ ጠርተው ፥ "አርዌን ፡ ገድለኽ ፡ ከቀንበሩ ፡ ነጻ ፡ ያወጣኸን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እናነግሥኻለን ። እኛ ፡ ላንተ ፣ ልጆቻችን ፡ ለልጆችኽ ፡ ታማኝ ፡ ዜጎች ፡ ኾነን ፥ ዐልጋኽን ፡ ከዘርኽ ፡ ሳናወጣ ፡ እንኖራለን" ፡ ብለው ፥ የታወቀውን ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ ቃል ፡ ኪዳናቸውን ፡ አሰሩ ፡ ድረስ ፥ ከቀንበሩ ፡ ነጻ ፡ የሚያወጣቸው ፡ አንዳች ፡ ታዳጊ ፡ አላገኙም ፡ ነበር ። እንዳሰሩ ፡ ግን ፥ አንድነታቸውን ፡ አገኙ ፤ ሥልጡንሕዝባዊው ፡ ክሂል ፡ ሞላላቸው ። ባንዱ ፡ ዠግናቸው ፡ ዐብረው ፡ ኼደው ፥ አርዌን ፡ ገድለው ፥ የፍትሕ ፡ መንግሥታቸውን ፡ እንደገና ፡ በርትዕ ፡ ሠሩ ፤ ርሱም ፡ በመብትና ፡ በግዴታ ፡ ተመዛዛኝነት ፡ በረጋ ፡ ዛኅን ፡ ላይ ፡ ጸንቶ ፡ ሊኖር ፡ ነው ።

አቢሳን ፥ ሥልጡንሕዝብናን ፡ ያናዎሩ ፡ መነሻ ፣ መገሥገሻና ፡ መድረሻ ፡ አድርጎ ፡ ሲሠራ ፥ አንድነቱን ፡ እያጠነከረ ፡ ችሎቱን ፡ አዳበረ ። ያገርን ፡ ሥራ ፡ የኅብረት ፡ በሚያደርግበት ፡ አገባብ ፡ የግለኛ ፡ አባሉም ፡ እያደረገ ፡ ክንዋኔውን ፡ ተከፋፍሎ ፡ አገመረው ። የብጤዎቹን ፡ አህጉራት ፡ መብትና ፡ ነጻነት ፡ በግራም ፡ በቀኝም ፡ እንደ ፡ ራሱ ፡ እያከበረም ፥ ብድሩን ፥ ርሱ ፡ በብጤዎቹ ፡ ተከበረ ። ከዚህም ፡ በላይ ፥ በተፈጥሮ ፡ የታደላትና ፡ የሀላዌው ፡ ያዋሐዳት ፡ ያፍሪቃ ፡ ቀርን ፡ ብሔሩ ፥ ዙሪያዋን ፡ በውሃ ፡ የተቀጠረች ፣ በእሳት ፡ የታጠረችና ፡ በያፋፏ ፡ በቃጥላ ፡ የታቀበች ፡ ምጥቅት ፡ ተራራ ፡ መኾኗ ፥ ማንኛውንም ፡ ዐመፀኛ ፡ ለወረራ ፡ ወይም ፡ ለዘረፋ ፡ ተስፋ ፡ ሲያስቈርጥ ፥ ገነቷ ፣ ሀብቷና ፡ አየሯ ፡ ደግሞ ፥ በፍቅር ፡ ለመግባት ፡ ያያትንና ፡ በዝናዋ ፡ ያወቃትን ፡ ኹሉ ፡ አጕመዠ ።

በ፫ ፡ ሺሕ ፡ ፺፬ ፡ ዓመተ ፡ ዓለም ፡ ግድም ፥ በሴም ፡ ልሳነ ፡ የብስ ፡ የተነሣው ፡ የሰባቱ ፡ ዓመት ፡ ረኃብ ፡ ሰውን ፡ በፈጀ ፡ ጊዜ ፥ አንጋደ ፡ ሴም ፣ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፣ ነገደ ፡ ኅምያር ፣ ነገደ ፡ ሐበሻት ፡ እያሠኙ ፥ ጓዝ ፡ ጕዝጓዛቸውን ፡ ይዘው ፥ ከደቡብ ፡ የመን ፡ ተነሥተው ፥ እንዳንበጣ ፡ በዝተው ፥ በመከራው ፡ በር ፡ በባብ ፡ ኧልመንደብና ፡ በዐጻባው ፡ መልካ በዐሰብ ፡ በኵል ፡ አቢስያ ፡ ገቡ ። ቀጥሎም ፥ እስራኤላውያን ፡ ከምስር ፡ ሲወጡ ፥ ከሙሴ ፡ ጋራ ፡ አስቀድመው ፡ ለርዳታ ፡ ምስር ፡ ኼደው ፡ ከነበሩት ፡ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ የሚኾኑ ፡ የአበሳንያ ፡ ዐርበኞች ፡ ጋራ ፥ መጠናቸው ፡ የበዛ ፡ ካማት ፡ (ቅማንት) ፡ አባይን ፡ ተከትለው ፡ መጥተው ፡ አበሳንያ ፡ ገቡም ፥ ተሰደዱም ።

አቢሳን ፥ ኹሉንም ፡ በየጊዜያቸው ፥ በሰላምና ፡ በርኅራኄ ፡ እየተቀበለ ፥ በመብትና ፡ በግዴታ ፡ ከራሱ ፡ ጋራ ፡ ባገሬነት ፡ አስተካክሎ ፥ በሥልጡንሕዝብና ፡ ሲሠራ ፥ አንድንም ፡ አገር ፡ ሳያጠቃ ፣ ባንድ ፡ አገር ፡ ሳይጠቃ ፡ ኖረ ።

ከዚያም ፥ አጋቦሳዊው ፡ ዘርዐ ፡ ንጉሥ ፡ ሐረግ ፡ ላይ ፡ ፳፫ ፡ ነገሥታትን ፡ አከታትሎ ፥ እ፳፬ኛው ፡ ተራ ፡ ላይ ፥ ማክተሚያው ፡ እኾነችው ፡ ስመ ፡ ጥሯ ፡ ማክዳ ፣ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ ወሳባ ፡ ንግሥ ፡ ድረስ ፥ ሥልጡንሕዝብና ፡ በሰላምና ፡ በፍትሕ ፡ እየሠራ ፡ መጣ ።

*(ይቀጥላል ። )*


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

## ድርሰት

essay | essai | مقال

# "ንጉልዮሽ" ፡ እና ፡ ማርከሻው ።

ክፍል ፡ 1/3 ኛ ፡ እና ፡ ክፍል ፡ 2/3 ኛ ፤

ወሌ ፡ ነጋ ።



## ክፍል ፡ 1/3 ፤

## ንጉልዮሽ ።

*"ኢትዮጵያ ፥ ዘንድሮ ፡ የወረደባት ፡ መከራ ፥ በታሪኳ ፡ ውስጥ ፡ ከምናገኘው ፡ ኹሉ ፡ የባሰ ፥ በመከራነት ፡ ብቻ ፡ የማይወሰን ፥ በድንገት ፡ ያልደረሰ ፥ ኀምሳ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ በረቀቀ ፡ ተንኰል ፣ በማይላላ ፡ ኀይል ፣ በማይበርድ ፡ ክፋት ፡ ሲቈለልባት ፡ የኖረ ፡ ጠቅላላ ፡ ጥፋት ፡ ነው ።"*

ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥

*"ታሪካዊ ፡ ዐጪር ፡ ማስታወሻ"* ፥ 1967 ፡ ዓ.ም. ።

የታሪኩ ፡ መነሻ ፡ ዘመን ፡ ከመራቁ ፡ የተነሣ ፡ ዕድሜው ፡ በትኽክል ፡ የማይታወቀው ፣ ሽማግሌው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ከ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፥ ነባር ፡ ሀገራዊ ፡ ሥርዐቱና ፡ ደንቡ ፣ እምነቱና ፡ ባህሉ ፡ ኹሉ ፡ ከመጤዎች ፡ ፍልስፍናና ፡ ሥርዐት ፣ ደንብና ፡ ፈሊጥ ፣ ስግብግብነትና ፡ ነጣቂነት ፡ ጋራ ፡ ሲጋጩ ፥ ሀገሩ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለታላላቅ ፡ ነውጦች ፡ ተዳረገች ፤ በ *"አብዮት"* ፡ የዐመፃ ፡ አዙሪት ፡ ውስጥ ፡ ድንገት ፡ ተወረወረች ። እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስም ፥ ካዙሪቱ ፡ ሰብሮ ፡ መውጣት ፡ ተስኗት ፥ ከማጡ ፡ ወደባሰው ፡ ዐዘቅት ፡ እየተንሸራተተች ፡ ስትወርድ ፡ እናያታለን ። ከቶ ፡ ለዚህ ፡ ውድቀት ፡ ለምንና ፡ እንዴት ፡ ተዳረገች ፧ ማንስ ፡ ዳረጋት ፧ እንዴትስ ፡ ተመልሳ ፡ ትወጣለች ፧ የሚሉት ፡ ጥያቄዎች ፡ ጧት ፡ ማታ ፡ መተከዣዎቻችን ፡ ኾነዋል ። ለነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ጥያቄዎች ፡ የተሟላ ፡ መልስን ፡ የሚሰጡ ፡ ሊቃውንት ፡ አይጠፉምና ፥ የማላገምረውን ፡ አልዠምርም ። ኾኖም ፥ እንደ ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሀገራዊ ፥ *"ለዚህ ፡ ውድቀት ፡ ለምን ፡ ተዳረግን ፧ ማንስ ፡ ያወጣናል ፧ እንዴትስ ፡ ተመልሰን ፡ እንነሣለን ፧ "* ፡ ለሚሉ ፡ የተወሳሰቡ ፡ ጥያቄዎች ፥ አንድ ፡ የመልስ ፡ መዠመሪያ ፡ የምትኾን ፡ ማስታወሻን ፡ ለንባብ ፡ ማብቃቱ ፡ ተገቢ ፡ ስለ ፡ መሰለኝ ፥ የሚከተለውን ፡ በጽሑፍ ፡ አስፍሬያለኹ ። ይህን ፡ የመልስ ፡ መዠመሪያ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ይገልጸዋል ፦ *"ንጉልዮሽ"* ።

*"ንጉልዮሽ"* ፡ ላማርኛችን ፡ ዐዲስ ፡ ቃል ፡ ይመስለኛል ። ዐዲስ ፡ ቃል ፡ መኾኑም ፡ አይደንቅም ፥ ምክንያቱም ፡ ዛሬ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የገጠማት ፡ አጠቃላይ ፡ ችግር ፥ ቀድሞ ፡ በታሪካችን ፡ ያልታየ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ ዐዲስ ፡ መጠሪያን ፡ ጠይቋል ፤ ዐዲስ ፡ መፍትሔንም ፡ ይሻል ።

የ *"ንጉልዮሽ"* ፡ ዘር ፡ የግእዙ ፡ *"ነኈለ"* ፡ ባማርኛ ፡ *"ፈረሰ ፣ ተናደ ፣ ረከሰ ፣ ተዋረደ ፣ ባዶ ፡ ኾነ"* ፡ ማለት ፡ ሲኾን ፤ ከርሱ ፡ *"ንጉል"* ፡ ሳድስ ፡ ቅጽል ፡ ይገሰሳል ፡ (*"የፈረሰ ፣ የተናደ ፣ የረከሰ ፣ የጠፋ ፣ ባዶ ፡ የኾነ"* ፡ ማለት ፡ ነው) ። ፈረንጅኛ ፥ *"null"* ፣ *"nil* ፣ *"nihil"* ፡ ከሚለው ፡ ጋራ ፡ በድምፅም ፡ በትርጕምም ፡ ይስማማል ። ዘሩ ፡ የግእዙ ፡ *"ነኈለ"* ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፡ የሚል ፡ መላ ፡ ምት ፡ አለ ፤ ይመስላል ።

በፈረንጅኛ ፡ ደግሞ ፡ *"nihilism"* ፡ የሚሉት ፡ ኀሊኛ ፡ ወይም ፡ *"ideology"* ፡ አለ ፤ *"የሀገርን ፡ ተቋማት ፡ ማፍረሻ ፣ መናጃ ፡ ዘዴ"* ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ። በሌላው ፡ ዓለም ፡ በገቢር ፡ ተፈጽሞ ፡ ታይቷል ፤ እንደ ፡ ዩጎስላቪያ ፡ ያሉ ፡ ጥቂት ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ሀገሮችም ፡ በርሱ ፡ ጠፍተዋል ። ካ 19 ኛው ፡ ምእትያ ፡ አጋማሽ ፡ እስከ ፡ 20 ኛው ፡ ምእትያ ፡ መባቻ ፥ በነኰርኳር ፡ ወይም ፡ በ"*revolution*" ፡ ስም ፥ በመስኮብ ፡ ምልክ ፡ ውስጥ ፡ የተነሣው ፡ የፍርሰት ፡ አዙሪት ፡ የንኊልዮሽ ፡ ወይም ፡ የ"*ኒኂሊዝም*" ፡ አንዱና ፡ ዐይነተኛው ፡ መዘዝ ፡ ተብሎ ፡ በታሪክ ፡ ተመዝግቧል ። "*ኒኂሊዝም*" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ራሱ ፡ ለመገመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ዐዲስ ፡ ኹኔታ ፡ ለመግለጽ ፡ የዋለው ፡ በመስኮብ ፡ ምሁራን ፡ ነበር ። ምናልባት ፡ ዛሬ ፥ እንዳሳለፋችን ፥ "*አገር ፡ አፍቃሪ*" ፣ "*ወግ ፡ አጥባቂ*" ፥ አለዚያም ፡ "*አዘብጣጭ*" ፣ "*ኂላ ፡ ቀር*" ፡ ብለን ፡ ሚናቸውን ፡ የምንለየው ፡ የዚያ ፡ ዘመን ፡ የመስኮብ ፡ ምሁራን ፥ የገጠማቸውን ፡ ዐዲስ ፡ ችግር ፡ መርምረው ፥ ሲያገኙት ፡ ምክንያቱን ፡ የገለጹበት ፡ ዐዲስ ፡ ቃል ፡ ነበር ።

የመስኮብ ፡ አገር ፡ አፍቃሪዎች ፥ የመጣባቸውን ፡ አደጋ ፡ ለይተው ፡ ስም ፡ ሲሰጡት ፥ መነሻውን ፡ ምዕራብ ፡ አውሮፓ ፥ በተለይም ፡ የጀርመን ፡ ፍልስፍና ፥ ልዩ ፡ ስሙን ፡ "*ሄጊሊያኒዝም* | *hegelianism*" ፡ ብለው ፡ ከጌኦርግ ፡ ሄጌል [6] ፡ (1762-1823 ፡ ዓ.ም.) ፡ ፍልስፍና ፡ አመንጭተውታል ።

ከቶ ፡ የ"*ሄጊሊያኒዝም*" ፡ ወይም ፡ የሄጌልዮሽ ፥ ከርሱም ፡ የመነጩት ፡ የ"*አናርኪዝም*" ፡ ወይም ፡ የመረንዮሽ ፣ የ"*ኒኂሊዝም*" ፡ ወይም ፡ የንኊልዮሽ ፣ የ"*ኮምዩኒዝም*" ፡ ወይም ፡ የጋርዮሽ ፡ እና ፡ የመሳሰሉት ፡ እንደ ፡ "*ናዚዝም*"ና ፡ "*ፋሺዝም*" ፡ ያሉ ፡ ጽንፍዮሾች ፡ ("*extremisms*") ፥ መነሻቸውና ፡ መድረሻቸው ፡ ምን ፡ ይኾን ፧

ብዙ ፡ ዝርዝር ፡ ውስጥ ፡ ሳንገባ ፥ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ብቻ ፡ በጥቂት ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ ጠቅልሎ ፡ ለመንገር ፡ ያኽል ፥ የ"*ሄጊሊያኒዝም*" ፦

- መነሻው ፡ የሰው ፡ መምለክ ፡ (አምላክን ፡ በሰው ፡ መተካት) ፤
- መድረሻው ፡ ደግሞ ፥ ከሰውም ፡ ይልቅ ፡ የራስ ፡ ወገን ፡ ሰው ፡ መምለክ ፤

የሚሉት ፡ ራስን ፡ ማብለጥ ፥ ራስን ፡ ማስቀደም ፥ አለዚያም ፡ ራስን ፡ ማምለክ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ይቻላል ።

ሰው ፡ በመምለኩ ፥ ከሰው ፡ ኀሊና ፡ ውጪ ፡ እውነት ፡ (እውንነት) ፡ አይኖርምና ፥ ሰውን ፡ አንድያው ፡ የታሪክ ፡ ምስክርና ፡ የመጨው ፡ ጊዜ ፡ ተንባይ ፡ ነቢይ ፥ ከታሪክ ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ የሚረማመድ ፡ የ"*መሻሻል*" ፡ መሪ ፣ ፊታውራሪ ፡ ያደርገዋል ። በዚህም ፡ አያበቃ ፤ መላኪው ፡ ሰው ፥ በታሪክ ፡ ግሥጋሤው ፥ በነጮች ፥ ከነጮችም ፡ በፕሮቴስታንት ፡ ነጮች ፡ ቊንጮነት ፥ መደዴ ፡ ዕርገቱን ፡ ከዕርከን ፡ ወደ ፡ ዕርከን ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ የሚሰፍንና ፥ ኹሉን ፡ ከልዕልናው ፡ የሚቃኝ ፡ አድርጎ ፡ ያበጃጀዋል ። ይህ ፡ ከምኞት ፡ የመነጨ ፡ ግብዝ ፡ ጥበብ ፥ ለኹለት ፡ የግራና ፡ የቀኝ ፡ ጽንፍዮሾች ፥ ባንድ ፡ ወገን ፡ ለጋርዮሽ ፥ በሌላው ፡ ወገን ፡ ለናዚዝምና ፡ ለፋሺዝም ፡ እኩል ፡ መጋለቢያ ፡ ሜዳቸውን ፡ ሰጣቸው ። ጋርዮሽ ፡ በ"*ዲያሌክቲክስ*" ፡ መቂናጥ ፡ የሚፈልገውን ፡ የታሪክ ፡ ግሥጋሤ ፡ የሚሸምንበትን ፡ ስልት ፡ ሲጨብጥበት ፤ ናዚዝምና ፡ ፋሺዝም ፡ ደግሞ ፥ የነጭን ፡ "*ልዕለ ፡ ሰብእና*" ፡ የሚያሳምኑበትን ፡ የስብከት ፡ ጭብጥና ፡ የግፍ ፡ መሰወሪያ ፡ አገኙበት ። ኹለቱም ፡ ወገኖች ፡ ለምኞቶቻቸው ፡ ልጓም ፡ ሳይኖርባቸው ፥ የሌላውን ፡ መብት ፡ "*በሚ፟ገ፟ባ*" ፡ እየረመረሙ ፥ "*በታሪክና ፡ በመብት ፡ ተመድቦልናል*" ፡ ባሉት ፡ የ"*መሻሻል*" ፡ ኺደት ፡ ውስጥ ፥ የልዕልናውን ፡ ዕርከን ፡ ተሠየሙበት ።

ይህም ፡ ሊታመን ፥ ከሄጌልዮሽ ፡ ዕርሾ ፡ የፈላው ፡ "*መረንዮሽ*" ፣ በተለይ ፡ ደግሞ ፡ "*ጋርዮሽ*" ፡ በ"*ቦልሼቪኮች*" ፡ እና ፡ በ"*ሜንሼቪኮች*" ፡ አካልነትና ፡ ግዘፍ ፡ የሚረማመድ ፡ አፍራሽ ፣ ናጅ ፡ ኀይል ፡ ኾኖ ፥ ያን ፡ ታላቅ ፡ የመስኮብ ፡ ምልክ ፡ እንዳልነበረ ፡ አደረገው ። ለሰባ ፡ ዓመት ፡ በሶቪየት ፡ ኅብረት ፡ ይዘት ፡ (régime) ፡ ታጅሎ ፡ ቈይቶ ፥ መጨረሻውን ፡ በ 1981 ፡ ዓ.ም. ፥ ፍንዳታን ፡ በሚመስል ፡ መበታተን ፥ ላ 15 ፡ ሀገሮች ፡ ተበታተነ ። "*በምን ፡ ታጀለ ፧* " ፡ ቢሉ ፥ መልሱ ፦ *ሥልጣኔንና ፡ ሥልጣንን ፣ ሃይማኖትንና ፡ ባህልን ፣ ሥርዐትንና ፡ ደንብን ፣ ታሪክንና ፡ ትውፊትን ፡ "ባዶ ፣ ንኊል" ፡ ብሎ ፡ በካደ ፡ የንኊልዮሽ ፡ ፍልስፍናና ፥ ኂላ ፡ ደግሞ ፡ ነባሩን ፣ ትውፊታዊውን ፡ ሥርዐት ፡ "ጠራርጎ ፡ በጣለ" ፡ በሶቪየት ፡ ኅብረት ፡ የጋርዮሽ ፡ ይዘት* ።

ወደራሳችን ፡ ጉዳይ ፡ ስንመለስ ፥ ከዘመኑና ፡ ከየብሱ ፡ መራራቅ ፡ በቀር ፥ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያን ፥ ዛሬ ፡ የገጠማት ፡ አደጋ ፡ ይኸው ፡ ንኊልዮሽ ፡ ያመጣብን ፡ አደጋ ፡ መኾኑ ፡ በብዙ ፡ ማስረጃዎች ፡

6 Georg ፡ Hegel ፥ 1770-1831 ፡ A.D.


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ይረጋገጣል ። የንኊልዮሽ ፡ አደጋው ፡ ከውስጥ ፡ ከመጣ ፡ ቅራኔ ፡ ወይም ፡ ጥያቄ ፡ ከመመንጨትም ፡ የባሰ ፥ ከውጭ ፡ በታቀደ ፣ በተመራና ፡ በተደገፈ ፥ ኢትዮጵያን ፡ የማፈራረስና ፡ አፍሪቃን ፡ የመቀራመት ፡ የምልክዮሽ ፡ (ወይም ፡ የ"*imperialism*") ፡ ዘመቻ ፡ ስልት ፡ መኾኑ ፡ ዐይነቱን ፡ ይለየዋል ፤ አደጋውንም ፡ ያቀለዋል ።

አሮጌ ፡ ሥርዐት ፥ እንደ ፡ አሮጌ ፡ ጫካ ፡ ኹሉ ፥ የጥፋት ፡ እሳት ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ እየተነሣበት ፥ ለብልቦ ፡ የሚምረውን ፡ ያኽል ፥ አቃጥሎም ፡ ያጠፋዋል ። ኢትዮጵያችን ፡ ጥንታዊት ፡ ሀገር ፡ እንደ ፡ መኾኗ ፡ መጠን ፥ በታሪኳ ፡ ዐያሌ ፡ ለውጦችንና ፡ ነውጦችን ፡ አሳልፋለች ። ምናልባትም ፥ በረዥም ፡ ዕድሜዋ ፡ "ግሎባሊዜሽን"ን ፡ ካንዴም ፡ ኹለት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ሳታስተናግድ ፡ አልቀረችም ። "የብርሃን ፡ ዘመን"[7] ፡ የተባለው ፡ የፍልስፍናና ፡ የዕውቀት ፣ የጥበብና ፡ የኪነት ፡ ምርት ፡ ከረሸተበት ፡ ካ 16 ኛው ፡ ምእትያ ፡ አንሥቶ ፡ ባውሮፓ ፡ ታላቅና ፡ አጠቃላይ ፡ ለውጥ ፡ ታይቷል ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ አላቋረጠ ። ለውጡም ፡ በመላ ፡ ዓለም ፡ ተስፋፍቶ ፥ ያገኛቸውን ፡ ግዛታውያንም ፡ ሃይማኖታውያንም ፡ ልማዳውያንም ፡ ሥርዐቶች ፡ ይፈትናል ። የተቋቋሙትን ፡ እያደሰ ፥ ያልተቋቋሙትን ፡ እየደመሰሰ ፥ ዛሬ ፡ በየጕዳዩ ፡ የምናየውን ፡ የመንግሥታትን ፡ አህጉራዊ ፡ ሚዛንና ፡ አሰላለፍ ፡ ሰጥቶናል ። ዐያሌ ፡ ያፍሪቃና ፡ የእስያ ፣ ያውሮፓና ፡ ያሜሪካ ፥ እንዲሁም ፡ የዖቅያንያ ፡ መንግሥታትና ፡ ሕዝቦች ፥ የጠፉት ፡ ጠፍተው ፥ የተረፉት ፡ ደግሞ ፡ በጠባያቸው ፡ ተለውጠው ፡ ይገኛሉ ። ኢትዮጵያም ፡ በዚሁ ፡ ፈተና ፡ ከባድ ፡ ዋጋን ፡ እየከፈለች ፡ ዐልፋ ፥ ተለዋውጣ ፥ ኹላችን ፡ በምናውቀውና ፡ በሚያሳስበን ፡ ኹኔታ ፡ ውስጥ ፡ ትገኛለች ። የብርሃን ፡ ዘመኑ ፡ ያመጣው ፡ የርትዕ ፡ አስተሳሰብ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ዐዲሷ ፡ አይደለምና ፥ ጸናችበት ፡ እንጂ ፡ አልፈረሰችበትም ፤ ተረታችለት ፡ እንጂ ፥ አልተረታችበትም ።

የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡ ወይም ፡ "ሥልጡንሕዝብና" ፥ በመሠረቱ ፥ የርትዕ ፡ ሥልጣኔ ፡ ነው ። ኢትዮጵያ ፥ በሀገራዊ ፡ ሥርዐቷ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ የሚከበርባት ፥ ሰው ፡ በሰውነቱ ፡ የሚታይባትና ፥ በሕግ ፡ ፊት ፡ ኹሉም ፡ የተስተካከለባት ፤ ከራሷም ፡ ዐልፋ ፥ የተጠቁ ፡ ኹሉ ፡ ከቅርብም ፡ ከሩቅ ፡ ሀገር ፡ መጥተው ፡ የሚጠጉባትና ፡ የሚተርፉባት ፡ እውነተኛ ፡ "ሀገር" ፡ መኾኗ ፡ ተመስክሮላታል ። ነገደ ፡ ዮቅጣን ፡ ከመካከለኛው ፡ ምሥራቅ ፡ ተሰደው ፡ በሰላም ፡ የሰፈሩባት ፤ የክርስትና ፡ አባቶች ፡ ከሮም ፡ ምልካዊ ፡ ጥቃትና ፡ ብደላ ፡ ሸሽተው ፡ የተረፉባት ፤ የእስልምናው ፡ ነቢይ ፡ የሙሐመድ ፡ ወገኖች ፡ ከሀገራቸው ፡ ተሳደው ፡ የተጠጉባትና ፥ ሃይማኖታቸውን ፡ በሰላም ፡ ያስፋፉባት ፡ ብፅዕት ፡ ሀገር ፡ ናት ።

ዐልፎ ፡ ዐልፎም ፥ ከሀገራዊው ፡ የርትዕ ፡ ሥርዐት ፡ ውጪ ፥ ዐምባ ፡ ገነኖች ፡ የወነበዱበትንም ፥ በዘረፋና ፡ በሽፍትነት ፡ የሚተዳደሩ ፥ የሀገራዊነትን ፡ ጣዕም ፡ ገና ፡ ያልቀመሱ ፡ ጎሳዎችም ፡ የዘረፉበትንና ፡ የመዘበሩበትን ፡ ቀውጢ ፡ ዘመንም ፡ ያስተናገደች ፡ ሀገር ፡ ናት ። በድምሩ ፡ ግን ፥ ኢትዮጵያ ፡ መመዘን ፡ ያለባት ፡ በቋሚ ፡ ሀገራዊ ፡ ሥርዐቷ ፡ እንጂ ፥ በእየዘመኑ ፡ በደረሱ ፡ የውንብድና ፡ ወቅቶች ፡ ሊኾን ፡ አይገባም ። ይህም ፡ በመኾኑ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሥልጣኔ ፡ ርቱዕነት ፡ በተለይ ፡ በቅኝ ፡ ግዛት ፡ ተደጋጋሚ ፡ ወረራዎች ፡ ላይ ፡ ባሳየው ፡ የበላይነት ፡ ተረጋግጧል ።

ታዲያ ፡ ዛሬ ፡ ምን ፡ አገኘን ፧ ምን ፡ ነካን ፧

ትውልዱ ፡ ምንን ፡ ተመግቦ ፣ እንዴትስ ፡ ተኰትኵቶ ፡ አደገ ፧ ማንን ፡ አክብሮ ፥ ማንንስ ፡ ንቆ ፧ ከቶ ፡ ይህን ፡ የወሰነብንስ ፣ ያስፈጸመብንስ ፡ ማን ፡ ይኾን ፧ በየትኛውስ ፡ አገባብ ፧ መቼ ፧ ለምን ፧ የሚሉ ፡ ብዙ ፡ ጥያቄዎች ፡ ባእምሯችን ፡ ዘወትር ፡ ይጕላላሉ ። በየምክንያቱም ፡ ወይ ፡ ላንዱ ፡ ወይ ፡ ለሌላው ፡ ጥያቄ ፡ መልሱን ፡ እያገኘን ፥ "ለኹሉሳ ፧ " ፡ ስንል ፡ ደግሞ ፥ በጠቅላላው ፥ አኹንም ፡ መልሱ ፡ "ንኊልዮሽ" ፡ ኾኖ ፡ እናገኘዋለን ።

ንኊልዮሽ ፥ ባጋጣሚ ፡ አልወደቀብንም ፤ ምናልባት ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ እየወለደ ፡ በተከታተሉ ፡ አራት ፡ ረድፎች ፡ ተረማምዶብናል ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ፦

- የመዠመሪያው ፡ ረድፍ ፥ ከ 1901 ፡ ዓ.ም ፡ እስከ ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፥ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ ዘመን ፤
- ኹለተኛው ፡ ረድፍ ፥ ከ 1933 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፥ የስእነት ፡ ዘመን ፤
- ሦስተኛው ፡ ረድፍ ፥ ከየካቲት ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ ግንቦት ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፥ የውንብድና ፡

7 Age of Enlightenment | age de lumière.


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ዘመን ፤

• አራተኛውና ፡ የመጨረሻው ፡ ረድፍ ፥ ከግንቦት ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፥ የ"ዩጎስላቪዜሽን" ፡ ዘመን ።

ለእያንዳንዱ ፡ ረድፍ ፡ ማስረጃውን ፡ እዚህ ፡ ማቅረቡ ፡ "ለቀባሪው ፡ አረዱት" ፡ ስለሚኾን ፥ ለየረድፉ ፡ ከዋና ፡ ዋና ፡ ደረጃዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ጥቂቶቹን ፡ በክፍል ፡ 2 ፡ እዘረዝርና ፥ በተለይ ፡ በምንገኝበት ፡ ባራተኛው ፡ ወሳኝ ፡ ረድፍ ፡ አኹን ፡ የሚታየውን ፡ አደጋና ፡ ሊከተል ፡ የታቀደውን ፡ ጥፋት ፡ አመልክቼ ፥ በ 3ኛውና ፡ መጨረሻ ፡ ክፍል ፡ ንትልዮሽ ፡ ለደገሰልን ፡ ጥፋት ፡ ማብረሻዎቹ ፡ ይኾኑ ፡ የመሰሉኝን ፡ ሀገራውያን ፡ ሥራዎች ፡ ባጪሩ ፡ ጠቍሜ ፡ አጠቃልላለኹ ።



## ክፍል ፡ 2/3 ፤

## ንትልዮሽና ፡ ተወራራሽ ፡ ጥፋቶቹ ።

*"I later asked Sir Willie Morris, who had been our Ambassador in Addis Abeba at the time of the revolution, if it had been Russian or Chinese agents who had introduced communism into Ethiopia. He answered, «There was no need. The revolution was largely brought about by British and American school teachers and university lecturers.»"*

Wilfred Thesiger, ***The Life of My Choice***, London, 1987 AD.

የሚከተሉት ፡ 4 ፡ ረድፎች ፥ እያንዳንዳቸው ፡ ሙሉ ፡ መጽሐፍ ፡ አይበቃቸውም ፤ ልዘርዝር ፡ ቢሉ ፡ የማይጨረስ ፡ ውቂያኖስ ፡ ስለሚኾን ፥ ሳላበዛ ፥ ፍሬ ፡ ነገሩን ፡ ብቻ ፡ በጥቂት ፡ አረፍተ ፡ ነገር ፡ ሰብስቤ ፡ አስታውሳለኹ ። በሌላ ፡ ኹኔታ ፥ የታሪክ ፡ ተመራማሪዎች ፡ እነዚህን ፡ የታሪክ ፡ ረድፎች ፡ ሊመረምሯቸውና ፡ በመጽሐፍ ፡ አሟልተው ፡ ሊመዘግቧቸው ፡ ይገባል ። እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ስናነሣ ፡ ነው ፡ "የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ገና ፡ አልተጻፈም!" ፡ የሚያሠኘን ፤ አዎን ፥ ገና ፡ አልተጻፈም ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ አንባብያንን ፡ ለማሳሰብ ፡ ያኽል ፥ ስለ ፡ ታሪክ ፡ ስንጽፍ ፥ ዛሬ ፡ በሕይወት ፡ ዐብረውን ፡ የማይገኙ ፡ ያለፉ ፡ አባቶችንና ፡ እናቶችን ፥ ስም ፡ ጠርተንም ፡ ኾነ ፡ ሳንጠራ ፥ ማንሣታችን ፡ አይቀርምና ፥ ባንዳንድ ፡ ኹኔታ ፡ "ሙት ፡ ወቃሽ" ፡ ሊያሠኙ ፡ የሚችሉ ፡ አገላለጾች ፡ ይገጥማሉ ። ለመውቀስ ፡ አስቀድሞ ፡ ሞያን ፡ ሠርቶ ፡ መገኘት ፡ ያሻል ፤ የኾነውን ፡ በመግለጽና ፡ በማስታወስ ፡ እንጂ ፡ በወቀሳ ፡ መንፈስ ፡ አንድም ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ ትረካ ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ እንዳልሰፈረ ፡ አንባብያን ፡ እንዲረዱልኝ ፡ እለምናለኹ ። ምናልባት ፡ ከተለመደው ፡ ትረካ ፡ ለየት ፡ ያለ ፡ ቢኖር ፥ አንባብያን ፡ ሊያውቁት ፡ ስለሚገባና ፡ ለታሪካችንም ፡ ማስረጃ ፡ ስለሚኾን ፥ ባጪሩ ፡ ተጠቅሷል ።

### 1 ፤ የመዠመሪያው ፡ ረድፍ ፥ ከ 1901 ፡ ዓ.ም ፡ እስከ ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፥ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ ዘመን ፤

ከዳዊት ፡ ዘር ፡ የሚወርደው ፡ ሰሎሞናዊው ፡ ዘርዐ ፡ ነገሥት ፥ በቃል ፡ ኪዳኑ ፡ መሠረት ፥ በወንድ ፡ ዘርፍ ፡ እየተወራረሰ ፥ ኢትዮጵያን ፡ ለ 3000 ፡ ዓመት ፥ ከሞላ ፡ ጐደል ፥ በሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ገዝቷል ፤ ሐራነቷንም ፡ አስጠብቋል ።

ከ 1857 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 1906 ፡ ዓ.ም. ፡ የነገሡት ፡ ታላቁ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዳግማዊ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፥ ባለመታደል ፥ አንድያ ፡ ወንድ ፡ ልጃቸው ፥ አቤቶ ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ምኒልክ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ቢሞቱባቸው ፥ በ 1901 ፡ ዓ.ም. ፥ ዘውዳቸውን ፡ ለሴት ፡ ልጃቸው ፡ ልጅ ፥ ለልጅ ፡ ኢያሱ ፡ አወረሱ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ፈረሰ ፥ ሥርዐተ ፡ መንግሥቱም ፡ በገቢር ፡ ተጣሰ ። ከንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ በወንድ ፡ ዘርፍ ፡ የሚወለዱ ፡ ሌሎች ፡ መሳፍንት ፡ ሳይጠፉ ፥ በወንድ ፡ ዘርፍ ፡ ሊቀጥል ፡ የሚገባው ፡ ንግሥና ፥ "ዘውዱ ፡ ከልጆቼ ፡ አይውጣ" ፡ በሚል ፣ መሣሣትን ፡ በሚመስል ፡ ውሳኔ ፥ አለዚያም ፡ በቅርብ ፡ አማካሪዎች ፡ ተቃውሞ ፥ በሴት ፡ ዘርፍ ፡ እንዲቀጥል ፡ ተደረገ ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ከንጉሥ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ከሚወለዱት ፡ መሳፍንት ፡ ውስጥ ፥ ምናልባት ፡ ለራስ ፡ ዳርጌ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ለዝነኛው ፡ ፊታውራሪ ፡ አስፋው ፡ ዳርጌ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፥ አለዚያም ፡ ከመርድ ፡ አዝማች ፡ ኀይሌ ፡ ሣህለ ፡ ሥላሴ ፡ ለሚወለዱት ፡ ለፊታውራሪ ፡ ጉልላቴ ፡ ኀይሌ ፥ ዐልጋቸውን ፡ ባወረሱና ፡ መሳ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ባስደሰቱም ፡ ባረጋጉም ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፥ ፊታውራሪ ፡ አስፋው ፡ ዳርጌ ፥ በመሠረተ ፡ ቢስ ፡ ጥርጣሬ ፡ ፊቱኑ ፡ ተይዘው ፡ ታስረው ፡ ነበር ። የፊታውራሪ ፡ ጉልላቴን ፡ መንገሥ ፡ ደግሞ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡ ይቃወሙ ፡ ነበር ፡ ይባላል ። በሌላ ፡ ዘርፍ ፡ ከሚወለዱት ፡ መሳፍንትም ፡ ላንደኛው ፡ ዘውዱን ፡ ሊያወርሱ ፡ በቻሉ ፡ ነበር ፤ ይህም ፡ ሳይኾን ፡ ቀረ ። *"ያፄ ፡ ሥርዐቱ ፥ ያብርሃም ፡ ራቱ ፡ አይጓደልም"* ፡ ይባልባት ፡ የነበረችው ፡ ኢትዮጵያ ፥ ድንገት ፡ እሥርዐት ፡ ጉድለት ፡ ውስጥ ፡ ገባች ። የይገባኛል ፡ ጥያቄው ፡ ለጊዜው ፡ ቢታፈንም ፡ ቅሉ ፥ ሕዝቡን ፡ በየወገኑ ፡ ሊከፋፍለው ፡ ግዴታ ፡ ኾነ ። የታፈነው ፡ የይገባኛል ፡ ጥያቄ ፥ በሌላ ፡ መልክ ፡ አቂሞ ፥ የውጭ ፡ ኀይሎችን ፡ እጅ ፡ የሚያስገባ ፥ ከተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ የመነጨ ፡ የስያሳ ፡ ንቃቃትን ፡ ፈጠረ ። በሴት ፡ ዘርፍ ፡ የሚወለዱትም ፡ ለይገባኛል ፡ ጥያቄው ፡ አቈበቈቡ ፤ መካሮቻቸውም ፡ ተደረቡላቸው ፤ የውጭ ፡ ኀይሎችም ፡ ለቅኝ ፡ ግዛት ፡ ዐቅዳቸው ፡ መልካም ፡ አጋጣሚን ፡ ፈጠረላቸው ።

አለዕድሜያቸውና ፡ አለብስለታቸው ፡ ለዚህ ፡ ታላቅ ፡ ሀገራዊ ፡ ኀላፊነት ፡ በዚህ ፡ ኹኔታ ፡ የተሠየሙት ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፥ በሰል ፡ ቢሉ ፡ ምናልባት ፡ የማይፈጽሙትን ፡ የሒሳብ ፡ ስሕተት ፡ ፈጸሙ ። ከኢትዮጵያ ፡ ታሪካዊ ፡ ብሔር ፡ ከመሳው ፡ ያፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡ የፈረንሳይን ፣ የእንግሊዝንና ፡ የኢጣሊያን ፡ ቅርምቶች ፡ አስጥላለኹ ፡ በሚል ፡ ትኽክለኛ ፡ ዐላማ ፥ ነገር ፡ ግን ፡ ዐቅምን ፡ ያላገናዘበ ፡ ስያስ ፥ ባንደኛው ፡ ዓለም ፡ ጦርነት ፡ ዋዜማ ፡ ላይ ፥ መንግሥታቸውን ፡ ከጀርመንና ፡ ከቱርክ ፡ መንግሥታት ፡ ጋራ ፡ አሰለፉ ። በዚህ ፡ አደራረጋቸው ፡ በተለይ ፡ የፈረንሳይንና ፡ የብሪታንያን ፡ መንግሥታት ፡ ዐቅዳዊ ፡ ጠላትነትን ፡ ጋበዙ ። እነዚህ ፡ የቅኝ ፡ ግዛት ፡ ኀይሎችም ፥ *"ተገቢ"* ፡ ያሉትን ፡ የጣልቃ ፡ ገብነት ፡ ምክንያት ፡ አግኝተው ፥ *"የሤራ ፡ ፖለቲካውን"* ፡ ተያያዙት ። ወዲያው ፥ የልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ዐልጋ ፡ ተገልብጦ ፥ የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ቀጠለ ፤ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንንም ፡ እንዲሁ ፡ ለዘውድ ፡ ሙሉ ፡ ተገቢነት ፡ ሳይኖራቸው ፡ በዐልጋ ፡ ወራሽነት ፡ እሥልጣኑ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ ወጡ ። ርግጥ ፡ ነው ፥ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ሲነግሡ ፥ የወንድ ፡ ዘርፍ ፡ እስኪገኝ ፡ በጊዜያዊነት ፡ ተብሎ ፡ በመኳንንቱ ፡ ተመክሮ ፡ ነበር ፡ ይባላል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ቀድሞ ፡ የታየውን ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ አባባሰው ፡ እንጂ ፡ አላሻሻለውም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፥ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፥ በስመ ፡ መንግሥታቸው ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተብለው ፡ ከነገሡበት ፡ ከ 1923 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ 1928 ፡ ዓ.ም. ፡ ድረስ ፥ መንግሥታቸው ፡ የመሳውን ፡ መሳፍንት ፣ የመሳውን ፡ መኳንንትና ፡ የመሳውን ፡ ሕዝብ ፡ ውዴታና ፡ ድጋፍ ፡ ያላገኘ ፡ ደካማ ፡ ኾነ ።

ርግጥ ፡ ነው ፥ ዘመኑ ፡ የምዕራብ ፡ ሥልጣኔ ፡ ውጤቶች ፡ የኾኑት ፡ የኪነት ፡ መሣሪያዎች ፡ (ባቡር ፣ መኪና ፣ ስልክ ፣ የኤሌትሪክ ፡ ኀይል ፣ ወዘተ.) ፡ እና ፡ ዐብረው ፡ የሚመጡት ፡ የሥርዐት ፡ መሻሻሎች ፡ በዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ባገሪቱ ፡ ገብተው ፡ ነበርና ፥ ባፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥትም ፡ መስፋፋታቸው ፡ ቀጠለ ።

ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ በተለይ ፡ ለዘመናዊ ፡ ሥርዐተ ፡ ትምህርት ፡ ልዩ ፡ ትኵረት ፡ ሰለ ፡ ነበራቸው ፥ የቅኝ ፡ ግዛት ፡ ኀይሎችን ፡ ተቃውሞ ፡ እየታገሉ ፥ ዐቅማቸው ፡ የፈቀደውን ፡ ያኽል ፡ ምዕራባዊ ፡ ጥበብንና ፡ ዕውቀትን ፡ በሀገሪቱ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሊያስፋፉ ፡ ሞክረዋል ፤ ዘመናዊት ፡ ኢትዮጵያንም ፡ እንዲሁ ፡ ለመፍጠር ፡ ተጣጥረዋል ። በዚህ ፡ ረገድ ፥ *"ዘመናዊ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት"*ም ፡ ያስፈልጋል ፡ በሚል ፡ ሐሳብ ፥ በኢትዮጵያ ፡ ጥንታዊ ፡ ዐፄ ፡ ሥር ፡ ወይም ፡ ሥርዐተ ፡ ነገሥት ፡ ላይ ፥ ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡— *"ሰጥተነዋል"* ፡ ሲሉ ፥ ያ 1924 ቱን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አጸደቁ ።

ኢትዮጵያ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ትተዳደርበት ፡ የነበረው ፡ ሥርዐተ ፡ ነገሥት ፥ በ 1262 ፡ ዓ.ም. ፡ ባፄ ፡ ይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፥ በሕዝብ ፡ እንደራሴዎች ፡ ተሠርቶ ፡ የጸደቀው ፡ ዐፄ ፡ ሥር ፡ ነበር ። *"ታዲያ ፡ ዛሬ ፡ እንዴት ፡ ሕዝብ ፡ ሳይመክርበት ፥ በሥርዐተ ፡ ነገሥት ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ይጫናል ፧ "* ፡ የሚል ፡ ቍጭትንና ፡ ተቃውሞን ፡ እዘመኑ ፡ ሊቃውንት ፣ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ ዘንድ ፡ አስነሣ ። በተለይ ፡ ደግሞ ፥ *"በሥርዐተ ፡*


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ነገሥቱ ፡ መሠረት ፥ በወንድ ፡ ዘርፍ ፡ የሚወለዱ ፡ ለዘውዱ ፡ የሚገቡ ፡ መሳፍንት ፡ እያሉ ፥ እንዴት ፡ ባቋራጭ ፡ ሴላ ፡ ይይዘዋል ፨ " ፡ በሚል ፡ ክርክር ፡ የተነሣው ፡ መለያየት ፥ ረድፍ ፡ በረድፍ ፡ እየወረደ ፥ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ እየተዛመተ ፥ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መከፋፈልን ፡ ፈጠረ ። ኢትዮጵያ ፡ በተጋለጠችበት ፡ በዚህ ፡ ኹኔታ ፥ የኢጣሊያ ፡ ፋሺስት ፡ ይዘት ፥ የብሪታንያንና ፡ የፈረንሳይን ፡ ማበራቻ ፡ አግኝቶ ፥ በ 1928 ፡ ዓ.ም. ፡ ኢትዮጵያን ፡ በቅኝ ፡ ግዛትነት ፡ ወሮ ፡ ለመያዝ ፡ ሲዘምትባት ፥ ያሳዝናል ፥ በሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ ምክንያት ፡ ተዳክሞ ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጣን ፥ መመከት ፡ ተስኖት ፡ ሀገሪቱን ፡ ለቆ ፡ ለመሰደድ ፡ በቃ ።

እንሆ ፥

- አንድም ፥ ሀገሪቱን ፡ ከከበበው ፡ የቅኝ ፡ ግዛት ፡ ኀይል ፡ አደጋ ፡ የተነሣ ፥ ነገሥታቱ ፥ በውርስ ፡ ምክንያት ፡ የሚመጣን ፡ የሥልጣን ፡ ጦርነት ፡ ለማስወገድ ፡ ሲሉ ፡ በወሰኑት ፡ ውሳኔ ፡ ሥርዐትን ፡ ሲጥሱ ፥ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ ተፈጠረ ፤
- አንድም ፥ ዘመናዊነትን ፡ በመሻትና ፡ "ነበር"ን ፡ በመርሳት ፡ የተኳደለውን ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፥ በዘመናዊ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅትና ፡ ኀይል ፡ ደግፎ ፥ ማንኛውንም ፡ ተቃዋሚ ፡ እየደመሰሱ ፡ የሚኼዱበት ፡ "ማኪያቬሊያዊ" ፡ የስያሳ ፡ ስልት ፡ ያገዛዙ ፡ ዘይቤ ፡ ኾነ ።

ኹኔታው ፡ በጠቅላላ ፡ ላፍራሽ ፡ የንኊልዮሽ ፡ ኀይሎች ፡ ተመቻቸላቸው ፦

- ሀገራዊው ፡ ሥርዐት ፡ ተዳክሞ ፡ ቈያቸው ፤
- የመንግሥት ፡ ተቃዋሚና ፡ ተከፊታ ፡ በቀላሉ ፡ ተገኙላቸው ፤
- በላቀ ፡ የጦር ፡ ድርጅት ፡ ቢያጠቁት ፥ ሀገራዊው ፡ ሥልጣን ፡ የማይመክታቸው ፡ መኾኑን ፡ አረጋገጡ ።

ወዲያው ፥ ፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ወረረችን ፤ ስድስት ፡ ወር ፡ ባልሞላ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊውን ፡ ጦር ፡ በታትና ፥ እመናገሻ ፡ ከተማችን ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ በጠላትነት ፡ ገባች ። የንኊልዮሽ ፡ ዠንፎ ፡ የኾነው ፡ "ፋሺዝም" ፥ ለጊዜውም ፡ ቢኾን ፥ መኰራሪያውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ አገኘ ።

ኾኖም ፥ ለፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ የተንበረከከላት ፡ ስላልተገኘ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ዐርበኞች ፡ በተነሡበት ፥ በማይሞተው ፡ ሥልጡንሕዝብናቸው ፥ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ታግለውና ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ አባረሯት ፤ ጥንታዊ ፡ መንግሥታቸውን ፡ አሸጋግረው ፥ የተሰደዱ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸውንም ፡ ለመቀበል ፡ በቁ ። ይህ ፡ ተጋድሏቸው ፥ ከኢትዮጵያም ፡ ዐልፎ ፡ በቅኝ ፡ ግዛት ፡ ሥር ፡ ለነበሩት ፡ የዓለም ፡ ሕዝቦች ፡ ኹሉ ፡ አርኣያ ፡ ኾኗቸው ፥ እነርሱም ፡ ተራቸውን ፡ ለትግልና ፡ ለነጻነት ፡ በቁ ።

የንኊልዮሽ ፡ መዘዝ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ አላበቃም ።

**2 ፤ ኹለተኛው ፡ ረድፍ ፥ ከ 1933 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፥ የስእነት ፡ ዘመን ፤**

የተገቢነት ፡ ሕጸጹ ፡ ባይወገድም ፥ በድል ፡ አድራጊነት ፡ ለተመለሰውና ፡ በወቅቱ ፡ ማማረጫ ፡ ላልተገኘለት ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ "አሜን" ፡ ብሎ ፡ ተገዛ ። "ምንም ፡ በሙቱ ፥ ዐራድማ ፡ ሸምቱ" ፡ ነውና ፥ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥት ፡ የቀድሞ ፡ ጸጋውን ፡ ያልተገፈፈ ፥ አርዕድ ፡ አንቀጥቅጥ ፡ ያለው ፥ ሥነ ፡ ሥርዐቱ ፡ የሚያኰራ ፥ የሕዝብ ፡ አለኝታ ፡ ነበር ።

ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግን ፥ ሕዝቡ ፡ ምን ፡ ቢገዛላቸው ፥ ያለባቸውን ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ ምናልባት ፡ ስላልረሱ ፥ የሕዝብን ፡ ሙሉ ፡ ችሎት ፡ ከሥራ ፡ ሊያሳትፉ ፡ አልወደዱም ። ሀገራዊውን ፡ ሥልጣን ፡ ለብቻቸው ፡ ጠቅልለው ፡ ጨብጠው ፡ በመያዝ ፡ ገዙ ። ባንድ ፡ ሰው ፡ ችሎታ ፡ የተወሰነው ፡ ሀገራዊው ፡ ሥልጣንም ፡ በውጤቱ ፡ ደካማ ፡ ኾነ ። በይፋ ፥ "ዘመናዊነትን ፡ አስፋፋለኹ ፤ እድገትን ፡ አመጣለኹ" ፡ ቢልም ፡ ቅሉ ፥ የሞላውን ፡ ሕዝብ ፡ ችሎት ፡ ሊያሳትፍ ፡ ባለመፍቀዱ ፥ ያንዲት ፡ ታላቅ ፡ ሀገር ፡ ምርት ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ምግብና ፡ ሊቀጭጭ ፡ ግዴታ ፡ ኾነ ። ጥንታውያን ፡ ሥልጣኔዎች ፥ እነቻይና ፣ እነህንድ ፣ እነጃፓን ፡ በልማታቸው ፡ ሲመነደጉ ፥ ኢትዮጵያ ፡ እዚያው ፡ አዘብጥጣ ፡ ቀረች ።

ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ስማቸውን ፡ የሚያስጠሩ ፡ ብዙ ፡ ሥራዎችን ፡ ለሀገራችንም ፣ ላፍሪቃም ፣ ለዓለምም ፡ በጠቅላላው ፡ ሠርተዋል ። በሀገር ፡ ደረጃ ፥ በርሳቸው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የመዠመሪያዎቹ ፡ የግእዝም ፡ ያማርኛም ፡ መዛግብተ ፡ ቃላት ፡ ተሰናድተው ፡ ታትመዋል ። የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ የራሷን ፡ ፓትሪያርክ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

መሠየም ፡ የቻለችው ፡ በርሳቸው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። በውጭ ፡ ስያሳና ፡ በመባሕታዊ ፡ መስክ ፡ ደግሞ ፥ በቅኝ ፡ ገዢዎች ፡ ግፍ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ተነጥላ ፡ የቈየችው ፡ ባሕር ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ እናት ፡ ሀገሯ ፡ መቀላቀሏ ፤ እንዲሁም ፥ ያፍሪቃ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ መቋቋምና ፥ መንበሩን ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ማስደረግ ፡ ትውልድ ፡ የማይረሳባቸው ፡ ውለታዎቻቸው ፡ ናቸው ። ቍጥብ ፣ ቍጥብ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፥ ሌሎች ፡ ስማቸውን ፡ በበጎ ፡ የሚያስጠሩ ፡ ዐያሌ ፡ ሥራዎችንም ፡ ሠርተዋል ። ማንኛውም ፡ የልማት ፡ ሥራ ፥ መጠኑ ፡ ለቀጣጥጥራቸው ፡ የማያስቸግር ፡ ሲኾን ፡ እንጂ ፥ ከዚያ ፡ በላይ ፡ አይፈቀድም ። በግል ፡ ተነሣሽነትም ፡ የንግድ ፡ ድርጅት ፡ ያቀደ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፥ *"ከፍ ፡ ያለ ፡ ዐቅምን"* ፡ የሚጠይቅ ፡ ቢኾን ፥ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሳይፈቅዱት ፡ አይፈጸምም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ዐያሌ ፡ የመንግሥትም ፡ የግልም ፡ የልማት ፡ ዕቅዶች ፥ *"ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እስኪፈቅዱ"* ፡ እየተባለ ፥ ሰነዶቻቸው ፡ በየምግብናው ፡ ተቈልለው ፡ ዐቧራ ፡ አልብሷቸው ፡ ቀርተዋል ።

በዘመናቸው ፡ በኀላፊነት ፡ የነበሩ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ዘወትር ፡ እያዘኑ ፡ የሚመሰክሩባቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ በደሎችም ፡ ነበሩ ። ለምሳሌ ፥ አንድ ፡ ባለሥልጣን ፡ በሥራው ፡ መልካምነት ፡ እሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ስሙ ፡ በበጎ ፡ የተጠራ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ወዲያው ፡ ይሻራል ፤ አለዚያም ፡ የሚያስከስሰው ፡ *"እንከን"* ፡ ተፈልጎለት ፡ ወይ ፡ ተፈጥሮለት ፡ ይከሰሳል ፣ ይጋዛል ፤ ከዚህም ፡ የከፋ ፡ አደጋ ፡ ያገኘዋል ። የማኪያቬሊ ፡ የስዕረት ፡ አገዛዝ ፡ ስልት ፡ በገቢር ፡ የተፈጸመበት ፡ ሀገር ፡ ቢኖር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በቀዳሚነት ፡ ትጠራለች ፡ ሲሉ ፡ ታዛቢዎች ፡ መስክረዋል ። በዚህ ፡ ረገድ ፥ ተጽፎ ፡ የማያልቅ ፡ አሳዛኝ ፡ ታሪክ ፡ አለ ። ይህኛው ፡ ያፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ገጽታ ፡ ገና ፡ አልተጻፈም ።

ይህ ፡ ኹሉ ፥ ከሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ የመነጨ ፡ *"ሳይቀድሙኝ ፡ ልቅደማቸው"* ፡ ከሚል ፡ የመከላከል ፡ ዐቅድ ፡ የመጣ ፡ መኾኑን ፡ ብዙዎች ፡ መስክረዋል ።

የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ ያለበት ፡ መሪ ፡ ደግሞ ፥ በግዴታ ፡ ለውጭ ፡ መንግሥታትና ፡ *"ለኀያላን"* ፡ ተጽዕኖ ፡ ይሸነፋል ።

በመሠረቱ ፥ በየትኛውም ፡ ዓለም ፥ የብቻ ፡ ሥሉጥ ፡ (autocrat) ፡ አገዛዝ ፥ በ *"ጥቀመኝ ፥ ልጥቀምኽ"* ፡ ግብይት ፥ ኀያላን ፡ መንግሥታትን ፡ ይጋብዛል ። በሥልጣን ፡ ሰገነቱ ፡ ላይ ፡ ለመቈየት ፡ ሲል ፥ መንግሥታዊውን ፡ ድርጅትና ፡ ኀይል ፡ ለማጠናከር ፡ የሚበጁትን ፡ የውጭ ፡ አማካሪዎች ፡ ጋብዞ ፡ ባገዛዙ ፡ ማሳተፍ ፡ ከውዴታነት ፡ ዐልፎ ፡ ግዴታውም ፡ ይኾናል ። ኀያላኑም ፥ በዚህ ፡ ኹኔታ ፡ ዘላቂና ፡ ዐቅዳዊ ፡ ጥቅማቸውን ፡ ለማረማመድ ፡ ሲሉ ፥ ለብቸ ፡ ሥሉጡ ፡ ሙሉ ፡ ተባባሪነታቸውን ፡ ቢያሳዩም ፥ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ የሚመጣው ፡ ኹኔታ ፡ በሚፈልጉት ፡ አግጣጫ ፡ እንዲለወጥ ፡ የማያቋርጥ ፡ የስርጀታ ፡ ሥራን ፡ ሊሠሩ ፡ ግዴታ ፡ ይኾናል ። በኢትዮጵያ ፡ የደረሰው ፡ ይህ ፡ ኾነ ።

ሱታፌው ፡ ከተርታው ፡ የሥራ ፡ መስክ ፡ ተነሥቶ ፡ እስከ ፡ ፍጹም ፡ ምስጢራዊው ፡ የጸጥታና ፡ የደኅንነት ፡ ሥራ ፡ መስክ ፡ እያደገ ፥ እኹል ፡ ገብ ፡ ኾነ ። የሥርዐተ ፡ ትምህርት ፡ አወጣጥ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ የገንዘብ ፡ አያያዝና ፡ የወርቅ ፡ ንግድም ፡ ቍጥጥር ፡ ለውጭ ፡ አማካሪዎች ፡ የውሳጤ ፡ ቈራጭነት ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ተሰጠ ። የጦር ፡ ሰራዊት ፡ ማሠልጠኛው ፡ ተቋም ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ የደኅንነቱ ፡ መዋቅርም ፡ እባዕዳን ፡ አማካሪዎች ፡ ቍጥጥር ፡ ገባ ፤ *"ተቃዋሚን"* ፡ በመከላከል ፡ ሰበብ ፥ እውነተኛ ፡ አገር ፡ አፍቃሪዎች ፡ ከመንግሥታዊው ፡ አገልግሎት ፡ ተባረሩ ፤ ሊባረሩ ፡ ያልቻሉትም ፡ ለማያቋርጥ ፡ ግፍና ፡ ብቀታ ፡ ተዳረጉ ።

በክፍላተ ፡ ሀገር ፡ ኤርትራ ፣ ሐረርጌ ፣ ባሌ ፡ … ፥ የሕዝቡ ፡ ችግር ፡ በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ሊፈታ ፡ ሲገባው ፥ *"ዐማፅያንን ፡ ለመከላከል"* ፡ በሚል ፡ *ማመካኛ* ፥ የባዕድ ፡ የጸጥታ ፡ አማካሪዎች ፡ ባመለከቱት ፡ የ *"አንቲ-ኢንሰርጀንሲ"* ፡ ስልት ፥ ንጹሓን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባሠቃቂ ፡ ኹኔታ ፡ ከመገደላቸው ፡ ጋራ ፥ አፍራሻውን ፥ የተዘመተበትን ፡ ዐመፃ ፡ የሚኰተኵትና ፡ የሚያገነለብት ፡ ደባ ፡ ተፈጸመ ፤ መዘዙም ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ጕዳቱን ፡ ማድረስ ፡ ቀጥሏል ።

በግልጽም ፡ ባይኾን ፡ በውሳጤ ፥ መንግሥታዊው ፡ ችሎት ፡ በብዙ ፡ ረገድ ፡ በውጭ ፡ አማካሪዎችና ፡ በውስጥ ፡ ተባባሪዎች ፡ በቀላሉ ፡ ተሸመደመደ ።

ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ ለመስጠት ፡ ያኽል ፥ በተለይ ፥ ከ 1933 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፥ ምዕራባዊው ፡ ትምህርት ፡ በሥርዐተ ፡ ትምህርታችን ፡ ያንበሳውን ፡ ድርሻ ፡ ይዞ ፥ በፀረ ፡ ቅኝ ፡ ግዛት ፡ ጦርነቶች ፡ ያልተሳተፈውን ፡ ዐዲስ ፡ ትውልድ ፡

ተቀብሎ ፤ ሲያስተምር ፥ ከብዙ ፤ ጥቅሞቹ ፤ ጋራ ፥ ትውልዱን ፤ ከነባር ፤ ሥርዐቱም ፤ አፈናቀለው ። ወላጆቹን ፤ መስሎ ፥ ከውጪውም ፤ ትምህርት ፤ መልካሙን ፤ ኹሉ ፤ ይዞ ፤ በማፈል ፥ ሀገርን ፤ የሚጠቅም ፤ ትውልድ ፤ ከመኾን ፤ ይልቅ ፥ በብዙ ፤ ረገድ ፤ ወላጆቹን ፤ የናቀና ፤ የተፃረረ ፥ የውጪውንም ፤ ትምህርት ፤ ለከፍ ፤ ለከፍ ፤ አድርጎ ፤ እመኻል ፤ ላይ ፤ የተንገዋለለና ፤ የተደናገረውን ፤ ትውልድ ፤ ለመኾን ፤ በቃ ። በመንግሥታዊው ፤ አስተዳደርም ፤ የሚታየው ፤ መሽመድመድ ፤ የወጣቱን ፤ ትዕግሥት ፤ ተፈታተነው ። ለውጥ ፤ በመቶ ፤ ዓመትም ፤ የማይመጣ ፤ መሰለው ። *"በነውጥና ፤ በዐመፃ ፤ ካልኾነ ፤ በቀር ፥ ለውጥ ፤ ከሥርዐቱ ፤ ሊመጣ ፤ አይችልም"* ፤ ብሎ ፤ ደመደመ ። ለተከታዩ ፤ የንጉልዮሽ ፤ ረድፍ ፤ ተሰናድቶ ፤ ተገኘ ።

**3) ሦስተኛው ፤ ረድፍ ፥ ከየካቲት ፤ 1966 ፤ ዓ.ም. ፤ አንሥቶ ፤ እስከ ፤ ግንቦት ፤ 1983 ፤ ዓ.ም. ፥ የውንብድና ፤ ዘመን ፤**

በዚህ ፤ ዘመን ፥ ኢትዮጵያ ፥ የሌለባትን ፤ በሽታ ፤ ኹሉ ፤ *"አለብሽ"* ፤ ተባለች ። ለምሳሌ ፥ ባንዳንድ ፤ የጎሳ ፤ ልማዶች ፤ እንጂ ፥ በሀገራዊ ፤ ሥርዐታችን ፤ ታይቶም ፤ ተሰምቶም ፤ የማይታወቀውን ፤ የ*"ፊዎዳሊዝም"* ፤ በሽታ ፤ *"አለብሽ!"* ፤ ተብላ ፥ ተማሪዎቿ ፤ በሰበቡ ፤ ሀገራዊ ፤ ሥርዐታቸውን ፤ ጠልተው ፤ እንዲገረስሱት ፤ ተሰበኩ ። ከየካቲት ፤ 1966 ፤ ዓ.ም. ፤ እስከ ፤ ግንቦት ፤ 1983 ፤ ዓ.ም. ፤ ድረስ ፤ ያለው ፤ ዘመን ፥ በፍጹም ፤ ባዕድ ፤ በኾነ ፤ ኀሊና ፥ *"አብዮቱ"* ፤ በነባሩ ፤ ሀገራዊ ፤ ሥርዐታችን ፤ ላይ ፤ *"ሥር ፤ ነቀል"* ፤ ፍንቀላውን ፤ የፈጸመበትና ፥ ኹለተኛውን ፤ ትውልድ ፤ ለናላ ፤ ዕጥበትና ፤ ለርስ ፤ በርስ ፤ ጦርነት ፤ ማገዶነት ፤ የዳረገበት ፥ ለተከታዩም ፤ ሀገር ፤ በታኝ ፤ አራተኛ ፤ ረድፍ ፤ መንገድ ፤ የጠረገበት ፤ ዐይነተኛው ፤ የንጉልዮሽ ፤ ዘመን ፤ ኾነ ።

ካዲስ ፤ አበባ ፤ ወይም ፤ ከክፍለ ፤ ሀገር ፤ ከተማዎች ፤ ወጥተው ፤ የኢትዮጵያን ፤ የመሬት ፤ ሥሪት ፤ መመርመር ፤ ቀርቶ ፤ ያላዩ ፤ ተማሪዎችና ፤ ጥቂት ፤ ምሁራን ፥ በ*"መሬት ፤ ላራሹ"* ፤ ኀይለ ፤ ቃል ፤ ብቻ ፤ ተነሣሥተው ፥ ኢትዮጵያን ፤ ቀጥ ፤ አድርጎ ፤ ያቆመውን ፤ ዋና ፤ ምሰሶ ፥ ርስትን ፥ ፈንቅለው ፤ ጣሉት ፤ ሳያውቁ ፥ ሀገርንና ፤ ሕዝብን ፤ በደሉ ።

ሥልጡንሕዝባዊት ፤ (democratic) ፤ በተባለችው ፤ ታላቅ ፤ ብሪታንያ ፥ በዛሬ ፤ ዘመን ፥ 95% ፤ የሀገሪቱ ፤ ምድር ፤ (የዕርሻ ፤ መሬቶችን ፤ ጨምሮ) ፤ 40 ፤ ሺሕ ፤ በማይሞሉ ፤ የንጉሣውያን ፤ ቤተሰቦች ፤ አባላት ፤ ታላላቅ ፤ ከበርቴዎችና ፤ የንግድ ፤ ተቋማት ፤ ርስቶች ፤ መኾናቸው ፤ ይታወቃል ። የቀረው ፤ 5% ፥ ባብዛኛው ፤ የከተማ ፤ ቦታ ፤ ከመኾኑ ፤ ጋራ ፥ ከሙሉ ፤ ርስትነት ፤ (freehold) ፤ ይልቅ ፤ በኪራይ ፤ ይዞታነት ፤ (leasehold) ፤ ይመደባል ። ከብሪታንያ ፤ ተርታ ፤ ሕዝብ ፤ ውስጥ ፤ *"ርስት ፤ አለኝ"* ፤ የሚለው ፥ ባማካይ ፤ ከ 150 ፤ ሜትር ፤ ማእዘን ፤ የማይበልጥ ፤ የከተማ ፤ ቦታን ፤ እንጂ ፥ በገጠርስ ፤ ቅንጣት ፤ መሬት ፤ የለችውም ። ከደርግ ፤ በፊት ፤ የነበረው ፤ የኢትዮጵያ ፤ ኹኔታ ፥ ከዛሬው ፤ የብሪታንያ ፤ ኹኔታ ፤ እጅጉን ፤ የተሻለ ፤ እንደ ፤ ነበር ፤ መረጃዎች ፤ ኹሉ ፤ ያረጋግጣሉ ። በብዙ ፤ ሚልዮን ፤ የሚቈጠሩ ፤ ኢትዮጵያውያን ፤ ባለርስት ፤ ነበሩ ። ርግጥ ፤ ነው ፥ መሬቶቹ ፤ እጅግ ፤ ኋላ ፤ ቀር ፤ በኾነ ፤ የዕርሻ ፤ ልማት ፤ ዘዴዎች ፤ ከመታረሳቸው ፤ ጋራ ፥ ያስተዳደር ፤ ጕድለቶች ፤ የማንጓጓዣ ፤ ዕጥረቶች ፤ የመሬት ፤ ጥበቶች ፤ የተፈጥሮ ፤ አደጋዎች ፤ ተዳምረው ፤ ያስከተሉት ፤ እድገት ፤ አልቦነት ፤ ሕዝቡን ፤ ለአንጻራዊ ፤ ችጋር ፤ ዳርጎት ፤ ነበር ። የኾነው ፤ ኾኖ ፥ ሕዝቡ ፤ የማንንም ፤ እጅ ፤ ሳያይ ፥ ራሱን ፤ ችሎ ፤ በነጻነት ፤ የሚኖርባት ፤ ሀገር ፤ ነበረችው ።

ከዓለም ፤ ሀገሮች ፤ ኹሉ ፤ የባለርስቱ ፤ መጠን ፤ ከፍተኛ ፤ የኾነባት ፤ ኢትዮጵያ ፥ በጥቂት ፤ ቀናት ፤ የውንብድና ፤ ኀይሎች ፤ የምቀኝነት ፤ ውሳኔ ፥ ሕዝቧ ፤ ርስቱን ፤ እንዲህ ፤ ተነጥቆ ፥ እመናጢነት ፤ ወለል ፤ ላይ ፤ በድንገት ፤ ተነጠፈ ። ርስቱን ፤ በማጣቱ ፤ ራሱን ፤ መቻል ፤ የተሳነው ፤ ሕዝብ ፥ የርዳታ ፤ ድርጅቶች ፤ ተመጽዋች ፥ አለዚያም ፤ የስደት ፤ ጽዋን ፤ ቀማሽ ፤ ኾኖ ፥ በረኻርም ፤ ታሪኩ ፤ ለመዠመሪያ ፤ ጊዜ ፤ ካገሩ ፤ ተሰደደ ። የኢትዮጵያ ፤ ኦርቶዶክስ ፤ ተዋሕዶ ፤ ቤተ ፤ ክርስቲያንም ፥ መተኪያና ፤ ወደር ፤ በማይገኝላቸው ፤ የ 20 ፤ ምእትያ ፤ አገልግሎቶቿ ፤ ያገኘቻቸውን ፤ ርስቶቿን ፤ አላግባብ ፤ በጕልበት ፤ ተዘረፈች ።

ከነጭና ፤ ቀይ ፤ ሽብር ፤ የተረፉት ፤ የዚያ ፤ ዘመን ፤ ወጣቶች ፥ ዛሬ ፤ አርጅተው ፥ ያን ፤ በወላጆቻቸው ፤ ላይ ፤ የጠሉትን ፤ ርስት ፤ መልሰ ፤ ለማብጀትና ፤ ለልጆቻቸው ፤ ለማውረስ ፥ በስደት ፤ ዓለም ፤ የ 20 ና ፤ የ 30 ፤ ዓመት ፤ *"mortgage"* ፤ ገብተው ፥ ሞት ፤ ሳይቀድማቸው ፤ ከፍሎ ፤ ለመጨረስ ፤ ሲፍጨረጨሩ ፤ እናያለን ። በቀድሞ ፤ አገራቸው ፤ ደግሞ ፥ ዛሬ ፥ ያባቶቻቸው ፤ የእናቶቻቸው ፤ የቀድሞ ፤ ርስቶች ፤ ለባዕዳን ፤ መንግሥታትና ፤ ድርጅቶች ፤ በርካሽ ፤

ይቸበቸቡባቸዋል ። *"ምቀኛ ፥ ራሱን ፡ ይነቅል ፤ ጠላቱን ፡ ይተክል"* ፡ የሚሉት ፡ የአበው ፡ አባባል ፡ ምንኛ ፡ ተረጋገጠ!

የ*"ዘር ፡ ፖለቲካ"*ም ፡ በዚሁ ፡ *"በደርግ ፡ ዘመን"* ፡ ተተክሎብንና ፡ መድኀኒትን ፡ ዐጥቶ ፥ እንሆ ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ሕዝብን ፡ ያጨራርሳል ፥ ያፈናቅላል ፥ ያሰድዳል ።

ከፊተኛውም ፡ ጊዜ ፡ የባሰ ፥ በደርግ ፡ ዘመን ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ፈጽሞ ፡ የታጣበት ፡ የውንብድና ፡ ዘመን ፡ ነበርና ፥ ስእነቱም ፡ ፍጹም ፡ ኾነ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፥ የደርግ ፡ ይዘት ፡ ከኸሉ ፡ የባሰ ፡ ደካማና ፡ ለውጭ ፡ ኀይሎች ፡ ታዛዥ ፡ ኾነ ። ያሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ የጦር ፡ መሣሪያን ፡ ቢነፍገው ፥ ወደሶቪዬት ፡ ኅብረት ፡ ፊቱን ፡ አዞረ ፤ የህልውናው ፡ ጕዳይ ፡ ነውና ፥ የ*"ማርክሢዝም ፡ ሌኒኒዝም"* ፡ ፍልስፍናንም ፡ ሳይረዳው ፣ ሳይወደው ፡ በግዱ ፡ ተቀበለ ። *"ሾኽን ፡ በሾኽ"* ፡ እንዲሉ ፥ በ*"ማርክሢዝም ፡ ሌኒኒዝም"* ፡ መናጃ ፡ ነባሩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ግዛታዊ ፡ ሥርዐት ፡ ሲናድ ፥ ንጉሠ ፡ ነገሥት ... 

**4) አራተኛውና ፡ የመጨረሻው ፡ ረድፍ ፥ ከግንቦት ፡ 1983 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፥ የ*"ዩጎስላቪዜሽን"* ፡ ዘመን ፤**

እንዲህ ፡ በተዳከመች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላይ ፥ አሜሪካ ፡ ሠራሹ ፡ *"የአፓርትሀይድ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት"* ፥ የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ *"ሕዝቦች"* ፡ ብሎ ፡ የካደበት ፥ ዐማርኛን ፡ ከሀገራዊ ፡ ቋንቋነት ፡ አውርዶ ፡ ወደ ፡ ተርታ ፡ የሥራ ፡ ቋንቋነት ፡ የወረወረበት ፥ ኢትዮጵያን ፡ ባፈንጋጮች ፡ *"ክልሎች"* ፡ ከላሎ ፥ የዩጎስላቪያን ፡ ፍጻሜ ፡ በሚያስታውስ ፡ ውድቀት ፥ ለግንጣሌያቸው ፡ ያቃረበበት ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ ተዋቀረ ። በመኻከሉም ፥ የኢትዮጵያ ፡ መነሻ ፡ አካል ፡ የኾነችው ፡ ባሕር ፡ ምድር ፥ በውጭ ፡ ኀይሎች ፡ ተጽዕኖ ፡ ለ*"መገንጠል"* ፡ በቃች ።

ደርግ ፡ በውንብድናው ፡ የዘረፈው ፡ የድኻው ፡ ርስት ፥ ዛሬ ፡ በኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ ሕገ ፡ ውንብድና ፡ በዘረፋነት ፡ ጸንቶ ፥ ለቀጣዩ ፡ የ*"ካፒታሊዝም"* ፡ ምዕራፍ ፥ ለውጩ ፡ ዓለም ፡ ባለሀብቶች ፡ ሊሸጥ ፡ ተሰናድቷል ፤ ሸያጩ ፡ *"ሕጋዊ ፡ መሠረት"* ፡ እንዲኖረውም ፥ *"የርስት ፡ ሕግጋትን ፡ ማሻሻል"* ፡ የሚቀጥለው ፡ የሥራ ፡ ረድፍ ፡ ይኾናል ።

አላንዳች ፡ ውክልናም ፡ ኾነ ፡ ሥልጣን ፥ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፥ በዶክተር ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ አንደበት ፥ ይህን ፡ መጪ ፡ የ*"ካፒታሊዝም"* ፡ ምዕራፍ ፡ የሚቀበለው ፡ መኾኑን ፡ ገልጾ ፥ በመንግሥት ፡ እጅ ፡ የሚገኙ ፥ እንደኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድና ፡ ኢትዮቴሌኮም ፡ ያሉ ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ ለግል ፡ ባለሀብቶች ፡ እንደሚዛወሩ ፡ አስታውቋል ። ዐዲሱን ፡ ምዕራፍ ፡ ሲያበሥርም ፥ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተንባል ፡ ከፍራንሲስ ፡ ፉኩያማ (8) ፡ ጋራ ፥ ለሥምረታቸው ፡ ትምሳሊት ፡ እንዲኾን ፥ አንድ ፡ ዛፍ ፡ ተክለዋል ።

*"የዘፈን ፡ ዳር ፡ ዳሩ ፡ እስክስታ ፡ ..."* ፡ እንዲሉ ፤ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ በሚቼ ፡ አቶ ፡ መለስ ፡ ዜናዊ ፡ አንደበት ፦ *"መሬት ፡ የመንግሥት ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ ደርግ ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ አላመጣነውም"* ፡ አሠኝቶ ፡ የተከላከለበትንም ፥ በ*"ሕገ ፡ መንግሥቱ"* ፡ (አንቀጽ ፡ 40 ፣ ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ 3) ፡ *"መሬት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ፡ ሕዝቦች ፡ የጋራ ፡ ርስት ፡ ነው"* ፡ ካለ ፡ በኋላ ፥ በአንቀጽ ፡ 40 ፣ ንኡስ ፡ አንቀጽ ፡ 6 ፡ ደግሞ ፡ *"በሕጉ ፡ መሠረት ፡ ተፈላጊውን ፡ ክፍያ ፡ የከፈሉ ፡ የግል ፡ ባለሀብቶች ፡ በመሬቱ ፡ የመጠቀም ፡ መብታቸውን ፡ መንግሥት ፡ ያረጋግጥላቸዋል"* ፡ ሲል ፥ የኀያላኑን ፡ ንጥቂያና ፡ ቅርምት ፡ አስቀድሞ ፡ *"ተገቢ"* ፡ አሠኝቷል ። የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ርስት ፥ ዛሬ ፡ ማንም ፡ ባለሀብት ፥ ኢትዮጵያዊም ፡ ኾነ ፡ ባዕድ ፥ መጥቶ ፡ በገንዘብ ፡ የሚገዛውና ፥ ሲፈልግ ፡ የሚያለማው ፣ የሚበክለውም ፥ የሚለውጠው ፣ ዐጥሮ ፡ የሚዘጋውም ፡ የብቻው ፡ መበልጸጊያ ፡ ኾኗል ። ባለቤቶቹ ፡ ናቸው ፡ የተባሉት ፡ *"ብሔሮች ፣ ብሔረሰቦችና ፡ ሕዝቦች"* ፥ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ *"ነገሮች"* ፡ እንጂ ፥ በእውንና ፡ በገቢር ፡ *"ባለቤት"* ፡ ለመኾን ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ አካልም ፡ ኾነ ፡ ህልውና ፡ የሌላቸው ፡ ባዶዎች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ ንጥቂያውና ፡ ቅርምቱ ፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ ውስጥ ፡ ፍጹም ፡ ኾኗል ። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ እስካልተወገደና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እግዚእናውን ፡

8 ፍራንሲስ ፡ ፉኩያማ ፡ (Francis Fukuyama) ፥ *"The End of History and the Last Man"* ፡ የተባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ የደረሰ ፡ (1983 ፡ ዓ.ም.) ። *"አባይን ፡ ያላየ ፡ ምንጭ ፡ ያመሰግናል"* ፡ እንዲሉ ፥ *"ኮምዩኒዝምን ፡ ከደመሰሰው ፡ ከ Anglo-Saxon ፡ ሥልጣኔ"* ፡ የተሻለ ፡ አይመጣም ፡ በሚል ፡ ትምክሕት ፥ ከክብሩና ፡ ከጥቅሙ ፡ ይቋደስ ፡ ዘንድ ፡ ሡክቶ ፥ በጀርመናዊው ፡ በሄጌል ፡ ፍልስፍና ፡ መሠረት ፥ ነጭ-አልዓሊ ፡ ስብከትን ፡ የሚያረማምድ ፡ ትውልደ ፡ ጃፓናዊ ፡ አሜሪካዊ ፡ ደራሲና ፡ የሥነ ፡ ግዛት ፡ ወይም ፡ የግዛትኛ ፡ መምህር ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ወይም ፡ ባለቤትነቱን ፡ ባዲስ ፡ ሕገ ፡ *መንግሥት* ፡ እስካላረጋገጠ ፡ ድረስ ፥ የርስት ፡ ነገር ፡ ከባዕዳን ፡ ይዞታነቱ ፡ አይወጣም ፤ የንጉልዮሽ ፡ መድረሻ ፡ ውጤት ፡ ንጥቂያና ፡ ቅርምት ፡ ነውና ።

ንጥቂያውና ፡ ቅርምቱ ፡ እስኪረጋገጥ ፡ ድረስ ፥ የንጉልዮሽ ፡ ከፋፋይ ፡ ስብከት ፥ ከትምህርት ፡ ቤቱ ፡ እስከ ፡ ምድራሱ ፡ (እስከ ፡ *"ዩኒቨርስቲው"*) ፥ ከሕዝባዊው ፡ ማኅበር ፡ እስከ ፡ መንግሥታዊው ፡ ተቋም ፥ ከግሉ ፡ ማወራኛ ፡ እሰከ ፡ መንግሥታዊው ፡ ማወራኛ ፡ ድረስ ፥ ጧት ፡ ማታ ፡ ተጠናክሮ ፡ ይሰበካል ። የ*"ፖለቲካ ፡ ፍካሬው"* ፡ ሳይቀር ፡ (*"ሕዝቦች"*፣ *"ብሔር"*፣ *"ብሔረሰብ"*፣ *"ክልል"*፣ *"ዴሞክራሲ"*፣ *"ሳይንሳዊ"*፣ *"ምክንያታዊ"*፣ *"መቻቻል"*፣ *"የራስን ፡ ዕድል ፡ በራስ ፡ መወሰን ፥ እስከ ፡ መገንጠል"*፣ *"የሕዝብ ፡ ለሕዝብ ፡ ግንኙነት"*፣ *"ብሔራዊ ፡ መግባባት"*፣ *"ሰላም"*፣ *"ሰላም"*፣ *"ሰላም"*፣ ... ፡ እያለ) ፥ ሕዝብን ፡ ከማሰብ ፡ አውጥቶ ፡ በደመ ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ መነዳት ፡ የሚገፋፋ ፡ ዐዚም ፣ አፍዝ ፡ አደንግዝ ፡ ያለው ፡ ኾኖ ፡ ይቀጥላል ።

ታዲያ ፡ *"ኢትዮጵያም ፡ የለች! ፡ የኢትዮጵያም ፡ ሕዝብ ፡ የለ!"* ፡ ተብሎ ፡ በገሀድ ፡ በሚሰበክበት ፡ ኹኔታ ፥ የኛ ፡ የ*"ብሔር ፡ ብሔረሰቦች ፡ ታጋዮች"* ፡ *"ኦሮሚያ ፡ ሪፓብሊክ"*፣ *"ትግራይ ፡ ሪፓብሊክ"*፣ *"ኦጋዴኒያ ፡ ሪፓብሊክ"*፣ ወዘተርፈ ፡ ... ፡ እያሉ ፡ ቢያልሙ ፡ ለምን ፡ ይደንቀናል ፨ አስቀድሞ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ካልነበረበት ፡ ከባዶ ፡ *መነሣታቸው* ፡ አይደለምን ፨

እውኑ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አይደለም ። *"ነጻው ፡ ፕሬስ"* ፡ ሳት ፡ ብሎት ፥ የሕዝቡን ፡ ስሜት ፡ በጠየቀ ፡ ቍጥር ፥ ሕዝብ ፡ የሚጮኽላቸው ፡ አኹንም ፡ ኸሌም ፡—

- *"አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ነን ፤ ሕዝቦች ፡ አትበሉን!"*
- *"በዘር ፡ አትከፋፍሉን ፤ አንድ ፡ ሀገር ፡ ነን! ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ነን!"*
- *"ላልሠራነው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንገዛም ፨ "*
- *"የሕግ ፡ የበላይነት ፡ ይከበር!"*
- *"ደርግ ፡ በውንብድናው ፡ የዘረፈውን ፡ ርስታችንን ፡ ለባዕዳን ፡ አትቸብችቡብን! ፡ ርስታችን ፡ ይመለስልን!"*
- *"መንግሥት ፡ የለም!"*
- *"ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ አላግባብ ፡ ከወጣበት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የሥልጣን ፡ ሰገነት ፡ ይውረድ!*
- *ባዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እንተዳደር!"*

የሚሉ ፡ ቋሚዎች ፡ እምነቶቹን ፡ ነው ።

ወዲያው ፡ ከ*"ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ"* ፡ እስከ ፡ ተርታው ፡ የይዘቱ ፡ ሹመኛ ፥ ሹሉም ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ እየቀረቡ ፡— *"የኢትዮጵያ ፡ ሕዝቦች ፡ ..."*፣ *"የብሔር ፡ ብሔረሰቦች ፡ እኩልነት ፡ ..."*፣ ወዘተ. ፡ እያሉ ፥ ድምፁን ፡ በድምፃቸው ፡ ለማፈን ፡ ይረባረባሉ ፤ ከ*"ነጻው ፡ ፕሬስ"*ም ፡ ጥቂት ፡ የማይባሉ ፥ ይህኑ ፡ ያስተጋባሉ ።

ላለፉት ፡ 28 ፡ ዓመታት ፡ ሳያቋርጥ ፡ ይፈጸም ፡ የነበረው ፡ የ*"ዘር ፡ ማጽዳት"* ፡ ዘመቻና ፥ የኢትዮጵያ ፡ የገሮባ ፡ ዐጥንት ፡ የኾነችዪቱን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ የማጥቃት ፡ ዘመቻ ፥ ካንድ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ በተጠናከረ ፡ መልክና ፡ በገሀድ ፡ በየቦታው ፡ መካኼዱ ፥ የይዘቱንና ፡ የደጓሚዎቹን ፡ መቻኰል ፡ ያሳያል ። መቻኰሉ ፥ *"ኢትዮጵያ ፡ ናት ፡ ቀድማ ፡ የምትደረመሰው ፡ ወይስ ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፨ "* ፡ ለሚለው ፡ ጥያቄ ፥ በማያወላውል ፡ መንገድ ፡ የይዘቱ ፡ መደርመስ ፡ መቅደሙ ፡ ስላሠጋቸው ፡ እንጂ ፥ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ የላቸውም ። የሚፈለገው ፥ ለምእት ፡ ዓመት ፡ የተደከመለት ፡ ርኩስ ፡ የንጉልዮሽ ፡ ተልእኮ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፥ ይዘቱን ፡ ማሸጋገር ፡ እንጂ ፥ ኢትዮጵያን ፡ ማሸጋገር ፡ አይደለም ።

እውነቱን ፡ ለመናገር ፥ ኢትዮጵያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በመኾኗ ፥ ሕዝቧም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብን ፡ በመኾኑ ፡ እንጂ ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የወረደብንን ፡ መዐትና ፡ የተፈጸመብንን ፡ ግፍ ፡ ሌላ ፡ ሀገርም ፡ ኾነ ፡ ሕዝብ ፡ ይቋቋሙት ፡ አይመስለኝም ። የነባሩ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሥርዐት ፡ ርቱዕነትና ፡ ጽናት ፡ አኹንም ፡ ተረጋግጧል ። ገደልናት ፡ ያሏት ፡ ኢትዮጵያ ፥ እንኳን ፡ ሊገድሏት ፡ ጣፏንም ፡ አልነኳት ። በግንቦት ፡ እንደተቈረጠ ፡ ዕንጨት ፡ የጠነጠነ ፡ ይዘቱ ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አይደለችም ።

እውነት ፡ ነው ፥ ለ 100 ፡ ዓመታት ፡ ንጉልዮሽ ፡ ባደረሰብን ፡ መናጋት ፡ ምክንያት ፥ ትውልዱ ፡ የተደናገረው ፡ መስሏል ። እውነት ፡ ነው ፤ ያ ፡ ታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ ተኰሳቀሎ ፡ መገኘቱ ፥ የኸገብ ፡ ችኮሎችን ፡ የልብ ፡ ልብ ፡ ሳይሰጣቸው ፡ አልቀረም ። የታሪክ ፡ ጠላቶቹም ፡— *እንደ ፡ ዛሬ ፡ ተጋልጦልን ፡ ዳግመኛ ፡ አናገኘውምና ፥ አንዴ ፡ ለመቼውም ፡ እወደቀበት ፡ እናስቀረው* ፡ ብለው ፡ ተረባርበውበታል ።

ባንድ ፡ ወገን ፥ ማኅበራዊው ፡ ማወራኛ ፡ "ዕለቁ! ፡ ዕለቁ!" ፡ ይላል (9) ፤ በሌላው ፡ ወገን ፥ የ"መንግሥት" ፡ ማወራኛ ፡ ሳያቋርጥ ፡ "ሕዝቦች! ፡ ሕዝቦች!" ፡ "ብሔሮች! ፡ ብሔሮች!" ፡ "ክልል! ፡ ክልል!" ፡ "የተለያዩ! ፡ የተለያዩ!" ፡ ሲል ፡ ይመሻል ። "አንተም ፡ ተው ፤ አንተም ፡ ተው ፤ እንዲህም ፡ አይደል!" ፡ የሚለው ፡ ያስታራቂው ፡ የሽማግሌው ፡ ድምፅ ፡ ታፍኗል ፤ ራሱን ፡ "ነጻ ፡ ፕሬስ" ፡ ያለውም ፡ እንኳ ፡ ማስተጋባት ፡ የዠመረው ፡ ከጥቂት ፡ ወራት ፡ ወዲህ ፡ ነው ። ይህ ፡ አልበቃ ፡ ብሎ ፥ የ"ኀያላኑ" ፡ ማወራኛዎች ፥ በተለይ ፡ የነገሩ ፡ ዘቀሪዎች ፥ ያንኑ ፡ አፍራሽ ፡ የውሸት ፡ ስብከታቸውን ፡ አላንዳች ፡ ይሉኝታ ፡ ደጋግመው ፡ ይነዛሉ ፤ "የኛ ፡ ሰዎች" ፡ ያሏቸውንም ፡ በክብርና ፡ በማዕርግ ፡ ይክቧቸዋል ። ምን ፡ አለፋችኹ ፤ ቤንዚኑ ፡ ተርከፍክፎ ፥ ጥፋቱ ፡ ሊፈጸም ፡ ያንዲት ፡ ትንሽ ፡ የእሳት ፡ ብልጭታ ፡ ጕዳይ ፡ ኾኗል ።

ሀገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ናት ። ሀገር ፡ ረቂቅ ፡ ናት ፤ ሀገር ፡ ሥልጣኔ ፡ ናት ። ኢትዮጵያ ፡ በሥልጡንሕዝብና ፡ የታነጸች ፡ ሀገር ፡ ናት ፤ እንደ ፡ ብርጭቆ ፡ ወርውረው ፡ የሚሰብሯት ፡ ዕቃ ፡ አይደለችም ። ቀድሞም ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተረታችው ፡ ለበለጠ ፡ ሥልጣኔ ፣ ለምትበልጥ ፡ ጸጋ ፡ ነበር ፤ አኹንም ፥ የበለጠ ፡ ሥልጣኔን ፡ ይዘው ፡ ለሚመጡላት ፡ ትረታለች ። የስግብግብነትን ፡ ሞት ፣ የንጉልዮሽን ፡ ፍርሰት ፡ ይዞ ፡ የሚመጣባትን ፡ ኀይል ፡ ኹሉ ፡ ግን ፥ በረዥም ፡ ታሪኳ ፡ እንዳሳየችው ፥ ሕያውት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዛሬም ፡ ትቀብረዋለች ።

"ዩጎስላቪዜሽን" ፡ ከነስሙ ፡ ባዕድ ፥ በክፉ ፡ ምኞትነቱ ፡ ያለ ፥ ነገር ፡ ግን ፡ በገቢር ፡ መፈጸሚያ ፡ አካል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ ያልተገኘለት ፡ ፉርሽ ፡ ኾኖ ፡ ቀርቷል ። ኢትዮጵያ ፡ ዩጎስላቪያንም ፡ ሶቪዬት ፡ ኅብረትንም ፡ አይደለች ፤ የስድስት ፡ ሺሕ ፡ ዘመን ፡ ታሪክ ፡ ያላት ፡ ሥልጣኔ ፡ ናት ፤ ሕዝቧም ፡ ፈጽሞ ፡ የተዋሐደ ፡ አንድ ፡ ሀገራዊ ፡ ሐራ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ዐም ፡ ሐራ ፡ ኾኗል ።

"ይህ ፡ ሐራ ፡ ሕዝብ ፡ ጥንታዊነትን ፡ እንዴት ፡ አገኘ ፧ ይህችስ ፡ ሐራ ፡ ሀገር ፡ በየትኛው ፡ ሥልጣኔ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ ብትታነጽ ፡ ይኾን ፡ ሳትደፈር ፥ ጸንታ ፡ እዘመናችን ፡ የደረሰችው ፧ " ፡ የሚሏቸውን ፡ መሠረታውያን ፡ ጥያቄዎች ፡ አጥቂዎቻችን ፡ ደፍረው ፡ የማይመረምሯቸው ፥ ምናልባት ፥ መልሶቻቸው ፡ የጥቃታቸውን ፡ ፍሬ ፡ ቢስነት ፣ የምኞታቸውንም ፡ ርኵሰት ፡ ቀድመው ፡ ስለሚያረጋግጡባቸው ፡ ይኾናል ። አለዚያም ፥ ሰውን ፡ ባመለከ ፡ በስግብግብ ፡ ፍልስፍና ፡ ሞራ ፥ ዐይነ ፡ ልቡናቸው ፡ ተጋርዶ ፥ በሰው ፡ ሠራሽ ፡ ጥበባቸው ፡ ተመክተው ፥ ምላጭ ፡ በሚያስውጥ ፡ እልክ ፡ ጨክነው ፡ ጥቃታቸውን ፡ "እስከ ፡ መጨረሻው ፡ እንግፋበት" ፡ ብለውም ፡ ይኾናል ። በዚህ ፡ ፀረ ፡ ሥልጣኔ ፡ ድርጊታቸው ፡ በራሳቸው ፡ ህልውና ፡ መፍረዳቸውን ፡ ዐጥተውት ፡ ይኾን ፧ ወይስ ፡ "ክፉ ፡ ሥራ ፡ የለም ፤ መጥፎ ፡ ውጤት ፡ እንጂ!" ፡ ብለው ፥ ደግመው ፡ ደግመው ፡ መሞከራቸው ፡ ይኾን ፧

"ከባለቤቱ ፡ ያወቀ ፡ ቡዳ ፡ ነው"ና ፥ የማንንም ፡ ልቡና ፡ አንመረምርም ፥ ማንንም ፡ ደግሞ ፡ አንመክርም ፤ ኹሉም ፡ ለራሱ ፡ ይወቅበት ። እኛም ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ኀላፊነታችን ፡ በመዠመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ለሀገራችን ፡ ነውና ፥ በባላገርነት ፡ ለሀገር ፡ በአንድነት ፡ ቆመን ፥ በሥራና ፡ በመሥዋዕትነት ፡ ኢትዮጵያን ፡ መታደግ ፡ አለብን ። ኢትዮጵያ ፥ ከወደቀችበት ፥ በሥልጡንሕዝብናዋ ፡ ዳግመኛ ፡ ትነሣለች ።

(ይቀጥላል ።)

9 በማኅበራዊው ፡ ማወራኛ ፡ መርዘኛውን ፡ መልክት ፡ ከሚያስተላለፉና ፡ ከሚያዛምቱ ፡ ጠብ ፡ ቋጣሪዎች ፡ መኻከል ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ የውጭ ፡ ኀይሎች ፡ ቅጥረኞች ፥ አንዳንዶቹም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ "ለምድ" ፡ ያጠለቁ ፡ የውጭ ፡ ዜጋዎች ፡ ስለ ፡ መኾናቸው ፡ ብዙ ፡ ማስረጃዎች ፡ ተገኝተዋል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

# ክዋኔ

constitution | دستور

*[በዚህ ፡ ዐምድ ፥ ስለሕገ ፡ መንግሥት ፡ (ወይም ፡ ክዋኔ) ፡ ጕዳይ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሐሳቦችና ፡ አስተያየቶች ፡ ይቀርቡበታል ። ]*



## መልክት ፡ ለማወራኛዎች ።

ያንድ ፡ ሀገር ፡ ሕዝብ ፥ ርስ ፡ በርሱ ፡ የሚነጋገርበት ፡ አንድ ፡ **ሀገራዊ ፡ ቋንቋ ፡ ወይም ፡ ልሳን** ፡ አለው ፤ ሀገራዊ ፡ ቋንቋው ፡ ቢነካበት ፥ ሀገራዊ ፡ ህልውናው ፡ እንደተነካበት ፡ ይቈጠራል ።

ዛሬ ፡ ታሪካዊ ፡ ወቅት ፡ ላይ ፡ ደርሰናል ። የወደ ፡ ፊት ፡ ዕጣ ፡ ፈንታችን ፡ ወይ ፡ እሚሰምርበት ፥ አለዚያም ፡ ምናልባት ፡ ለዘለቄታው ፡ እሚበላሽበት ፡ ረድፍ ፡ ላይ ፡ እንገኛለንና ፤ እያንዳንዳችን ፡ ኀላፊነት ፡ አለብን ። በተለይ ፡ ደግሞ ፥ ማወራኛዎች ፡ (media) ፥ በሚለፍፉት ፡ ዜናና ፡ በሚነዙት ፡ አስተያየት ፡ የሚያለሙትን ፡ ያኽል ፡ ሊያጠፉም ፡ ይችላሉና ፥ ታላቅ ፡ ኀላፊነት ፡ አለባቸው ።

የማወራኛዎች ፡ ዋጋ ፡ በሚዘግቡት ፡ ወሬ ፥ በቃሉ ፡ ትኽክልነት ፥ በይዘቱ ፡ እውነተኛነት ፡ ይለ̇ካ̇ል ።

### 1 ፤ የቃል ፡ ትኽክልነት ።

የኢትዮጵያን ፡ ሕዝብ ፡ በመካድ ፥ *"የኢትዮጵያ ፡ ሕዝቦች"* ፡ እያሉ ፡ ትኽክለኛ ፡ ወሬን ፡ መዝገብ ፡ ይቻላልን ፦ ወይስ ፡ አለትርጕሙ ፥ *"ብሔር ፣ ብሔረሰቦች"* ፡ እያሉ ፦ ወይም ፡ ደግሞ ፡ አላግባብ ፡ *"ክልል"* ፡ እያሉ ፦

ቃላቱ ፡ አሉ ፥ የዋሉበት ፡ ጕዳይ ፡ ግን ፡ አይገ̇ለ̇ጥባቸውም ። አወራኚው ፡ ለጕዳዩ ፡ ትኽክለኛውን ፡ ቃል ፡ አግኝቶ ፡ ማዋል ፡ ይጠበቅበታል ። ካ 40 ፡ ዓመታት ፡ ወዲህ ፡ በተለይ ፡ የግዛት ፡ ግሳችን ፡ መዘበራረቅ ፡ አግኝቶታል ። የተዘበራረቀውን ፡ ለማስተካከል ፡ ከመዝገበ ፡ ቃላት ፡ የተሻለ ፡ መሣሪያ ፡ አይገኝም ።

በማናውቀው ፡ ቋንቋ ፡ ከመጻፋችን ፡ በፊት ፡ ቋንቋውን ፡ እንማራለን ፤ ከተማርነውም ፡ ወዲያ ፥ ስንጽፍበት ፥ መዝገበ ፡ ቃላትን ፡ ይዘን ፡ እያጣራን ፡ እንጂ ፥ *"በይመስለኛል"* ፡ አንጽፍም ። ዐማርኛ ፡ ሀገራዊ ፡ ቋንቋችን ፡ ነው ፤ አድገንበታል ፣ ተምረነዋልም ። ኾኖም ፥ በሀገራዊ ፡ ቋንቋችን ፡ ላይ ፡ የደረሰውን ፡ የትርጕም ፡ መፋለስና ፡ መዘበራረቅ ፡ ተገንዝበን ፥ ተፈላጊውን ፡ ጥንቃቄ ፡ እያደረግን ፡ ልንጽፍ ፡ ልንናገር ፡ ይገባል ።

ሀገራዊ ፡ መግባቢያችን ፡ ዐማርኛ ፥ ይህን ፡ ዕንቅፋት ፡ በተፈጥሮው ፡ የተሻገረው ፡ ቢኾንም ፥ በገቢር ፡ ገና ፡ ያልተሻገርነው ፡ አለንና ፥ ፈጥነን ፡ ልንሻገረው ፡ ይገባል ። ለዚህም ፡ ሌላ ፡ ዘዴ ፡ የለም ፤ በመዝገበ ፡ ቃላት ፡ እያጠራን ፡ ለመጻፍና ፡ ለመናገር ፡ እንትጋ ። *"ልግም ፥ እግዜር ፡ አይወድም"* ፡ ነውና ፥ ስንፍናንና ፡ ልግምን ፡ እናስወግድ ።

ከዚሁ ፡ ጋራ ፥ ማወራኛዎች ፡ የመጥፎ ፡ አርኣያ ፡ ማዛመቻ ፡ ሊኾኑ ፡ አይገ̇ባ̇ቸውም ። ለምሳሌ ፡ አንዳንድ ፡ ባለጊዜዎች ፡ ቀርበው ፡ በሚናገሩበት ፡ ጊዜ ፥ በራስ ፡ ካለመተማመን ፡ የተነሣ ፥ *"ተምረዋል"* ፡ የሚያሠኛቸው ፡ እየመሰላቸው ፥ የማያስፈልጉ ፡ የእንግሊዝኛ ፡ ቃላትን ፡ ካማርኛው ፡ እየዘነቁ ፡ መናገርን ፡ ይዘዋል ። ዕርማቱ ፡ ለሚያሻቸው ፡ ተናጋሪዎች ፥ ከንግግሩ ፡ በፊት ፥ ገለል ፡ አድርጋችኹ ፥ ነውር ፡ መኾኑን ፡ እያሳሰባችኹ ፡ ብትቃኟቸው ፡ ጥሩ ፡ ነው ።

### 2 ፤ የወሬ ፡ ታማኝነት ።

የማወራኛ ፡ ሥራ ፡ ትልቅ ፡ ዐቅምን ፡ የሚጠይቅ ፡ የድርጅት ፡ ሥራ ፡ ነውና ፥ ዐቅሙ ፡ የሌለው ፡ በድጎማ ፡ ሊሠራ ፡ ይገደዳል ።

***"የመንግሥት"* ፡ ማወራኛዎች** ፥ የማያጥጥ ፡ የገንዘብ ፡ ምንጭ ፡ ያለላቸውን ፡ ያኽል ፥ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ በሌለበት ፡ ኹኔታ ፡ የታማኝነት ፡ ችግር ፡ አለባቸው ።

*"የሚከፍል ፡ ያዛ̇ል"* ፤ በድጎማ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ **የግል ፡ ማወራኛ** ፡ ድርጅት ፡ ነጻ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አያስደፍርም ። በቅርቡ ፡ አንዳንድ ፡ ማስረጃዎችን ፡ አይተናል ።

ዛሬ ፡ ደግሞ ፥ በኢንተርኔት ፡ ዘመን ፥ **ማኅበራዊ ፡**


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

**ማወራኛ** ፡ (social media) ፡ የውርኝቱ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኾኗል ። ወጪው ፡ አነስተኛ ፡ ነው ፤ የሚያ ፡ ብቃትን ፣ የድርጅት ፡ ምላትን ፣ የአቋም ፡ ግዑዝነትን ፡ (neutrality) ፡ ስለማሟላቱ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ዋስትና ፡ የለም ።

በእነዚህ ፡ ሦስት ፡ ክፍሎች ፡ የሚመደበውን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የማወራኛ ፡ ዐቅም ፥ ከተያዘው ፡ ሀገርን ፡ የመታደግ ፡ ትግል ፡ ለማሳተፍ ፥ ከእያንዳንዱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ማወራኛ ፡ መገርመር ፡ ይኖርብናል ።

ከ"*መንግሥት*" ፡ ማወራኛው ፡ ብንገርምር ፥ ባለፉት ፡ 28 ፡ ዓመታት ፡ እንዳየነው ፥ ከዋና ፡ አዘጋጅ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ተላላኪው ፥ ባብዛኛው ፡ የሕ.ወ.ሐ.ት. ፡ አባላት ፡ በመኾናቸው ፥ አሳምኖ ፡ ማሳተፉ ፡ ከንቱ ፡ ይመስላል ። ካንድ ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፥ ቅጥሩ ፡ ወደ ፡ "*ብዝኀነት*" ፡ ያመራል ፡ ተብሎ ፡ ሲጠበቅ ፥ በተወሰኑ ፡ የሕ.ወ.ሐ.ት. ፡ አባላት ፡ ምትክ ፡ የዐቅዳዊ ፡ ሽሪኩ ፡ የኦ.ዴ.ፓ. ፡ አባላት ፡ ተተክተዋል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ከያግጣጫው ፡ ይሰማል ፤ ሌላ ፡ የሚያጓጓ ፡ ነገር ፡ የለውም ። ባኹኑ ፡ ኹኔታ ፥ በ"*መንግሥት*" ፡ ማወራኛ ፡ በኩል ፥ በነጻነት ፡ ሊሠራ ፡ የሚችል ፡ አወራኚ ፡ አይጠበቅም ።

በግል ፡ ማወራኛ ፡ ድርጅቶች ፡ በኩል ፡ ይልቅ ፡ የተስፋ ፡ ጭላንጭል ፡ አለ ። በ"*መንግሥት*" ፡ ማወራኛ ፡ አንጻር ፥ እላይ ፡ የጠቄምነው ፡ ድጐማ ፡ ካልገታው ፡ በቀር ፥ የግሉ ፡ ማወራኛ ፡ የተሻለ ፡ ነጻነት ፡ አለውና ፥ ገበያውን ፡ (አንባቢውን ፣ አድማጪውንና ፡ ተመልካቹን) ፡ ለመቈጣጠር ፡ አይቸግረውም ። የገበያው ፡ ዐቅም ፡ ከደንሚ ፡ ነጻ ፡ ያወጣዋል ፡ የሚል ፡ ተስፋ ፡ አለ ።

በተመሳሳይ ፥ የማኅበራዊ ፡ ማወራኛ ፡ አባላት ፥ በየግላቸው ፡ ነጻ ፡ የመኾን ፡ ወይ ፡ ያለመኾን ፥ ባለሚያ ፡ የመኾን ፡ ወይ ፡ ያለመኾን ፡ ችግር ፡ ቢገድባቸው ፡ እንጂ ፥ እውነተኛና ፡ ታማኝ ፡ ወሬን ፡ በተስተካከለ ፡ አገላለጽ ፡ ከመልፈፍ ፡ የሚከለክላቸው ፡ የለም ። ካኹኑ ፡ ያቈጠቈጡት ፡ እሳት ፡ የላሱ ፡ ዜነኛዎች ፡ ይህን ፡ ተስፋ ፡ አለምልመውታል ።

እስካኹን ፡ የተነገረው ፡ እንደተያዘ ፡ ኾኖ ፥ ለኹሉም ፡ የማወራኛ ፡ ክፍሎች ፡ የሚከተለውን ፡ መልክት ፡ በትሕትና ፡ እናስተላልፋለን ። መልክቱ ፡ ዐዲስ ፡ አይደለም ፤ በማወራኛ ፡ ሚያ ፡ የሠለጠነ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ያውቀዋል ። ነገር ፡ ግን ፥ በዘመናችን ፡ በብዙ ፡ ረገድ ፡ በገቢር ፡ ስላልተከበረ ፥ ማስታወሱ ፡ ይጠቅማል ፦

ሀ) **"*ከሺሕ ፡ ወርዋሪ ፥ አንድ ፡ መዐት ፡ አውሪ*"** ፤
የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በዚህች ፡ ሰዓት ፡ በሀገሩ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ እግዚአናውን ፡ ለማስከበር ፡ በያግጣጫው ፡ ተነሣሥቷል ። በሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ዐዲስ ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ ለመሥራትና ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ መንግሥቱን ፡ ለመመሥረት ፡ ይቻለው ፡ ዘንድ ፥ የማወራኛ ፡ ድርጅቶች ፥ በለፈፋዎቻቸው ፥ ቃላትን ፡ መርጠው ፣ ዜናን ፡ አጣርተው ፡ ያቅርቡለት ። ቢደፍሩ ፡ ደግሞ ፥ የትግሉን ፡ ዜና ፡ ይዘግቡለት ፤ እንደበትም ፡ ይኹኑት ። እስካኹን ፡ ይህኑ ፡ ሲፈጽሙ ፡ የቈዩትን ፡ እናመሰግናለን ።

ለ) **"*ሳያስረግጡ ፡ ወሬ ፤ ሳይገድሉ ፡ ጐፈሬ*"** ፤
ከውጭም ፡ ከውስጥም ፡ የሚተላለፉላቸውን ፡ በተለይ ፡ የአኃዝ ፡ መረጃዎች ፡ በሚገባ ፡ ሳይፈትሹ ፡ እንዳለ ፡ በማወራኘት ፡ የአጥፊ ፡ "*ፕሮፐጋንዳ*" ፡ መሣሪያ ፡ አይኹኑ ። ቢችሉ ፥ ራሳቸው ፡ የመረጃው ፡ ምንጮች ፡ ይኹኑ ፤ እቦታው ፡ ድረስ ፡ እየኼዱ ፡ መረጃውን ፡ አጠናቅረው ፡ ለሕዝብ ፡ ያቅርቡት ። ካሉባልታ ፡ ይልቅ ፡ ርግጠኛውን ፡ ወሬ ፣ ውለኛውን ፡ መረጃ ፡ ያወራኙ ።

ገ) **"*እውነቱን ፡ ተናግሮ ፡ እመሸበት ፡ ያድሯል*"** ፤
ሰብአዊ ፡ መብት ፡ ሲጣስ ፥ የሀገር ፡ ደኅንነት ፡ ላደጋ ፡ ሲጋለጥ ፥ ውሸት ፡ ሲሰበክ ፥ ሙስና ፡ ሲፈጸም ፥ ወዘተ. ፥ አይተው ፡ እንዳላዩ ፣ ሰምተው ፡ እንዳልሰሙ ፡ አይኹኑ ። ደኅና ፡ ቀን ፡ እንዲወጣ ፡ እንደ ፡ እስክንድር ፡ ነጋ ፡ ይጋፈጡ ።

ሕዝብም ፥ የሚያሞኙትን ፡ ሳይኾን ፥ ለእውነት ፡ ብለው ፡ ውድ ፡ ዋጋን ፡ የሚከፍሉለትን ፡ ወገኖቹ ፡ የኾኑትን ፡ ዜነኛዎች ፡ ከመደገፍና ፡ ከመጠበቅ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አይልም ። እስካኹን ፡ የቸገረው ፥ እውነተኛውን ፡ ከግብዙ ፡ (ወይም ፡ ከግዙው) ፡ መለየቱ ፡ ነበር ፤ ነገሩ ፡ እየጋመ ፡ ሲኼድ ፥ እውነተኛውና ፡ ሌላው ፡ እያደር ፡ ይለያል ።

አደጋ ፡ ውስጥ ፡ ኾነው ፥ እነዚህን ፡ የማወራኛ ፡ ግዴታዎች ፡ ሳያጓድሉና ፡ ሳያዛንፉ ፡ ጠንቅቀው ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ኀብረተሰባቸውን ፡ በታማኝነትና ፡ በቅንነት ፡ ያገለገሉትን ፥ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ውድ ፡ የሕይወት ፣ የአካል ፣ የሀብት ፣ የንብረት ፡ ዋጋን ፡ የከፈሉልንን ፡ ክቡራት ፡ ኢትዮጵያውያትና ፡ ክቡራን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ዜነኛዎች ፡ ኹሉ ፥ እጅ ፡ እየነሣን ፥


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ለዝግና ፡ የሚገባውን ፡ ሰላምታ ፡ በሀገር ፡ ፍቅር ፡ እንሰጣቸዋለን ። ዋጋቸውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ አምላክ ፡ ይክፈልልን ❖

## ከመቃብር ፡ በላይ ።

### አንቺ ፡ ነሽ ፡ ሌላ ፥

### የኔ ፡ ወለላ ።

መኰንን ፡ ተክለ ፡ አረጋዊ [10] ።

ልለይሽ ፡ ተሳነኝ ፤
ዐይኔን ፡ ነው ፡ የጋረደኝ ፥
ወይስ ፡ አንቺው ፡ ነሽ ፡ የተለወጥሺብኝ ፥
ጥርስሽ ፡ ተቸምችሞ ፤
አፍንጫሽ ፡ ተጣሞ ።
ዦሮሽ ፡ ተተልትሎ ፤
እጅሽ ፡ ተጐንድሎ ።
ጉንጮችሽ ፡ ጐድጉደው ፤
አጥንቶችሽ ፡ ገጠው ።
ከንፈርሽ ፡ ተልጦ ፤
ዐይንሽ ፡ ተበልጥጦ ።
አካልሽ ፡ ሞስሙሶ ፤
ወዘናሽም ፡ ጠፍቶ ፤ ለዛሽ ፡ ተደምስሶ ።
አንቺ ፡ ነሽ ፥ ሌላ ፥
የኔ ፡ ወለላ ።
ጨርቅሽ ፡ በደም ፡ ታጥቦ ፥ መርገም ፡ በቀሚስሽ ፥
እንባ ፡ በደረትሽ ፥ ልቅሶ ፡ በልሳንሽ ፥
ሙሾ ፡ ባደባባይ ፥ ባደግንበት ፡ ግቢሽ ፤
ተገማምጦ ፡ አካልሽ ፥ በቀኅስል ፡ ነፍርቀሽ ፤
ሥቃይሽ ፡ በርትቶ ፥ ጠንክሮ ፡ ዋይታሽ ፤
መላው ፡ አቈብቍቦ ፥ ጓጉቶ ፡ ለጥፋትሽ ፤
"ማለፊያ ፡ ኾነልን ፤ ይበላት!" ፡ እያለሽ ።
ልጇን ፡ የምትበላ ፡ ድመት ፡ አድርገውሽ ፥
ኹሉን ፡ መተሩና ፡ ባዶሽን ፡ አስቀሩሽ ፤
ባለጌ ፡ ደፈረሽ ፥ ጐረቤትም ፡ ጠላሽ ።
አንቺ ፡ ነሽ ፡ ሌላ ፥
የኔ ፡ ወለላ ።
የአብዮት ፡ ዕልቂት ፥ ዐሳር ፡ በየቀኑ ፤
በድን ፡ በከተማሽ ፥ ዐፅም ፡ በየደኑ ፤
ኹሉም ፡ ዐለቁብሽ ፤ ኧረ! ፡ እነማን ፡ ዳኑ ፥

10 በ 1970 ዎቹ ፡ በሱዳን ፡ በረሐ ፡ በጠላት ፡ የተገደሉ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የነጻነት ፡ ታጋይ ።

# ዜና ፡ ስሌት ።

computing news | nouvelles d'informatique | اخبار العقل

## 5G ፡ ወይም ፡ 5 ኛ ፡ ትውልድ ፡ እና ፡ እኹል-ገብ ፡ ኢንተርኔት ።

**የአንከርት ፡ ስልክ ፡ ኪነት** ፡ (mobile phone technology) ፡ በሠላሳ ፡ ዓመታት ፡ ታሪኩ ፥ ዘንድሮ ፡ 5 ኛ ፡ ትውልዱን ፡ ወልዷል ። ወላጅ ፡ ከልጆቹ ፡ የሚለየውን ፡ ያኽል ፡ ይህ ፡ 5 ኛው ፡ የኪነት ፡ ትውልድ ፡ ከቀደሙት ፡ 4G ፡ እና ፡ 3G ፡ … ፡ ይለያል ።

5G ፡ ከሚያመጣቸው ፡ መሻሻሎች ፡ ውስጥ ፦

- ፍጥነት ፤ ሽቦ-አልቦ ፡ (wireless) ፡ የሚተላለፈው ፡ የስልክ ፡ መልክት ፡ መጠን ፡ እስከ ፡ 20 ፡ Gbps ፡ (Giga bits per second ፥ ወይም ፡ 20 ፡ ቢልዮን ፡ ኹለትዮ ፡ ንምራ ፡ በካልኢት) ፡ ይደርሳል ፡ (በ 4G ፡ ከ 1Gbps ፡ አያልፍም) ።
- የሥርጭት ፡ ዝግየታው ፡ (latency ው) ፡ ካ 1 ፡ ms ፡ (milliseconds ፡ ወይም ፡ ካ 1 ፡ ካልኢት-ሺኛ) ፡ አይበልጥም ።
- የበለጠ ፡ ፈሰሳ ፡ (bandwidth) ፡ እና ፡ የተሻሻለ ፡ የቀጠጥና ፡ ኪነት ፡ (antenna technology) ፡ ስለሚኖር ፥ በ 5G ፡ የሚዘዋወረው ፡ ልቅም ፡ (data) ፡ መጠን ፡ የላቀ ፡ ይኾናል ።
- 5G ፡ የቀለጠፈ ፡ የመርበብት ፡ አስተዳደር ፡ (network management) ፡ ስለሚኖረውም ፥ ከእውነተኛው ፡ 5G ፡ መርበብት ፡ ጋራ ፡ ሌሎች ፡ የመርበብት ፡ ክፍለቶችን ፡ ለመፍጠርና ፥ ለእያንዳንዱ ፡ የተለየ ፡ አስተዳደር ፡ ለመመደብ ፡ ያስችላል ።

ሽቦ-አልቦ ፡ መርበብት ፡ የሚዘረጋው ፡ በማቈሪያ ፡ (cell) ፡ ማማ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ሥርጭቱ ፡ ከማቈሪያ ፡ እማቈሪያ ፡ በሚቀባበል ፡ የምዕዛር ፡ (radio) ፡ ሞገድ ፡ (wave) ፡ ይከናወናል ። ኾኖም ፥ ለ 4G ፡ ረዥም ፡ የማቈሪያ ፡ ማማ ፡ ሩቅ ፡ ለሩቅ ፡ ያስፈለገውን ፡ ያኽል ፥ ለ 5G ፡ ደግሞ ፡ ቅርብ ፡ ለቅርብ ፡ የተተከሉ ፡ አነስተኛዎች ፡ ማማዎች ፡ ይበቁታል ፥ ምክንያቱም ፥ እጅግ ፡ ፈጣን ፡ ሥርጭት ፡ እንዲኖረው ፡ ብዙ ፡ ርቀት ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

በማይዘልቅ ፡ በከፍተኛ ፡ የምዕዛር ፡ ብዛት ፡ (frequency) ፡ ይሠራል ። ይህ ፡ ኹኔታ ፡ ግን ፡ 5G ን ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ የአካልና ፡ የአየር ፡ ጠባይ ፡ መሰናክሎች ፡ ይዳርገዋል ።

ባኹኑ ፡ ሰዓት ፥ 5G ፡ ዐሥር ፡ እማይሞሉ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ባነስተኛ ፡ ደረጃ ፡ ተዘርግቷል ፤ በመላ ፡ ዓለም ፡ እስኪዘረጋ ፡ 10 ፡ ዓመት ፡ ይፈጃል ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ።

5G ፥ በማሠራጫ ፡ ፈጣንነቱ ፣ በፈሰሳ ፡ ብልጫውና ፡ በመለስተኛ ፡ ዝግየታው ፡ ላዳዲስ ፡ ኪነቶች ፡ አዋዋል ፡ ይመቻል ። ከነዚህ ፡ ዐዳዲስ ፡ ኪነቶች ፡ ውስጥ ፥ ነጂ-አልቦ ፡ መጓጓዣ ፣ በ"ሮቦት" ፡ የታገዘ ፡ የርቀት ፡ ሥራ ፡ ይገኙበታል ።

በተለይ ፡ ደግሞ ፥ ባኹኑ ፡ ሰዓት ፡ እጅግ ፡ ለሚስፋፋው ፡ *"እ ኸል-ገብ ፡ መርበብት"* ፡ ወይም ፡ *"Internet of Things"* ፡ በር ፡ ይከፍትለታል ። እንደ ፡ ልብስ ፡ ማጠቢያ ፣ ማቀዝቀዣ ፣ መኪና ፣ ስልክ ፣ የቤት ፡ ማሞቂያ ፣ ... ፡ ያሉ ፡ መሣሪያዎች ፥ እንደ ፡ ሰዉ ፡ ኹሉ ፥ የ IP ([11]) ፡ አድራሻ ፡ ኖሯቸው ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ኾነ ፡ ካንዳች ፡ ማእከል ፡ ጋራ ፡ በ 5G ፡ መርበብት ፡ አማካይነት ፥ *"ደከመኝ ፤ ሰለቸኝ"* ፡ ሳይሉ ፥ መረጃን ፡ በማቀበል ፣ መቀባበልና ፡ ለማቀባበል ፡ አካባቢውን ፥ ለደኅናም ፡ ኾነ ፡ ለሌላ ፥ መቈጣጠር ፡ ያስችላሉ ።

እውነት ፡ ለመናገር ፥ 5G ፡ የሚያስችለው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ተዘርዝሮ ፡ የሚታወቅ ፡ አይደለም ። ገና ፡ ማንም ፡ ዛሬ ፡ ያላሰባቸው ፡ ብዙ ፡ አዋዋሎች ፡ ስለሚኖሩት ፥ በተለይ ፡ ኀያላን ፡ መንግሥታት ፡ ለየብቻቸው ፡ ጠቅልሎ ፡ የመያዝ ፡ ፍላጎትን ፡ ካኹኑ ፡ ማሳየት ፡ ዠምረዋል ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ ካልተጠነቀቀ ፥ ምናልባት ፡ ሳያውቀው ፡ ነጻነቱንም ፡ በመርበብት ፡ ሊነጠቅ ፡ ይችላልና ፥ ዘው ፡ ዘው ፡ ከማለቱ ፡ በፊት ፡ ለነጻነቱ ፡ በቂ ፡ ዋስትና ፡ መኖሩን ፡ አስቀድሞ ፡ ማረጋገጥ ፡ ይገባዋል ፨

---

11 IP ፡ ወይም ፡ Internet Protocol ፤ ከምንጩ ፡ እስከ ፡ መድረሻው ፡ የመረጃን ፡ የኢንተርኔት ፡ ፍናዌ ፡ ወይም ፡ አላላክ ፡ ዝርዝር ፡ የሚቈጣጠር ፡ ሥርዐት ።

## የ"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ መርበቢያ ፡ awdeqelem.net ፡ ከነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ አላግባብ ፡ ታግዷል ።

"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ የተባለው ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መግበር ፡ መርበቢያ ፡ awdeqelem.net ፡ ከነሐሴ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ መታገዱን ፡ ባለቤቱ ፡ አቶ ፡ ወሴ ፡ ነጋ ፡ ገልጸውልናል ።

የታገደበትን ፡ ምክንያት ፡ ሲያብራሩ ፥ የመርበቢያው ፡ አከራይ ፥ ፈረንሳዊው ፡ ድርጅት ፡ Groupe Magic Online ፡ ባሳየው ፡ ያገልግሎት ፡ ጕድለት ፡ ምክንያት ፥ ለሚቀጥለው ፡ ዓመት ፡ ደንበኛነታቸውን ፡ እንደማይቀጥሉ ፡ አሳውቀውት ፥ ከሌላ ፡ አከራይ ፡ ጋራ ፡ በሚነጋገሩበት ፡ ወቅት ፥ የኪራዩ ፡ ዘመን ፡ ከማለቁ ፡ 2 ፡ ወራት ፡ በፊት ፥ Groupe Magic Online ፡ (https://magic.fr) ፡ የመጪውን ፡ ዓመት ፡ ኪራይ ፡ አለፈቃዳቸው ፡ ከባንክ ፡ ሒሳባቸው ፡ ወስዶ ፥ ገንዘቡንም ፡ መልስ ፡ እንዳይባል ፥ መርበቢያቸውን ፡ ሳልጠየቁት ፡ ለሌላ ፡ አከራይ ፡ አኹንም ፡ አለፈቃዳቸው ፡ በማዛወሩ ፡ በተፈጠረ ፡ ውዝግብ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

አኹን ፥ ጕዳዩ ፡ የመርበቢያዎችን ፡ ስም ፡ ምዝገባና ፡ ጠቅላላ ፡ ጕዳይ ፡ በበላይነት ፡ ለሚመለከተው ፡ ለ ICANN ፡ ስለ ፡ ቀረበ ፥ ከምርመራ ፡ በኋላ ፡ የሚሰጠውን ፡ ውሳኔ ፡ እንደሚጠባበቁ ፡ ገልጸውልናል ።

Groupe Magic Online ፡ የተባለው ፡ ፈረንሳዊ ፡ ድርጅት ፡ የኢ.ሀ.ሥ.አ.ንም ፡ መርበቢያ ፡ (slttunhzb.net) ፡ ለብዙ ፡ ወራት ፡ ማወኩ ፡ ይታወሳል ። ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጕዳዩን ፡ ለፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ የውጭ ፡ ጕዳይ ፡ ምጋቤ ፡ ካቀረበው ፡ በኋላ ፥ መርበቢያውን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አከራይ ፡ ድርጅት ፡ ማዛወሩ ፡ ይታወሳል ።

"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ የተባለውን ፡ መግበር ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ስለሚሠራበትና ፡ ያገልግሎቱንም ፡ ጥቅም ፡ ለሌሎች ፡ ለማስተዋወቅ ፡ ስለ ፡ ወደደ ፥ በባለቤቱ ፡ በአቶ ፡ ወሴ ፡ ነጋ ፡ ፈቃድ ፥ መግበሩን ፡ ማንኛው ፡ ሰው ፡ ከመርበቢያችን ፡ ከ slttunhzb.net ፡

በነጻ ፡ ሊቀዳው ፡ እንደሚችል ፡ እናስታውቃለን ።

የጕዳዩን ፡ አካኼድ ፡ ተከታትለን ፡ በመጨረሻው ፡ ዕትማችን ፡ እንዘግባለን ❖

## ብሔረ ፡ ጥበብ ።

universe of science | univers de la science | عالم العلوم

## ምድርና ፡ ኀዋ ።

### ክፍል ፡ 3 ፤ ከርሠ ፡ ምድር ።

ምድራችን ፥ ከገጿ ፡ እስከ ፡ ውስጣውስጧ ፥ በሦስት ፡ የሚከፈሉ ፥ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክና ፡ ይዘት ፤ ግለትና ፡ ፍሰት ፤ ስፋትና ፡ ጥልቀት ፡ ባላቸው ፡ የመደቦች ፡ ንብብራት ፡ ተሠርታለች ።

የመጀመሪያው ፡ መደብ ፡ **የብሳዊ ፡ ቅርፊት** ፡ **(continental crust | croûte continentale)** ፡ የተባለው ፥ ከምድር ፡ ገጽ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ከ 20 ፡ እስከ ፡ 70 ፡ ኪሎሜትር ፡ ጥልቀት ፡ አለው ። ሰባቱን ፡ የብሶች ፡—

- **አፍሪቃ** ፡ (Africa | Afrique) ፤
- **እስያ** ፡ (Asia | Asie) ፤
- **አውሮፓ** ፡ (Europe) ፤
- **ሰሜን ፡ አሜሪካ** ፡ (North America | Amérique du Nord) ፤
- **ደቡብ ፡ አሜሪካ** ፡ (South America | Amérique du Sud) ፤
- **ዖቅያንያ** ፡ (Oceania | Océanie) ፤
- **ደቡባዊ ፡ ዋልታ** ፡ (Antarctica | Antarctique) ፤

ዐምስቱንም ፡ ውቅያኖሶች ፡—

- **አትላንቲክ ፡ ውቅያኖስ** ፡ (Atlantic | Atlantique) ፤
- **ሰላማዊ ፡ ውቅያኖስ** ፡ (Pacific | Pacifique) ፤
- **የህንድ ፡ ውቅያኖስ** ፡ (Indian | Indien) ፤
- **ሰሜናዊ ፡ ውቅያኖስ** ፡ (Arctic | Arctique) ፤
- **ደቡባዊ ፡ ውቅያኖስ** ፡ (Southern | du Sud) ፤

በርሱ ፡ ላይ ፡ ተነጥፈው ፡ እናያቸዋለን ። የብሳዊው ፡ ቅርፊት ፡ ባብዛኛው ፡ ጥቁር ፡ ድንጋይ ፡ ነው ፤ ውቅያኖሳዊው ፡ ቅርፊት ፡ ደግሞ ፡ እስከ ፡ 8 ፡ ኪሎሜትር ፡ ውፍረት ፡ ያለው ፡ የቦረቦጭ ፡ ድንጋይ ፡ ዐይነት ፡ ይገኝበታል ።

ኹለተኛው ፡ የሽፋን ፡ መደብ ፡ እስከ ፡ 2900 ፡ ኪሎሜትር ፡ ድንዳኔ ፡ ያለው ፥ ገና ፡ ፈጽሞ ፡ ያልጸና ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ የአለት ፡ **ልባስ** ፡ (mantle | manteau) ፡ ነው ። ይህም ፡ በመኾኑ ፥ **ፍልቅ ፡ ሸለቆ** ፡ (Rift Valley | vallée du Rift) ፡ በያመቱ ፡ በ 3 ፡ ሳንቲሜትር ፡ መሠንጠቁን ፡ ይቀጥላል ።

በሦስተኛውና ፡ በመጨረሻው ፡ መደብ ፥ በዚህ ፡ በአለት ፡ ልባስ ፡ የተሸፈነው ፥ ውፍረቱ ፡ 2500 ፡ ኪሎሜትር ፡ የሚኾን ፡ የምድር ፡ **አስኳል** ፡ (core | noyau) ፡ ይገኛል ። ይህ ፡ የምድር ፡ አስኳል ፡ ኹለት ፡ ክፍሎች ፡ አሉት ። በስተላይ ፡ ያለው ፡ **አፍአዊ ፡ አስኳል** ፡ (outer core | noyau externe) ፡ የቀለጠ ፡ የብረትና ፡ የኒኬል ፡ ባሕር ፡ ነው ። በውስጡ ፡ ኹለተኛው ፡ ክፍል ፡ **ውሳጣዊ ፡ አስኳል** ፡ (inner core | noyau interne) ፡ በ 6000 ፡ ደረጃ ፡ "ሴንቲግሬድ" ፡ የተንደረከከ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ያልቀለጠ ፡ የብረት ፡ አሎሎ ፡ ተወሽቆ ፡ ይገኝበታል ። ከምድር ፡ ስሕበት ፡ የተነሣ ፥ ከኹሉም ፡ አግጣጫ ፡ ኀይለኛ ፡ ተጽዕኖ ፡ ስለሚያርፍበት ፥ በዚህ ፡ ሙቀትም ፡ እንኳ ፡ ብረቱ ፡ ሳይቀልጥ ፡ በጥጥርነቱ ፡ ይኖራል ❖

## ከታሪክ ፡ አንዱ ፡ ዐምድ ።

history column | colonne d'histoire | خانة التاريخ

### የአኵስም ፡ ሐውልትንና ፡ ቅርሳቅርሶችን ፡ የማስመለስ ፡ ውሳኔ ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፥
ዐዲስ ፡ አበባ ፥ ግንቦት ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1960 ፡ ዓ.ም. ።

[የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ተዘርፈው ፡ የተወሰዱት ፡ የአኵስም ፡ ሐውልትና ፡ ቅርሳቅርሶች ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲመለሱ ፡ ማስገደጃ ፡ ውሳኔውን ፡ ልክ ፡ የዛሬ ፡ 51 ፡ ዓመት ÷ ቀጥሎ ፡ በተመለከተው ፡ ሰነድ ÷ ሕግ ፡ አድርጎ ፡ አጽድቆታል ። ሥርዐት ፡ በሥርዐት ፡ እንጂ ፡ በውንብድና ፡ አይለወጥ ፤ ወይ ፡ አይሻር ፤ ወይም ፡ ደግሞ ፡ አይሻሻልም ፤ በሕግነቱ ፡ ሳይለወጥ ፤ ሳይሻር ፤ ሳይሻሻል ፡ እንደጸና ፡ አኹንም ፡ ይገኛል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

የውሳኔው ፡ የመጨረሻ ፡ ቃል ፡–

*የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፥ ኢጣሊያ ፡ በውል ፡ ሊገድ ፡ የሚገባትና ፡ የምታከብረውም ፡ ቋንቋ ፡ ጭንቅ ፡ ወይም ፡ የጥቅም ፡ ግዴታ ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ አምኖና ፡ የአባሎቹን ፡ አስተያየት ፡ ኹሉ ፡ በዚሁ ፡ እውነትና ፡ በሐውልቱ ፡ መመለስ ፡ ብልጫ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ አስተባብሮ ፥*

*ሀ ፤ በዜጋ ፡ መሸጋገር ፡ ሊገድ ፥ በመጨዎቹ ፡ ላይ ፡ በር ፡ እስከ ፡ መዝጋት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ ነዋሪዎቹንም ፡ ፈጽሞ ፡ እስከ ፡ ማስወጣት ፥ በጥሬት ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የንግድ ፡ መከዋወጥን ፡ እስከ ፡ ማቆምና ፥ መደምደሚያውን ፥ በዲፕሎማሲ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ግንኙነትን ፡ ፈጽሞ ፡ እስከ ፡ ማቋረጥ ፡ ድረስ ፡ ተረማማጅ ፡ በሚኾን ፡ የጭቈና ፡ ዘዴ ፡ በግልጽና ፡ በማይቋረጥ ፡ አደራረግ ፡ በመጠቀም ፥ የአኩስም ፡ ሐውልትና ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የሚጠቀሱት ፡ ታሪካውያን ፡ መታሰቢያዎች ፡ በስድስት ፡ ወሮች ፡ ውስጥ ፡ ወደየነበሩበት ፡ ስፍራ ፡ እንዲመለሱ ፡ እንዲያደርግ ፡ ያስፈልጋል ፡ ሲል ፡ ወስኖ ፤*

***ለ ፤ ይህ ፡ ሐውልትና ፡ የሚጠቀሱት ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ ኹሉ ፡ እስከተመለሱና ፥ ከነርሱም ፡ መመለስ ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ የሚመለሰው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክብር ፡ ተሠይሞ ፥ የኹለቱ ፡ ሀገሮች ፡ ወዳጅነት ፡ በንጹሕ ፡ መንፈስ ፡ ላይ ፡ ከመመሥረቱ ፡ በፊት ፥ የዳበረ ፡ ፍቅር ፡ መገለጫ ፡ የኾነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጒብኝት ፡ ክብር ፡ ቀድሞ ፡ እንዳይሰጣት ፥ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ አገር ፡ መኼድ ፡ እስከዚህ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ እንዲዘገይ ፡ ያሳስባል ። "***

ይላል ።

ውሳኔው ፡ በወቅቱ ፡ በምክር ፡ ቤቱ ፡ በሙሉ ፡ ድምፅ ፡ ጸድቆ ፡ ቢያልፍም ፥ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ክልክሉን ፡ ተሯምደው ፥ ኢጣሊያን ፡ በይፋ ፡ ጐበኙ ። ጒብኝቱ ፡ የታቀደው ፡ ለመስከረም ፡ መጨረሻ ፡ 1963 ፡ ዓ.ም. ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፥ ከመስከረም ፡ 27 ፡ እስከ ፡ መስከረም ፡ 29 ፡ 1963 ፡ ዓ.ም. ፡ በኢጣሊያ ፡ ሰሜናዊትና ፡ ጥንታዊት ፡ ከተማ ፡ በጄኖዋ ፡ አካባቢ ፡ ከባድ ፡ ዝናብ ፡ ዘንቦ ፥ 44 ፡ ሰዎች ፡ በጐርፍ ፡ አደጋ ፡ ሲሞቱ ፣ ከ 2000 ፡ በላይ ፡ ነዋሪዎች ፡ ተፈናቅለው ፥ ዐያሌ ፡ ንብረትና ፡ ቅርሳቅርስ ፡ ወደሙ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ጒብኝቱ ፡ ተሯዝሞ ፥ ለጥቅምት ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1963 ፡ ዓ.ም. ፡ ተዛወረ ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ኢጣሊያ ፡ እንደ ፡ ደረሱም ፥ በማግሥቱ ፡ አንድ ፥ ጦሱን ፡ ያልዘነጋ ፡ የኢጣሊያ ፡ መዜንው ፥ ጒብኝታቸውን ፡ "ገፊ" ፡ ሲል ፡ "*la carogna*" ፡ ብሎ ፡ መጻፉን ፡ እቦታው ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ መስክረዋል ።

ዘንድሮ ፡ ደግሞ ፡ የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ ይዘት ፡ በዶክተር ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ መሪነት ፥ ይህኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሕጋዊ ፡ ውሳኔ ፡ ከመጣስም ፡ ዐልፎ ፥ ኢጣሊያ ፥ በዘረፈቻቸውና ፡ እስካኹን ፡ ባልመለሰቻቸው ፡ ቅርሳቅርስ ፡ ላይ ፥ የቀሩትን ፡ የአኩስም ፡ ከተማን ፡ ሐውልቶችና ፡ ቅርሳቅርስ ፡ "*እንድትከባከብ*" ፡ መዋዋሉን ፡ አስታወቀን ። አኹንም ፡ ሕግ ፡ ተጣሰ ፤ ሕግን ፡ የጣሰ ፡ ኹሉ ፡ በሕግ ፡ መጠየቁ ፡ አይቀርም ። ጒዳዩ ፡ የደም ፡ ዋጋ ፡ አለበትና ፥ የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ ኀላፊዎች ፡ ከዶክተር ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ አንሥቶ ፡ ይህን ፡ ልብ ፡ ብለው ፥ በፍጥነት ፡ ከስሕተታቸው ፡ እንዲመለሱ ፡ እናሳስባለን ።

የውሳኔውን ፡ ሙሉ ፡ ቃል ፡ እንሆ ። ]

---

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፥**

**ዐዲስ ፡ አበባ ፥**

**ግንቦት ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1960 ፡ ዓ.ም. ።**

**ልዩ ፡ ኮሚቴው ፤** ካስረዺው ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ክቡር ፡ አቶ ፡ ከተማ ፡ ይፍሩ ፡ የቀረቡለትን ፡ የፓሪስን ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ ግልባጭ ፥ ይህኑ ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የካቲት ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1943 ፡ ዓ.ም. ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥትና ፡ የኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ የተፈራረሙበትን ፡ ስምምነት ፡ ቅጂ ፥ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ታኅሣሥ ፡ 22 ፡ ቀን ፡ 1943 ፡ ዓ.ም. ፡ ያናገሩትንና ፡ ኢጣሊያ ፡ የተቀበለችውን ፡ የኅብረት ፡ መግለጫ ፥ በተጨማሪም ፡ ክቡር ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ያደረጉትን ፡ የቃል ፡ ማብራሪያ ፡ አስተካክሎ ፡ ከመረመረና ፡ ከተገነዘበ ፡ በኋላ ፥ ስለአኵስም ፡ ሐውልት ፡ (**ክዋኒት**) ፡ እና ፡ ስለቀሩትም ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ ያለውን ፡ ጠቅላላ ፡ ኹኔታ ፡ ባጪሩ ፡ እንደሚከተለው ፡ ኾኖ ፡ አግኝቶታል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

1 ፤ በውል ፡ ረገድ ፤

1.1 ፤ ኹለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፥ በቃል ፡ ኪዳን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ባንድ ፡ ወገን ፥ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደሞ ፡ ጠላት ፡ መንግሥታት ፡ በኅብረታቸውና ፡ በየግላቸው ፡ የሚያከብሩትን ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ በጥር ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1939 ፡ ዓ.ም. ፡ (10 January 1947) ፡ ፓሪስ ፡ ላይ ፡ ሲፈርሙ ፥ በጠቅላላ ፡ አጠቃቀስ ፡ በአንቀጽ ፡ 33 ፡ ኢጣሊያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ነጻና ፡ በራሷ ፡ ዐደር ፡ መንግሥትነቷን ፡ አረጋግጣ ፡ ዐውቃ ፥

1.1.ሀ ፤ በአንቀጽ ፡ 45 ፡ በጦርነቱ ፡ ዘመን ፡ በሰላምና ፡ ሰብኣዊ ፡ ፍጥረት ፡ ላይ ፡ ጥፋትን ፡ ያዘዙትንና ፡ በደልን ፡ ፈጽመው ፡ በብሔሯ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ የራሷንና ፡ የሌላ ፡ አገር ፡ ዜጎችንም ፡ ጭምር ፡ ይዛ ፡ ለፍርድ ፡ ልታሳልፍና ፡ በወንጀል ፡ ግብራቸው ፡ ላይ ፡ ኹሉ ፡ ምስክሮችን ፡ ልታቀርብ ፤

1.1.ለ ፤ በአንቀጽ ፡ 74 ፡ ለጦር ፡ ካሳዋ ፡ 25 ፡ ሚልዮን ፡ ያሜሪካን ፡ ዶላር ፡ ወይም ፡ 62.5 ፡ ሚልዮን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ልትከፍልና ፥

1.1.ሐ ፤ በአንቀጽ ፡ 37 ፡ እና ፡ በአንቀጽ ፡ 75 ፡ ደግሞ ፥ በጦርነቱ ፡ ምክንያት ፡ በዘረፋና ፡ በሌላ ፡ በማንኛውም ፡ አኳኋን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የወሰደቻቸውን ፡ መታሰቢያዎች ፣ ንዋየ ፡ ቅድሳትንና ፡ ታሪካውያን ፡ ዕቃዎችን ፥ እንደዚሁም ፡ መዛግብትንና ፡ ሰነዶችን ፣ ወርቆችንና ፡ ሀብቶችን ፡ ኹሉ ፡ በጥሩ ፡ ኹኔታና ፡ በራሷ ፡ ኪሳራ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ብሔር ፡ አውጥታ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ልታስረክብ ፡ ግዴታ ፡ ፈርማለች ፤ ከዚያም ፡ ወዲህ ፥

1.2.ሀ ፤ ይህኑ ፡ መሠረታዊ ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ መነሻ ፡ በማድረግ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥትና ፡ የኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ የካቲት ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1948 ፡ ዓ.ም. ፡ ባደረጉት ፡ የጠቅላላ ፡ መሳተፍ ፡ ውል ፡ ላይ ፥ ኢጣሊያ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ እ"ባንኮ ፡ ዲ ፡ ሮማ" ፡ የምታኖረውን ፡ 16.3 ፡ ሚልዮን ፡ ያሜሪካ ፡ ዶላር ፡ ወይም ፡ 40.75 ፡ ሚልዮን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ አስተዳደር ፡ ጉዳይ ፥ ሰፋ ፡ ባለ ፡ ዝርዝር ፡ ከተግባቡ ፡ በኋላ ፥ ከኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የተመለሱትን ፡ የዕቃዎች ፡ ዝርዝር ፡ በዐባሪ ፡ አ. ፡ (ANNEX A) ፡ ላይ ፡ አስፍረው ፥ ወደፊት ፡ ተፈልገው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሚላኩትን ፡ ዝርዝር ፡ ደግሞ ፡ በዐባሪ ፡ በ. ፡ (ANNEX B) ፡ አመልክተው ፥ እነዚህ ፡ ዕቃዎች ፡ የሚገኙበትን ፡ ስፍራና ፡ ኹኔታ ፡ ተከታትሎ ፡ መረጃን ፡ የሚያቀርብ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ መልክተኛ ፡ ይህ ፡ ውል ፡ በጸና ፡ በ30 ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ በየበኩላቸው ፡ ሊልኩ ፡ ተስማምተው ፥ በፓሪስ ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ ላይ ፥ በአንቀጽ ፡ 37 ፣ 74 ፣ 75 ፡ እና ፡ 79 ፡ የተዘረዘሩት ፡ የኢጣሊያ ፡ ግዴታዎች ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ስምምነት ፡ በሚያረካ ፡ አኳኋን ፡ ሞልተው ፡ የተፈጸሙና ፥ በነዚህ ፡ አ. ፡ በ. ፡ ሠ. ፡ ዐባሪዎች ፡ (ANNEXES A, B, C) ፡ ባሉት ፡ ብቻ ፡ የተተኩ ፡ አድርገው ፡ ጨርሰዋል ።

የአኾስምን ፡ ሐውልት ፡ ግን ፥ ይህ ፡ ውል ፡ በጸና ፡ በስድስት ፡ ወሮች ፡ ውስጥ ፡ የኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፥ በራሱ ፡ ጥንቃቄ ፣ ኀላፊነትና ፡ ኪሳራ ፡ ነቅሎና ፡ ጠቅልሎ ፡ ናፖሊ ፡ ላይ ፥ ኢትዮጵያ ፡ ለምትመርጠው ፡ መርከብ ፡ ሊያስረክብ ፡ በዐባሪ ፡ ሠ. ፡ (ANNEX C) ፡ ግዴታ ፡ ገብቷል ።

1.2.ለ ፤ ይህ ፡ ውል ፡ የጠቅላላ ፡ ሀገራቱን ፡ የወግና ፡ የታሪክ ፡ ዕቃዎችን ፣ መታሰቢያዎችንና ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳትን ፣ መዛግብትንና ፡ ሰነዶችን ፥ እንደዚሁም ፡ ወርቆችንና ፡ ገንዘቦችን ፡ ኹሉ ፥ የሚመለከት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ለሕዝብ ፡ ምር ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ ጸድቋል ።

2 ፤ ባፈጻጸም ፡ ረገድ ፤

2.1.ሀ ፤ የኢጣሊያ ፡ ሕዝብ ፥ አብዛኛው ፥ በተለይም ፡ ማኅበራውያኑ ፡ (ሶሲያሊስቶችና ፡ ማርክሲስቶች) ፥ ንጉሣውያን ፡ የተባሉት ፡ የፖለቲካ ፡ ወገኖች ፡ በሙሉ ፥ የአኾስም ፡ ሐውልት ፥ የቀሩትም ፡ መታሰቢያዎች ፥ የመንግሥትና ፡ የግል ፡ የወግ ፡ ዕቃዎች ፣ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትና ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፥ ሌሎችም ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ ኹሉ ፥ በሙሉ ፡ ጥር ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1939 ፡ ዓ.ም. ፡ በፈረምነው ፡ የሰላም ፡ ውል ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

በገባነው ፡ ግዴታና ፥ ቀጥሎም ፥ ወደን ፡ በተቀበልነው ፡ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ደንብ ፡ (U.N. Charter) ፡ መሠረት ፥ ለኢትዮጵያ ፡ በክብር ፡ እንዲመለሱ ፡ ያስፈልጋል ፤ ይህም ፡ መኾኑ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ተገቢ ፡ ካሳዋ ፡ ሲኾን ፥ ለኢጣሊያ ፡ ደግሞ ፡ ከጦር ፡ አንሺነት ፡ ወንጀል ፡ የሚያነጻት ፡ ክብር ፡ ከመኾኑ ፡ ጋራ ፥ በኹለቱ ፡ አገሮች ፡ ወዳጅነት ፡ መኻከል ፡ የተፈጠሩትን ፡ መሰናክሎች ፡ አስወግዶ ፥ ለፖለቲካና ፡ ለጥሪት ፡ መሳተፍ ፡ ተግባር ፡ ሰፊ ፡ ጎዳናን ፡ የሚከፍት ፡ ድርጊት ፡ ይኾናል ፡ ሲል ፡ በግልጽ ፡ ይደግፋሉ ።

2.1.ለ ፤ በመንግሥቱም ፡ በኩል ፥ የፋሺስት ፡ አገዛዝ ፡ ትዝታ ፡ ከሚሰማቸው ፡ ጥቂቶች ፡ አባሎች ፡ በቀር ፥ ሌሎች ፡ የአብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ አስተያየት ፡ ያረፈበትን ፡ እውነት ፡ በመከተል ፡ በክብር ፡ መመለሳቸውን ፡ ይደግፋሉ ፤ ስለ ፡ ኾነም ፥ በኢትዮጵያ ፡ በኩል ፡ ሕዝቡ ፡ ለሐውልቱና ፡ ለቀሩትም ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ መመለስ ፡ ጉዳይ ፡ ደንታም ፡ የለው ፡ ብለው ፡ ኢጣሊያኖች ፡ ከማመናቸውም ፡ በላይ ፥ ከመንግሥቱም ፡ አባሎች ፡ መኻከል ፡ ሐውልቱ ፡ ራሱ ፡ ከሚመጣ　በለውጡ ፡ ሰፊ ፡ ጥቅም ፡ የምታገኝበት ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ መቀበል ፡ ይሻላል ፥ የሚሉ ፡ መኖራቸው ፡ ለሐውልቱ ፡ መመለስ ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ የነሱ ፡ እስኪመስሉ ፡ ድረስ ፡ ያላሰቡበት ፡ ኾነዋል ።

2.2.ሀ ፤ በኢትዮጵያ ፡ በኩል ፡ የፓሪስን ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ መነሻ ፡ በማድረግ ፡ ዴሞክራቲክ ፡ ኢጣሊያ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የገባቻቸውን ፡ ግዴታዎች ፡ ለማስፈጸም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥትና ፡ የኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ የካቲት ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1948 ፡ ዓ.ም. ፡ የተፈራረሙት ፡ ስምምነት ፡ በአኵስም ፡ ሐውልትና ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ በሚጠቀሱት ፡ ጥንታውያን ፡ ቅርሶች ፡ ረገድ ፡ ገና ፡ ሞልቶ ፡ ያልተፈጸመ ፡ መኾኑ ፡ ተረጋግጧል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የኅብረት ፡ አስተያየቱን ፡ በይፋ ፡ የሚገልጽበት ፡ ድርጅትና ፡ ሕዋስ ፡ እስካኹን ፡ ያላበጀ ፡ በመኾኑ ፥ ስለአኵስም ፡ ሐውልትና ፡ ስለቀሩትም ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ ያለው ፡ ዐይነተኛ ፡ አስተያየት ፡ በጽሑፍ ፡ ተገልጾ ፡ ባናየውም ፥ ስለነዚሁም ፡ ታሪካውያን ፡ ረጃቶች ፡ ኹላችንም ፡ በየልቦናችን ፡ በምናኖረው ፡ የመቈርቈር ፡ ስሜት ፡ ዐይነት ፡ የሚቃጠል ፡ መኾኑ ፡ አይጠረጠርም ።

2.2.ለ ፤ የኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ስለአኵስም ፡ ሐውልት ፡ በየስምምነቱ ፡ የገባውን ፡ ግዴታ ፡ ከፍጻሜ ፡ እንዲያደርስ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ በቃልና ፡ በደብዳቤ ፡ መጠየቁ ፡ ተነግሯል ።

3 ፤ አስተያየት ።

ኮሚቴው ፡ ጉዳዩን ፡ በዝርዝር ፡ መርምሮ ፡ ይህን ፡ ከተረዳ ፡ በኋላ ፥ ኢጣሊያኖች ፡ ዘርፈው ፡ የወሰዷቸው ፡ የአኵስም ፡ ከዋኒትና ፡ የይሁዳ ፡ አንበሳ ፡ ሐውልት ፥ እንደዚሁም ፡ እላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ ውሎች ፡ የተዘረዘሩት ፡ ሌሎች ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ መመለስ ፡ ጉዳይ ፡ እንዲፋጠን ፡ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፥

3.1 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የኅብረት ፡ አስተያየቱን ፡ ለይፋው ፡ የሚገልጽባቸውን ፡ ድርጅትና ፡ ሕዋስ ፡ ስላላበጀ ፥ የሕዝብነቱ ፡ ወኪል ፡ የኾነው ፡ የሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በጉዳዩ ፡ ላይ ፡ የሚያደርገው ፡ ንግግር ፡ በጋዜጣ ፡ እንዲወጣ ፣ በራዲዮ ፡ እንዲነገርና ፣ በቴሌቪዥን ፡ እንዲታይ ፡ ማድረግ ።

3.2 ፤ የመንግሥቱ ፡ አባሎች ፡ አስተያየት ፡ ሀገራቱ ፡ ባገኘችው ፡ የሰላም ፡ ውልና ፥ ቀጥሎም ፡ የግርማዊነታቸው ፡ መንግሥት ፡ ከኢጣሊያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ባደረገው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ሐውልቱና ፡ ስለ ፡ ታሪካውያን ፡ ዕቃዎች ፡ ፈጥኖ ፡ መመለስ ፡ ጉዳይ ፡ ብቻ ፡ እንዲተባበር ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ስለታየው ፥ የሁለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ የወል ፡ ጉባኤ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ እንዲቀርብ ፡ ሲል ፡ ያዘዘውን ፡ የውሳኔ ፡ ረቂቅ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነድፎ ፡ አቅርቧል ።

**ውሳኔ ።**


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

በሰላማዊነቷ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ በኾነችዋ ፡ በመንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ድርጅት ፡ ውስጥ ፡ አባል ፡ በመኾን ፡ ጓደኛዋ ፡ በነበረችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላይ ፥ ፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ የዋለችውን ፡ የግፍ ፡ ወረራና ፡ ያስከተለው ፡ ጭካኔ ፡ በሀገሪቱ ፡ ላይ ፡ የጣለውን ፡ መከራ ፡ ኢጣሊያ ፥ ኹለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ፍትሕን ፡ እንድታከብር ፡ ባስገደዳት ፡ ጊዜ ፥ ከግብረ ፡ ገብነት ፡ ውጭ ፡ በሕገ ፡ ወጥነት ፡ የተፈጸመ ፡ የአረመኔነት ፡ ወንጀል ፡ ነው ፡ ስትል ፡ አውግዛ ፥ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ በታኅሣሥ ፡ 22 ፡ ቀን ፡ 1934 ፡ ዓ.ም. ፡ የወደፊት ፡ ትውልዶችን ፡ ከጦርነት ፡ መከራዎች ፡ ለማዳን ፥ የሰውን ፡ ልጅ ፡ መሠረታውያን ፡ መብቶችን ፣ ክብርንና ፡ ዋጋን ፥ እንደዚሁም ፡ የወንድንና ፡ የሴትን ፣ የታናናሽና ፡ የታላላቅ ፡ ሀገሮችንም ፡ እኩልነት ፡ አረጋግጦ ፡ ለመመሥረትና ፡ ፍትሕን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ከአህጉራውያን ፡ (international) ፡ ስምምነቶችና ፡ ከርትዕ ፡ የሚፈልቁትንና ፡ ግዴታዎች ፡ ለማስከበር ፥ እንደዚሁም ፡ በተስፋፋ ፡ የሰው ፡ ነጻነት ፡ መኻከል ፡ የሕዝብን ፡ የሥልጣኔ ፡ ርምጃ ፡ ለመደገፍ ፥ በጥር ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1939 ፡ ዓ.ም. ፡ ፓሪስ ፡ ላይ ፡ በዋለው ፡ የሰላም ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነጻነትና ፡ በራሷ ፡ ዐደር ፡ መንግሥትነቷን ፡ ዐውቃና ፡ አረጋግጣ ፡ ተቀብላ ፥

1 ፤ በጦርነቱ ፡ ዘመን ፡ በሰላምና ፡ በሰብኣዊ ፡ ፍጥረት ፡ ላይ ፡ ወንጀል ፡ ፈጽመው ፡ የሚገኙትን ፡ የራሷንና ፡ የሌላ ፡ አገር ፡ ዜጎችን ፡ ይዛ ፡ ለፍርድ ፡ ልትሰጥና ፥ በወንጀል ፡ ግብራቸውም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምትጠይቃቸውን ፡ ምስክሮች ፡ ልታቀርብ ፤

2 ፤ ለጦር ፡ ጉዳት ፡ ካሳዋ ፡ 25 ፡ ሚልዮን ፡ ያሜሪካ ፡ ዶላር ፡ ወይም ፡ 62.5 ፡ ሚልዮን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ልትክስ ፤

3 ፤ በጦርነቱ ፡ ምክንያት ፡ በዘረፋና ፡ በሌላ ፡ በማንኛውም ፡ አኳኋን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የወሰደቻቸውን ፡ መታሰቢያዎች ፣ ንዋየ ፡ ቅድሳትንና ፡ ሌሎች ፡ ታሪካውያን ፡ ዕቃዎች ፣ ሰነዶችንና ፡ መዛግብትን ፣ ወረቀቶችንና ፡ ገንዘቦችን ፡ ኹሉ ፡ በጥሩ ፡ ኹኔታና ፡ በራሷ ፡ ኪሳራ ፡ ከኢጣሊያ ፡ መሬት ፡ አውጥታ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ልታስረክብ ፡ ወዳ ፥ ሌሎችም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ፍትሖች ፡ ልትፈጽም ፡ በታላቅ ፡ ወግ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብታ ፡ ፈርማ ፡ ነበር ።

ባፈጻጸም ፡ ረገድ ፡ ግን ፥ በጦርነቱ ፡ ፍጻሜ ፡ በሕዝቧ ፡ እውነተኛ ፡ ስሜት ፡ ተገዳ ፡ ስለሰላም ፡ ዕርቅ ፡ ዴሞክራት ፡ ኾና ፡ ሰልታ ፡ የቀረበችው ፡ ኢጣሊያ ፡ በሰላሙ ፡ ውል ፡ መከታ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በተገኘው ፡ ፋታ ፡ በባለሥልጣኖቿ ፡ የኰራት ፡ ስሜት ፡ ተለውጣ ፥ ፍጹም ፡ በኾነ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የገባቻቸውን ፡ የፍትሕ ፡ መሠረቶች ፡ ረስታ ፥ ኢትዮጵያን ፡ ስታስብ ፡ ወደማያስተኛት ፡ የጠላትነትም ፡ ስሜት ፡ ተመልሳ ፥ የጦር ፡ ወንጀለኞችን ፡ አሳልፋ ፡ ለፍርድ ፡ በመስጠት ፡ ረገድ ፡ ፈጽማ ፡ አልበገር ፡ እንዳለች ፥ ኢትዮጵያ ፡ ወደጥንት ፡ የባሕርይ ፡ ወሰኗ ፡ ለመመለስ ፡ ሰላማዊ ፡ ፖለቲካዋን ፡ በምትመራበትና ፥ ትኽክለኛና ፡ ሕገኛ ፡ አቤቱታዋን ፡ ለተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ በምታቀርብበት ፡ ጊዜ ፥ በነዚህ ፡ የሀገር ፡ ክፍሎች ፡ መኻከልና ፡ በዓለም ፡ ሸንጎ ፡ ላይ ፡ በተቻላት ፡ የገንዘብ ፣ የፖለቲካና ፡ የዲፕሎማሲ ፡ መሣሪያዎች ፡ ኹሉ ፡ አለመቈጠብ ፡ እንደተቃወመች ፡ የጦር ፡ ካሳዋን ፡ ገንዘብ ፡ ቀንሶ ፡ ለማስቀረት ፡ እንደጣረችና ፡ እንደኾነላትም ፡ ታይቷል ።

ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ በዐሥር ፡ ዓመት ፡ የሰላም ፡ ሥራ ፡ ያከናወነችው ፡ የራሷ ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ውጤት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰፊ ፡ ገበያን ፡ እንድትፈጥር ፡ ባስገደዳት ፡ ጊዜ ፥ በኢትዮጵያ ፡ ያሉ ፡ ዜጎቿ ፡ ንብረትና ፡ ሥራ ፡ የውል ፡ መድን ፡ የሌላቸው ፡ መኾኑ ፡ የንግድ ፡ ፍላጎቷን ፡ እፍጻሜ ፡ እንዳይደርስ ፡ የሚቃወማት ፡ ስለ ፡ ኾነባት ፥ ፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በኀይል ፡ ወራ ፥ ሕዝቧንና ፡ ሰራዊቷን ፡ ኹሉ ፡ ዘርፋ ፡ ወስዳ ፥ ከወንጀል ፡ ኹሉ ፡ ለረከሰው ፡ የሕዝብን ፡ ሕይወትና ፡ ነጻነት ፣ መብትና ፡ ሀብት ፡ ለመንጠቅ ፡ ላፈሰሰችው ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ ምስክር ፡ ኾኖ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፥ ሮማ ፡ ከተማ ፡ ያቆመችውን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሐውልት ፡ ማንሣትና ፥ ባለቤቱ ፡ ለኾነችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ መመለስ ፡ በፋሺስት ፡ አገዛዝ ፡ ውስጥ ፡ ሳለች ፡ ከደረሰባት ፡ ግፍ ፡ ዋዱነት ፡ የሚያነጻት ፥ ከኢትዮጵያም ፡ ጋራ ፡ ጥቅም ፡ በሚኖረው ፡

ወዳጅነት ፡ የሚያስተሳስራት ፡ ምክንያት ፡ መኾኑን ፡ ስትነገር ፥ እውነትነቱን ፡ ተቀብላ ፥ የካቲት ፡ 26 ፡ ቀን ፡ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ባደረገው ፡ ስምምነት ፡ የአኵስምን ፡ ሐውልት ፡ በራሷ ፡ ጥንቃቄ ፣ ኀላፊነትና ፡ ገንዘብ ፡ እናፖሊ ፡ ወደብ ፡ ላይ ፡ አውጥታ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ልታስረክብ ፡ ግዴታ ፡ ገብታ ፡ ነበር ።

ይኹን ፡ እንጂ ፥ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ በፓሪስ ፡ የሰላም ፡ ውል ፡ ላይ ፡ በአንቀጽ ፡ 37 ፣ 74 ፣ 75 ፣ 79 ፡ የተጣለባትን ፡ ግዴታዎች ፡ ባዲሱ ፡ ስምምነት ፡ ካስወገደችና ፥ የዜጎቿን ፡ ንብረትና ፡ ሥራ ፡ በሕግ ፡ ካስጠበቀች ፡ በኋላ ፡ ዘንታ ፡ ከመቀመጧ ፡ በቀር ፡ ከቶ ፡ ግዴታዋን ፡ ለመፈጸም ፡ አልሞከረችም ።

በዳይ ፡ ሕዝብ ፡ በሰላም ፡ ውል ፡ ከሚፈጽማቸው ፡ ግዴታዎች ፡ በላይ ፡ ጥፋቱን ፡ ዐውቆ ፡ ከልብ ፡ በመጸጸት ፥ ተበዳይን ፡ ይቅርታ ፡ ካልጠየቀና ፡ ጠቡን ፡ የሚያስታውሱትን ፡ ነገሮች ፡ ዅሉ ፡ እንዲፋቁ ፡ ካላደረገ ፡ በቀር ፥ የአጥቂነት ፡ መንፈሱ ፡ ከርሱ ፥ የመበቀል ፡ ፍላጎቱ ፡ ደግሞ ፡ ከተበዳዩ ፡ ልቦና ፡ ሊወገድና ፥ እጅግ ፡ ጠቃሚ ፡ የኾነውን ፡ የወደፊቱን ፡ ወንድማማችነትን ፡ ኑሮ ፡ የሚያስገኘው ፡ ኹኔታ ፡ ሊፈጠር ፡ አለመቻሉን ፡ ኢጣሊያ ፡ አልተገነዘበችም ።

በኢትዮጵያ ፡ በኩል ፥ በቀደሙት ፡ ውሎች ፡ መንፈስ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ ከባሕርይ ፡ ከሚገኘውም ፡ ደግነት ፡ ጭምር ፡ በማንኛውም ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ወዳጅነትና ፡ መግባባት ፡ ያልጐደለው ፡ መተባበር ፡ ሲደረግላት ፥ ኢጣሊያ ፡ በርሷ ፡ በኩል ፡ ያው ፡ የጠላትነት ፡ ስሜቷ ፡ እያሸነፋት ፥ በገባችው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ ገንዘቧ ፡ ያልኾነውን ፡ ጥንታዊ ፡ ሐውልት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በማስረከብ ፡ እንኳ ፡ ለተደረገላት ፡ ሰፊ ፡ ውለታ ፡ አቻው ፡ ሊኾን ፡ የሚቃጣ ፡ ብድር ፡ ለመመለስ ፡ አልፈቀደችም ።

ለኢትዮጵያ ፥ የነገሥታቷ ፡ ገናንነት ፥ የጠቢባኗ ፡ ዕውቀት ፥ የሕዝቧ ፡ አንድነትና ፡ ጠቅላላው ፡ የሀገሪቱ ፡ ሕያውነት ፡ ግዙፍ ፡ ምሳሌ ፡ ኾኖ ፥ አኵስም ፡ ላይ ፡ የኖረውን ፡ ሐውልት ፡ ሮማ ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ የፋሺስቶች ፡ ግፈኝነት ፡ መታሰቢያ ፡ ኾኖ ፡ እንዲቈይ ፡ ወደደች ።

የኢትዮጵያ ፡ ውርደት ፡ የርሷ ፡ ጌጥ ፡ እንዲኾን ፡ ፈቀደች ። ይህም ፡ ኹኔታ ፡ ከውርደት ፡ ዅሉ ፡ የከፋው ፡ በራሷ ፡ ድርጊት ፡ የሚገለጽባት ፡ ነውር ፡ መኾኑን ፡ ልታውቅ ፡ አልፈቀደችም ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፥ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ደሙን ፡ አፍስሶ ፣ ዐጥንቱን ፡ ከስክሶ ፥ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መሪነት ፡ ጠላቱን ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፥ ነጻነቱን ፡ ዐድሶ ፥ የተወሰደ ፡ ሀገሩን ፡ አስመልሶ ፥ በክብር ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ እንደገና ፡ ከተቀመጠ ፡ ወዲያ ፥ ድል ፡ አድራጊ ፡ ኾኖ ፡ ድል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዅሉ ፡ ታሪኩና ፡ ክብሩ ፡ የኾነውን ፡ ሐውልቱን ፡ ተቀምቶ ፡ መኖር ፡ ፍጹም ፡ ውርደቱ ፡ መኾኑን ፡ ስለሚያውቅ ፥ አይቀበለውም ።

ስለዚህም ፥ የኢትዮጵያ ፡ የሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በግንቦት ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1960 ፡ ዓ.ም. ፡ ባዋለው ፡ የኹለቱ ፡ ምክር ፡ ቤቶች ፡ የጋራ ፡ ጉባኤው ፥ ይህን ፡ ዅሉ ፡ ኹኔታ ፡ በሰፊው ፡ አጥንቶና ፡ አመዛዝኖ ፥ ባንድ ፡ ወገን ፡ ኢጣሊያ ፡ ካልተጨነቀች ፥ ወይም ፡ የጥቅም ፡ ግዴታ ፡ ካልኾነባት ፡ በቀር ፥ የገባቻቸውን ፡ ውሎች ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ደንብ ፡ ጐልቶ ፡ በተገለጸው ፡ አህጉራውያን ፡ ስምምነቶችንና ፡ ብሔራዊ ፡ ርትዕን ፡ በማክበር ፡ ግዴታ ፡ መሠረት ፥ ወይም ፡ በግብረ ፡ ገብነት ፡ መንገድ ፡ የምትፈጽም ፡ እንደማትኾን ፡ ሲረዳ ፥ በሌላው ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፥ ኵሩውና ፡ ታሪኩን ፡ አክባሪው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ በአኵስም ፡ ሐውልት ፡ ስንኳን ፡ በመቅረቱ ፡ በመዘግየቱ ፡ እንኳ ፡ የማይስማማ ፡ መኾኑን ፡ በሚገባ ፡ ስላመነ ፤

*የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፥ ኢጣሊያ ፡ በውል ፡ ረገድ ፡ የሚገባትና ፡ የምታከብረውም ፡ ቋንቋ ፡ ጭንቅ ፡ ወይም ፡ የጥቅም ፡ ግዴታ ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ አምኖና ፡ የአባሎቹን ፡ አስተያየት ፡ ዅሉ ፡ በዚሁ ፡ እውነትና ፡ በሐውልቱ ፡ መመለስ ፡ ብልጫ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ አስተባብሮ ፥*

*ሀ ፤ በዜጋ ፡ መሸጋገር ፡ ረገድ ፥ በመጪዎች ፡ ላይ ፡ በር ፡ እስከ ፡ መዝጋት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ ነዋሪዎቹንም ፡ ፈጽሞ ፡ እስከ ፡ ማስወጣት ፥ በጥሪት ፡ መስክ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የንግድ ፡ መለዋወጥን ፡ እስከ ፡ ማቆምና ፥*

*መደምደሚያውን ፥ በዲፕሎማሲ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ግንኙነትን ፡ ፈጽሞ ፡ እስከ ፡ ማቋረጥ ፡ ድረስ ፡ ተረማማጅ ፡ በሚኾን ፡ የጭቈና ፡ ዘዴ ፡ በግልጽና ፡ በማይቋረጥ ፡ አደራረግ ፡ በመጠቀም ፥ የአኵስም ፡ ሐውልትና ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የሚጠቀሱት ፡ ታሪካውያን ፡ መታሰቢያዎች ፡ በስድስት ፡ ወሮች ፡ ውስጥ ፡ ወደየነበሩበት ፡ ስፍራ ፡ እንዲመለሱ ፡ እንዲያደርግ ፡ ያስፈልጋል ፡ ሲል ፡ ወስኖ ፤*

*ለ ፤ ይህ ፡ ሐውልትና ፡ የሚጠቀሱት ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ ኹሉ ፡ እስከተመለሱና ፥ ከነርሱም ፡ መመለስ ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ የሚመለሰው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክብር ፡ ተሠይሞ ፥ የኹለቱ ፡ ሀገሮች ፡ ወዳጅነት ፡ በንጹሕ ፡ መንፈስ ፡ ላይ ፡ ከመመሥረቱ ፡ በፊት ፥ የዳበረ ፡ ፍቅር ፡ መገለጫ ፡ የኾነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጕብኝት ፡ ክብር ፡ ቀድሞ ፡ እንዳይሰጣት ፥ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ አገር ፡ መኼድ ፡ እስከዚህ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ እንዲዘገይ ፡ ያሳስባል ፨*

---

# ሐተታ ፡ መጻሕፍት ።

books review | revue de livres | مراجعة الكتب

በቅርቡ ፡ ከደረሱን ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፦

▶ **አንዱዓለም ፡ አራጌ** ፤ *"በዘመናት ፡ መካከል ፤ በእስር ፡ ቤት ፡ ጭንቅ ፡ ውስጥ ፡ የተወለዱ ፡ ሥራዎች ።"* ፥ ዐዲስ ፡ አበባ ፥ 2010 ፡ ዓ.ም. ፤ 300 ፡ ገጾች ።

ኹላችን ፡ የምናውቃቸው ፥ የኹላችን ፡ ባለውለታ ፥ የነጻነት ፡ ታጋይ ፥ የስያሳ ፡ ሰው ፡ አንዱዓለም ፡ አራጌ ፥ ዛሬ ፥ ከብዙ ፡ ዓመት ፡ እስር ፡ ተፈትተው ፥ ይህችን ፡ መጽሐፍ ፡ አሳትመውልናል ፤ እንኳን ፡ ለዚህ ፡ አበቃዎ! ፡ እንኳን ፡ ደስ ፡ አለዎ! ፡ እንላቸዋለን ።




መጽሐፉ ፥ በትግል ፡ ሕይወት ፡ የሚደርሰውን ፡ አደጋ ፣ የሚፈጸመውን ፡ ግፍ ፣ የሚገጥመውን ፡ ፈተና ፣ የሚከፈለውን ፡ የመሥዋዕት ፡ ዋጋ ፡ ከመዝከር ፡ ከማስገንዘብ ፡ ጋራ ፥ በፈተና ፡ ያለፈ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ የሚያገኘውንም ፡ ትምህርት ፡ ጭምር ፥ አላንዳች ፡ የቂም ፡ በቀል ፡ ስሜት ፥ በእውነተኛ ፡ የፈላስፋ ፡ ዐይን ፡ አይተው ፥ በተዋበ ፡ ዐማርኛ ፡ ደርሰውልናል ። የተለመዱ ፡ የፊደል ፡ ስሕተቶች ፡ ቢኖሩበትም ፥ በጠቅላላው ፡ ደኅና ፡ የተናበበ ፡ ጽሑፍ ፡ በመኾኑ ፥ ንባቡ ፡ ይገራል ።

ድርሰቱ ፡ በስድ ፡ ንባብና ፡ በግጥም ፥ ባማርኛና ፡ በእንግሊዝኛ ፡ መሰናሰሉ ፥ የመጽሐፉን ፡ አወቃቀርና ፡ አቀራረብ ፡ ከተለመደው ፡ ለየት ፡ ያደርገዋል ። ዐያሌ ፡ ትምህርት ፡ ይገኝበታልና ፥ ንባቡን ፡ እንመክራለን ፨


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

# ጥርዮታዊ ፡ ትንታኔ ።

economic analysis | analyse économique | تحليل إقتصادي



## እድገት ፡ ወይስ ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፧

## እድገትና ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ በኢትዮጵያ ፥ ባለፉት ፡ 50 ፡ ዓመታት ።

---

እስከ ፡ 2005 ፡ ዓ.ም. ፡ ድረስ ፥ ከደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ ቀጥላ ፡ ያፍሪቃ ፡ 2ኛዋ ፡ ግዙፍ ፡ ጥርየት ፡ (economy) ፡ የነበረችው ፡ ናይጄሪያ ፥ ከ2005 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ ከደቡብ ፡ አፍሪቃ ፡ ልቃ ፥ 1ኛ ፡ መኾኗን ፡ ለዓለም ፡ ኹሉ ፡ ዐውጃለች ። ሌላ ፡ ነገር ፡ አይደለም ፥ የሀገራዊ ፡ ሒሳብ ፡ (national accounts) ፡ አያያዟን ፡ በማዘመንና ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ባግባቡ ፡ ያልተቈጠሩና ፡ ችላ ፡ የተባሉ ፡ የሀብት ፡ ዐይነቶችን ፡ በተገቢው ፡ በማሰብ ፥ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርቷ ፡ ከነበረበት ፡ 280 ፡ ቢልዮን ፡ ዶላር ፡ ወደ ፡ 509 ፡ ቢልዮን ፡ ዶላር ፡ ማደጉን ፡ አስታውቃለች ። የኢትዮጵያ ፡ ጥርየትም ፡ ግዝፈት ፡ በተገቢው ፡ ቢመረመር ፡ ኹኔታው ፡ ከዚህ ፡ የተለየ ፡ አይኾንም ። በተለይ ፡ የዕርሻና ፡ የከብት ፡ ርቢ ፣ የወርቅና ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ማዕድናት ፣ የአገልግሎት ፡ ዘርፈ ፡ ጥርየቶች ፡ ዛሬ ፡ ከሚታሰቡበት ፡ መጣናቸው ፡ ከ50% ፡ እስከ ፡ 80% ፡ እንደሚልቁ ፡ ይታመናል ። በዚህ ፡ ኹኔታ ፡ ውስጥ ፦ *"ዘንድሮ ፡ የኹለት ፡ አኃዝ ፡ እድገት ፡ ታይቷል"* ፡ የሚለው ፡ ያለፉት ፡ 15 ፡ ዓመታት ፡ ፉከራ ፡ ገና ፡ ካልተቈጠረው ፡ ሀብት ፡ በቂ ፡ ተረፍ ፡ ስላለለት ፥ ማስተባበሉ ፡ አይመችም ። *"እውነት ፡ ነው ፡ / ፡ ውሸት ፡ ነው"* ፡ ከማለት ፡ በፊት ፡ ዘርዘር ፡ ያለ ፡ ትንታኔ ፡ ያሻል ።

ያንድ ፡ ሀገር ፡ **ምጥራይ** ፡ (economic system) ፥ ማደግ ፡ ወይም ፡ አለማደጉ ፡ የሚለካባቸው ፡ ኹለት ፡ የልክ ፡ ዐይነቶች ፡ አሉ ፦ ***የስም*** ፡ እድገት ፡ ወይም ፡ ***ስማዊ*** ፡ እድገት ፡ (nominal growth) ፡ እና ፡ ***የእውን*** ፡ እድገት ፡ ወይም ፡ ***እውናዊ*** ፡ እድገት ፡ (real growth) ።

ጥርየቱ ፡ በሀገሩ ፡ ምንዛሪ ፡ ሲተመን ፥ ከዓምና ፡ ዘንድሮ ፡ የስም ፡ እድገት ፡ ሊያሳይ ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፥ ያንድ ፡ ሀገር ፡ አጠቃላይ ፡ ጥርየት ፡ ዓምና ፡ 1000 ፡ ቢልየን ፡ ብር ፡ ደርሶ ፡ ነበር ፡ ቢባል (12) ፤ ዘንድሮ ፡ ደግሞ ፡ 1200 ፡ ቢልየን ፡ ብር ፡ ደርሷል ፡ ቢባል ፥ (1200-1000)/1000 = 0.2 ፡ ወይም ፡ 20% ፡ (ኻያ ፡ በመቶ) ፡ አድጓል ፡ እንላለን ። እድገቱ ፡ ግን ፡ የስም ፡ እንጂ ፡ የእውን ፡ አይደለም ።

የእውን ፡ እድገቱን ፡ ለማወቅ ፡ ዓመታዊውን ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ (price inflation) ፡ ማገናዘብ ፡ ይኖርብናል ።

### 1 ፤ የዋጋ ፡ ንረት ።

የዋጋ ፡ ንረት ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ፧ የዋጋ ፡ ንረት ፡ በኹለት ፡ መንገድ ፡ ይገለጻል ፦

- ባንድ ፡ ምጥራይ ፡ ውስጥ ፡ (ለምሳሌ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ምጥራይ) ፡ በተወሰነ ፡ ዘመን ፡ (ለምሳሌ ፥ ባንድ ፡ ዓመት) ፡ የገበያ ፡ ዋጋዎች ፡ ኹሉ ፡ ያሳዩት ፡ እድገት ፡ መጠን ፡ መግለጫ ፡ ማለት ፡ ነው ፤
- ወይም ፥ ያንድ ፡ ሀገር ፡ ምንዛሪ ፡ (ለምሳሌ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ብር) ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ያሳየው ፡ የመግዛት ፡ ዐቅም ፡ መቀነስ ፡ ማለትም ፡ ነው ፡ (ለምሳሌ ፥ ዓምና ፡ አንድ ፡ ኩንታል ፡ ወይም ፡ 100 ፡ ኪሎ ፡ ጤፍ ፡ 2500 ፡ ብር ፡ የነበረው ፥ ዘንድሮ ፡ 3000 ፡ ብር ፡ ቢገባ ፥ ይኸው ፡ 2500 ፡ ብር ፡ ዘንድሮ ፡ የሚገዛው ፡ 83.3 ፡ ኪሎ ፡ ጤፍ ፡ ብቻ ፡ ነው) ።

ይህ ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ መጠን ፡ በ**ችርቻሮ ፡ ዋጋ ፡ ቋም** ፡ (retail price index) ፡ ይለካል ። የችርቻሮ ፡ ዋጋ ፡ ቋም ፡ ያንድ ፡ ዐይነተኛ ፡ ቤተሰብ ፡ የወጪ ፡ አርእስቶች ፡ ላይ ፡ ተመሥርቶ ፡ የሚታሰብ ፡ ቋም ፡ (index) ፡ ነው ። ለምሳሌ ፥ አንድ ፡ ቤተሰብ ፥ የምግብ ፣ የቤት ፡ ኪራይ ፣ የውሃ ፣ የኤሌትሪክ ፣ የጤና ፣ የልብስ ፣ የትምህርት ፡ ቤት ፣ የመጓጓዣ ፣ ወዘተርፈ ፥ ወጪዎች ፡ ይኖሩበታል ። እያንዳንዱ ፡ የወጪ ፡ አርእስት ፡ እጠቅላላው ፡ ወጪ ፡ ላይ ፡ የተወሰነ ፡ ድርሻ ፡ ይኖረዋል ። የችርቻሮ ፡ ዋጋ ፡

---

12 ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥታውያን ፡ ተቋማት ፡ የተገኘ ፡ ልቅም ።


©ኢ.ሀ.ሥ.ሕ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ቋሙን ፡ የሚያሰላው ፡ ድርጅት ፥ የወጪ ፡ አርእስቶቹን ፡ ዐይነትና ፡ ምጣኔያቸውን ፡ በየጊዜው ፡ እያዘመነ ፡ በጥንቃቄ ፡ ይወስናል ። ለምሳሌ ፥ የዛሬ ፡ 30 ፡ ዓምት ፡ የስልክ ፡ አገልግሎት ፡ ደንበኞች ፡ 0.5 ፡ ሚልዮን ፡ አይሞሉም ፡ ነበር ፥ ዛሬ ፡ ግን ፡ 50 ፡ ጊዜ ፡ የበለጠ ፡ የደንበኞች ፡ ብዛት ፡ አለ ፤ ስለዚህ ፥ የስልክ ፡ ወጪ ፡ በሀገሪቱ ፡ ቤተሰቦች ፡ ወጪ ፡ ውስጥ ፡ በዘመናችን ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ድርሻ ፡ ይኖረዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። የችርቻሮ ፡ ዋጋ ፡ ቋሙም ፡ ይህን ፡ ዐይነቱን ፡ የወጪ ፡ አርእስት ፡ ሚዛን ፡ ለውጥ ፡ በየጊዜው ፡ ማገናዘብና ፡ ማዘመን ፡ ይኖርበታል ።

የችርቻሮ ፡ ዋጋ ፡ ቋሙ ፡ አንድ ፡ **መደብ-ዓመት** ፡ (base year) ፡ ይኖረዋል ፥ ለምሳሌ ፡ መንግሥታዊው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የአኃዝ ፡ ተቋም ፡ (*"ማእከላዊ ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ባለሥልጣን"*) ፥ 2002 ፡ ዓ.ም.ን ፡ መደብ-ዓመት ፡ አድርጎ ፥ ከ1998 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 2009 ፡ ዓ.ም. ፡ ድረስ ፡ የኢትዮጵያን ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ ልቅም ፡ (data) ፡ እንደሚከተለው ፡ *[ሰንጠረዥ-፩]* ፡ ዘግቦታል ፡—

| *ሰንጠረዥ ፡ ፩ ፤ ማእከላዊ ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ባለሥልጣን* | | |
|---|---|---|
| ዓ.ም. (year) | የችርቻሮ ፡ ዋጋ ፡ ቋም (consumer price index) | የዋጋ ፡ ንረት ፡ መጠን ፡ (%) (rate of inflation) |
| 1998 | 50.4 | ... |
| 1999 | 59 | 17.24% |
| 2000 | 85.2 | 44.36% |
| 2001 | 92.5 | 8.48% |
| 2002 | 100 | 8.15% |
| 2003 | 133.2 | 33.25% |
| 2004 | 165.4 | 24.12% |
| 2005 | 178.8 | 8.08% |
| 2006 | 192 | 7.40% |
| 2007 | 211.4 | 10.11% |
| 2008 | 226.8 | 7.26% |
| 2009 | 249.1 | 9.85% |

በግጽው ፡ መልክ ፡ እንደሚከተለው ፡ ይከሠታል ፡—

የኢትዮጵያ ፡ የችርቻሮ ፡ ዋጋ ፡ ንረት ፡ ኺደት ፥
ከ1998 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 2009 ፡ ዓ.ም. ።




*ግጽው-፩*

ከአኃዛዊው ፡ ልቅም ፡ እንደምናየው ፥ ከመደብ-ዓመት ፡ 2002 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 2009 ፡ ዓ.ም. ፥ የችርቻሮ ፡ ዋጋ ፡ ንረት ፡ ቋም ፡ ከ 100 ፡ ወደ ፡ 249.1 ፡ አድጓል ፤ ወይም ፥ በሌላ ፡ አነጋገር ፥ በ 7 ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የችርቻሮ ፡ ዋጋ ፡ ባማካይ ፡ 2.5 ፡ ጊዜ ፡ አድጓል ። ባማካይ ፥ አንድ ፡ ሸቀጥ ፡ በ 2002 ፡ ዓ.ም. ፡ 100 ፡ ብር ፡ ያወጣ ፡ የነበረው ፥ በ 2009 ፡ ዓ.ም. ፡ 250 ፡ ብር ፡ ገባ ፡ ማለት ፡ ነው ። አኃዙ ፡ አማካይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ የዋጋው ፡ ንረት ፡ ከሸቀጥ ፡ እሸቀጥ ፡ ይለያል ።

ይህ ፡ የችርቻሮ ፡ ዋጋ ፡ ቋም ፥ በያመቱ ፡ የሚታየውን ፡ እድገት ፡ ከስማዊ ፡ (nominal) ፡ እድገትነት ፡ ወደ ፡ እውናዊ ፡ (real) ፡ እድገትነት ፡ ለውጦ ፡ በትኽክል ፡ ያስገነዝባል ።

**2 ፤ እድገት ።**

እድገት ፡ ማለት ፥ ያንድ ፡ ምጥራይ ፡ አጠቃላይ ፡ የማምረት ፡ ዐቅም ፡ ማደግ ፡ ነው ።

በርከት ፡ ያሉ ፡ የእድገት ፡ መለኪያዎች ፡ አሉ ፤ **የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርት** ፡ ወይም ፡ **ሀ.ው.ጠ.ም.** ፡ (gross domestic product ፡ ወይም ፡ G.D.P.) ፡ ዘወትር ፡ ይጠቀሳል ። ሀ.ው.ጠ.ም. ፥ አንድ ፡ ሀገራዊ ፡ ምጥራይ ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሚጠርየው ፡ የሚያመርተው ፡ በገንዘብ ፡ የተተመነ ፡ የሸቀጥና ፡ ያገልግሎት ፡ ምርት ፡ ድምር ፡ መጠን ፡ ተብሎም ፡ ይደነገጋል ። ይህ ፡ ጠቅላላ ፡ የሀብት ፡ መጠን ፡ በሀገሩ ፡ ጠቅላላ ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ሲካፈል ፡ ደግሞ ፥ **ነፍስ-ወከፍ ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርትን** ፡ (GDP per capita) ፡ ይሰጠናል ። የነፍስ-ወከፍ ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርት ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ማደግ ፡ የነዋሪውን ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ ማደግ ፡ የሚያሳየው ፣ እድገቱ ፡ ከስማዊ ፡ ይልቅ ፡ እውናዊም ፡ ኾኖ ፡ ሲረጋገጥ ፡ ነውና ፦

- የእድገቱ ፡ *መጠን* ፡ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ ከታየው ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ በላይ ፡ ኾኖ ፡ *መገኘት* ፡ አለበት ፤
- እንዲሁም ፡ የእድገቱ ፡ *መጠን* ፡ ከዓመታዊው ፡ የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ እድገት ፡ በልጦ ፡ *መገኘት* ፡ አለበት ።

ለምሳሌ ፣ አጠቃላይ ፡ ሀገራዊ ፡ የምርት ፡ እድገቱ ፡ ከዓምናው ፡ 20% ፡ ቢኾንና ፣ የዋጋ ፡ ንረቱ ፡ ደግሞ ፡ ከዓምናው ፡ 15% ፡ ቢኾን ፣ የምርቱ ፡ እውናዊ ፡ እድገት ፡ 20% - 15% = 5% ፡ ብቻ ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ፤ 10% ፡ እድገት ፡ በዋጋ ፡ ንረት ፡ ተበልቷል ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፣ ዓመታዊው ፡ የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ *መጠን* ፡ 1.8% ፡ ቢኾን ፣ የነፍስ-ወከፍ ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርት ፡ 5% -1.8% = 3.2% ፡ ብቻ ፡ ማደጉን ፡ እናገኛለን ።

## 3 ፤ ግብዝ ፡ ልቅም ።

በዚህ ፡ *መሠረት* ፡ ላይ ፡ ኾነን ፡ በረገዱ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥርየት ፡ ኹኔታ ፡ ለመሸለግ ፣ የአኃዛዊ ፡ ልቅሙን ፡ ጥራትና ፡ አስተማማኝነት ፡ ስንመለከት ፣ ብዙ ፡ ችግሮች ፡ ይገጥሙናል ።

### 3.1 ፤ ተቋማዊ ፡ ችግር ።

የኢትዮጵያን ፡ አኃዛዊ ፡ ልቅም ፡ በኀላፊነት ፡ የማጠናቀር ፡ ሥልጣን ፡ የተሰጠው ፡ እላይ ፡ የጠቀስነው ፡ *"ማእከላዊ ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ባለሥልጣን"* ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፣ ሀገሪቱ ፡ ራሷ ፡ የተቸገረች ፡ ሀገር ፡ ስለኾነች ፣ ተቋሙ ፡ በባጀትም ፡ በሰው ፡ ኀይልም ፡ ባልተሟላ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። የሥራውም ፡ ውጤት ፡ ከዓለም ፡ ደረጃ ፡ ጋራ ፡ ሲስተያይ ፡ አሳፋሪ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ። ይህን ፡ ለመገንዘብ ፣ የተቋሙን ፡ የኢንተርኔት ፡ መርበቢያ ፡ መጐብኘትና ፣ ይፋ ፡ ያወጣቸውን ፡ አኃዛውያን ፡ መዝገቦች ፡ አየት ፡ ማድረግ ፡ ይበቃል ። ባቀራረብ ፡ ረገድ ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ጥንቃቄ ፡ ያልተደረገበት ፡ ዝልጉስ ፡ መዝገብ ፡ በያይነቱ ፡ ቀርቧል ። ከፊት ፡ አድርጎ ፡ ላየው ፦ *እውን ፡ ያንዲት ፡ ሀገር ፡ ተቋም ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ያሰናዳ ፡ ወይስ ፡ ያንድ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ወጣቶች ፥ ያሠኛል* ። የተቋሙ ፡ ሠራተኞች ፣ በተለይ ፡ ባመራር ፡ ደረጃ ፡ የሚገኙት ፣ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ካንድ ፡ አካባቢ ፡ የመጡ ፡ መኾናቸው ፡ ይታወቃል ፤ ከደርግ ፡ ዘመን ፡ አንሥቶ ፣ ከሕዝብ ፡ ቈጠራና ፡ አሰፋፈር ፡ ዝምሮ ፡ እስከዋጋ ፡ ንረትና ፡ ምርት ፡ እድገት ፡ ድረስ ፡ አኃዛዊ ፡ *መረጃን* ፡ በዚህ ፡ ኹኔታ ፡ ሲያቀርቡልን ፡ ኖረዋል ። ይህ ፡ የተቋሙ ፡ ዝልጉስ ፡ ኹኔታ ፡ ለተፈለገው ፡ ስያሳዊ ፡ ስርጀታ ፡ ኸሉ ፡ ተመቺ ፡ የጥፋት ፡ *መሣሪያ* ፡ ኾኖ ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ዘልቋል ። *"በቃ!"* ፡ ሊባል ፡ ይገባል ፤ ኹኔታው ፡ ሲፈቅድም ፣ የምርመራ ፡ **ድርገት** ፡ (committee) ፡ ተቋቁሞ ፡ ሥራው ፡ በዝርዝር ፡ ሊመረመርና ፡ ተፈላጊው ፡ ሕጋዊ ፡ ርምጃ ፡ ሊፈጸም ፡ ይገባል ።

### 3.2 ፤ ስያሳዊ ፡ ችግር ።

አኃዛዊ ፡ *መረጃ* ፡ ዋነኛ ፡ ስያሳዊ ፡ *መሣሪያ* ፡ እንደ ፡ *መኾኑ* ፡ *መጠን* ፣ በተለይ ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ በሌለባቸው ፡ ሀገሮች ፡ ትኽክለኛ ፡ አኃዝ ፡ ይፋ ፡ አይወጣም ። *"ለፖለቲካችን ፡ ይጠቅመናል"* ፡ የሚባለው ፡ ብቻ ፡ ተቀምሞ ፡ በ*"ፕሮፓጋንዳ"* ፡ መልክ ፡ ይሠራጫል ። ማንም ፡ ትንፍሽ ፡ የሚል ፡ የለም[13] ። አንዳንድ ፡ የውጭ ፡ መንግሥታትና ፡ አህጉራውያን ፡ ተቋማት ፡ ተደርበው ፡ የ*"ፕሮፓጋንዳው"* ፡ ተባባሪዎች ፡ መኾናቸው ፡ ደግሞ ፣ የኢትዮጵያን ፡ ኹኔታ ፡ በተለየ ፡ ያባብሰዋል ።

### 3.3 ፤ ስልታዊ ፡ ችግር ።

የኢትዮጵያ ፡ መልክአ ፡ ምድራዊ ፡ ገጽታ ፡ የማይታለፉ ፡ የመገናኛና ፡ የተደራሽነት ፡ ችግሮችን ፡ ስለሚደቅን ፣ ሀገር ፡ ዐቀፍ ፡ የመረጃ ፡ አሰባሰቡ ፡ ኸል ፡ ጊዜም ፡ ቢኾን ፡ ጐደሎ ፡ ነው ። ለምሳሌ ፣ በቅርቡ ፡ በI.G.A.D. ፡ ሀገሮች ፡ ዋቢነት ፡ በ2002 ፡ ዓ.ም. ፡ በተደረገ ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርት ፡ አኃዝ ፡ ምርመራ ፣ በረገዱ ፡ ሲቀርቡ ፡ የኖሩት ፡ የኢትዮጵያ ፡ አኃዞች ፡ ከእውኑ ፡ 40% ፡ እስከ ፡ 80% ፡ ያነሱ ፡ እንደነበሩ ፡ ተረጋግጧል ። የአኃዝ ፡ ለቀማው ፡ ስልት ፡ መሻሻል ፡ ይኖርበታል ።

በዚህ ፡ ኹኔታ ፡ ውስጥ ፡ ኾነን ፣ የኢትዮጵያን ፡ የእድገትና ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ አኃዛውያን ፡ መረጃዎች ፡ እንዴት ፡ እንያቸው ፥ ባለፉት ፡ ዐሥር ፡ ዓመታት ፣

13 *"ኻብ ፡ ከኼደ ፡ ውሻ ፡ ጮኸ"* ፡ እንዲሉ ፣ ከ28 ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የምርጫ ፡ መቃረብ ፡ ያነቃቃቸው ፡ የ*"ዐማራ ፡ ክልል ፡ ተብዬው"* ፡ ሹመኞዎች ፡ *"የባጀት ፡ ቀመሩ ፡ እንደገና ፡ ይታይልን"* ፡ ሲሉ ፡ የጠየቁበት ፡ ምክንያት ፡ ፊቱኑ ፡ ያውቁት ፡ የነበረው ፡ *"የክልላቸው"* ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ በኹለቱም ፡ ተከታታይ ፡ የሕዝብ ፡ *"ቈጠራዎች"* ፡ ይፋ ፡ በወጡ ፡ ዘገባዎች ፡ ካ10 ፡ እስካ15 ፡ ሚልዮን ፡ መቅነሱና ፡ ለሌሎች ፡ ክልሎች ፡ ተላልፎ ፡ መሰጠቱ ፡ ድንገት ፡ ታስቧቸው ፡ ይመስላል ። ምን ፡ ይሄ ፡ ብቻ ፤ በደርዘን ፡ የሚቈጠሩ ፡ የተወካዮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መቀመጫዎችም ፡ እንደዚሁ ፡ ተሞጥልቀውላቸዋል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፣ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

*"ባለኹለት ፡ አኃዝ"* ፡ እድገት ፡ (ማለት ፡ ካ 10% ፡ የበለጠ ፡ እድገት) ፡ ታይቷል ፡ የሚባለው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ እውነት ፡ ይኾን ፨

ለጊዜው ፥ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥታውያን ፡ ተቋማትና ፡ እንደ ፡ ዓለም ፡ ባንክ ፡ (World Bank) ፡ እና ፡ እንደ ፡ አህጉራዊ ፡ የገንዘብ ፡ ቋት ፡ (International Monetary Fund) ፡ ባሉ ፡ አህጉራውያን ፡ (international) ፡ ተቋማት ፡ የተሰጡንን ፡ አኃዛውያን ፡ ልቅሞች ፥ ሳንጠራጠር ፡ *"አሜን"* ፡ ብለን ፡ እንቀበልና ፥ ብዙ ፡ የሚነገርለትን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ጥርየታዊ ፡ እድገት ፡ እስቲ ፡ አንድ ፡ አፍታ ፡ እንፈትሽባቸው ።

**4 ፤ እድገትና ፡ ንረት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ባለፉት ፡ 50 ፡ ዓመታት ።**

*"ማእከላዊ ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ባለሥልጣን"* ፡ ያጠናቀረውን ፡ መረጃ ፡ *"አሻሽሎ"* ፡ *"አህጉራዊ ፡ የገንዘብ ፡ ቋት"* ፡ (International Monetary Fund — I.M.F.) ፡ ከ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 2008 ፡ ዓ.ም. ፡ በኢትዮጵያ ፡ የታዩትን ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ መጠኖች ፡ ተራውን ፡ እንደሚከተለው ፡ ሰጥቶናል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ሰንጠረዥ–2 ፤ የኢትዮጵያ ፡ የችርቻሮ ፡ ዋጋ ፡ ቋም ፡ እና ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ መጠን ፡ ከ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ።
[ምንጭ ፦ አህጉራዊ ፡ የገንዘብ ፡ ቋት | Source: International Monetary Fund — I.M.F.]

| ዓ.ም. (year E.C.) | የችርቻሮ ፡ ዋጋ ፡ ቋም (retail price index) | የዋጋ ፡ ንረት ፡ መጠን (rate of inflation) |
|---|---|---|
| 1958 | 4.32 | |
| 1959 | 4.35 | 0.03 |
| 1960 | 4.36 | 0.01 |
| 1961 | 4.42 | 0.06 |
| 1962 | 4.87 | 0.45 |
| 1963 | 4.89 | 0.02 |
| 1964 | 4.6 | -0.29 (የዋጋ ፡ ሟሸሻ) |
| 1965 | 5.01 | 0.41 |
| 1966 | 5.44 | 0.43 |
| 1967 | 5.79 | 0.35 |
| 1968 | 7.45 | 1.66 |
| 1969 | 8.69 | 1.24 |
| 1970 | 9.93 | 1.24 |
| 1971 | 11.52 | 1.59 |
| 1972 | 12.04 | 0.52 |
| 1973 | 12.78 | 0.74 |
| 1974 | 13.53 | 0.75 |
| 1975 | 13.44 | -0.09 (የዋጋ ፡ ሟሸሻ) |
| 1976 | 14.57 | 1.13 |
| 1977 | 17.35 | 2.78 |
| 1978 | 15.64 | -1.71 (የዋጋ ፡ ሟሸሻ) |
| 1979 | 15.26 | -0.38 (የዋጋ ፡ ሟሸሻ) |
| 1980 | 16.35 | 1.09 |
| 1981 | 17.62 | 1.27 |
| 1982 | 18.53 | 0.91 |
| 1983 | 25.15 | 6.62 |
| 1984 | 27.8 | 2.65 |
| 1985 | 28.78 | 0.98 |
| 1986 | 30.97 | 2.19 |
| 1987 | 34.07 | 3.1 |
| 1988 | 31.18 | -2.89 (የዋጋ ፡ ሟሸሻ) |
| 1989 | 31.93 | 0.75 |
| 1990 | 32.22 | 0.29 |
| 1991 | 34.77 | 2.55 |
| 1992 | 35 | 0.23 |
| 1993 | 32.12 | -2.88 (የዋጋ ፡ ሟሸሻ) |
| 1994 | 32.64 | 0.52 |
| 1995 | 38.45 | 5.81 |
| 1996 | 39.7 | 1.25 |
| 1997 | 44.84 | 5.14 |
| 1998 | 50.36 | 5.52 |
| 1999 | 59.04 | 8.68 |
| 2000 | 85.26 | 26.22 |
| 2001 | 92.48 | 7.22 |
| 2002 (መደብ-ዓመት) | 100 | 7.52 |
| 2003 | 133.22 | 33.22 |
| 2004 | 163.56 | 30.34 |
| 2005 | 176.77 | 13.21 |
| 2006 | 189.84 | 13.07 |
| 2007 | 209.09 | 19.25 |
| 2008 | 224.27 | 15.18 |
| 2009 | 239.45 | 10.8 |
| 2010 | 250.25 | 9.9 |
| 2011 | 260.15 | 10.9 |

የ"ማእከላዊ ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ባለሥልጣን" ፡ ካጠናቀረው ፡ መረጃ ፡ ይልቅ ፡ "አህጉራዊ ፡ የገንዘብ ፡ ቋት" ፡ (International Monetary Fund — I.M.F.) ፡ ያሻሻለው ፡ መረጃ ፡ ለእውነቱ ፡ ይቀርባል ። ለምሳሌ ፥ ለ 2008 ፡ ዓ.ም. ፡ "ማእከላዊ ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ባለሥልጣን" ፡ የኢትዮጵያን ፡ ዓመታዊ ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ 7.26% ፡ ነበር ፡ ሲል ፥ "አህጉራዊ ፡ የገንዘብ ፡ ቋት" ፡ (International Monetary Fund — I.M.F.) ፡ ግን ፡ 15.18% ፡ ነበር ፡ ይላል ። በዋና ፡ ዋና ፡ ሸቀጣሸቀጥ ፡ በ 2008 ፡ ዓ.ም. ፡ የታየው ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ ከ 20% ፡ እስከ ፡ 30% ፡ የሚደርስ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ የ"አህጉራዊ ፡ የገንዘብ ፡ ቋት" ፡ ሽልግ ፡ ለእውኑ ፡ ይቀርባል ። በዚህ ፡ መሠረት ፥ ከ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ ዠምሮ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የታየውን ፡ አጠቃላይ ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ ስንመለከት ፥ ከ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 1998 ፡ ዓ.ም. ፡ ባሉት ፡ 40 ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ከአነስተኛ ፡ (<3%) ፡ እስከ ፡ መለስተኛ ፡ (<6%) ፡ የሚባል ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ ታይቷል ። ከ 1999 ፡ ዓ.ም. ፡ ወዲህ ፡ ግን ፥ የዋጋ ፡ ንረቱ ፡ ከ 8% ፡ በላይ ፡ ኾኗል ፤ እንዲያውም ፡ ከ 2003 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 2008 ፡ ዓ.ም. ፡ ድረስ ፡ የዋጋ ፡ ንረቱ ፡ ካ 13% ፡ እስከ ፡ 33% ፡ የሚዋዥቅ ፡ የ"ኹለት ፡ አኃዝ" ፡ ዋጋ ፡ ንረት ፡ ኾኖ ፡ ቈይቷል ። ለ 2009 ፡ ዓ.ም. ፡ እና ፡


©አ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ለ 2010 ፡ ዓ.ም. ፡ ኹኔታው ፡ ተባብሶ ፥ ከ 25% ፡ እስከ ፡ 35% ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ ታይቷል ።

በሰንጠረዥ–2 ፡ ኹለተኛ ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፡ እንደምናየው ፥ የ 2002 ፡ ዓ.ም. ፡ የዋጋ ፡ መጠን ፥ ባማካይ ፥ ከ 1958 ቱ ፡ የዋጋ ፡ መጠን ፡ (100 / 4.32 = 23.15) ፡ ጊዜ ፡ ይበልጣል ። በሌላ ፡ አነጋገር ፥ በ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ 1 ፡ ብር ፡ ይሸጥ ፡ የነበረ ፡ ሸቀጥ ፡ በ 2002 ፡ ዓ.ም. ፥ በዋጋ ፡ ንረት ፡ ምክንያት ፥ ባማካይ ፡ 23.15 ፡ ብር ፡ ደርሷል ፡ ማለት ፡ ነው ። የ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ የዋጋ ፡ መጠን ፡ እንደዚሁ ፥ ባማካይ ፥ ከ 1958 ቱ ፡ የዋጋ ፡ መጠን ፡ (260.15 / 4.32 = 60.22) ፡ ጊዜ ፡ ይበልጣል ። በሌላ ፡ አነጋገር ፥ በ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ 1 ፡ ብር ፡ ይሸጥ ፡ የነበረ ፡ ሸቀጥ ፥ በ 2011 ፡ ዓ.ም. ፥ በዋጋ ፡ ንረት ፡ ምክንያት ፥ ባማካይ ፡ 60.22 ፡ ብር ፡ ደርሷል ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህን ፡ ጭብጥ ፡ ለማስረገጥ ፡ የጥቂት ፡ ሸቀጦችንና ፡ አገልግሎቶችን ፡ ዋጋ ፡ በሰንጠረዥ–3 ፡ እናስተያይ ፦

ሰንጠረዥ–3
የጥቂት ፡ ሸቀጣሸቀጥንና ፡ አገልግሎቶችን ፡ የ 50 ፡ ዓመታት ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ ማገዳደሪያ

| ሸቀጣሸቀጥ ፡ እና ፡ አገልግሎቶች | የ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ ዋጋ (ዐዲስ ፡ አበባ) | የ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ዋጋ | በአማካይ ፡ ማናሪያ ፡ የተገኘ ፡ ዋጋ (የ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ ዋጋ ፡ በ 60.22 ፡ ሲባዛ) | የዋጋ ፡ ልዩነት ፡ በብር ፡ (በአማካዩ ፡ ማናሪያ ፡ ያልተገናዘበ ፡ ተጨማሪ ፡ የዋጋ ፡ ንረት) |
|---|---|---|---|---|
| ነጭ ፡ ጤፍ ፡ (ኩንታል) | 25 ፡ ብር | 2,800 ፡ ብር | 1,505.5 ፡ ብር | +1,294.5 ፡ ብር |
| በግ | 10 ፡ ብር | 1,800 ፡ ብር | 602.2 ፡ ብር | +1,197.8 ፡ ብር |
| ለጋ ፡ ቅቤ ፡ (1 ፡ ኪሎግራም) | 2.5 ፡ ብር | 150 ፡ ብር | ≃ 150 ፡ ብር | ≃ 0 ፡ ብር |
| ዕንቍላል | 0.05 ፡ ብር | 4 ፡ ብር | 3.11 ፡ ብር | +0.81 ፡ ብር |
| ቤት ፡ ኪራይ ፡ (1 ፡ ክፍል ፡ ቤት) | 50 ፡ ብር | 1,200 ፡ ብር | 2,408.8 ፡ ብር | −1,208.8 ፡ ብር |
| ቤት ፡ ኪራይ ፡ (3 ፡ ክፍል ፡ ቤት) | 300 ፡ ብር | 15,000 ፡ ብር | 18,066 ፡ ብር | −3,066 ፡ ብር |

በሰንጠረዥ–3 ፡ እንደምናየው ፥ ባለፉት ፡ 50 ፡ ዓመታት ፥ ምግብ–ነክ ፡ የኾኑ ፡ ሸቀጦች ፡ ዋጋዎች ፥ ካማካዩ ፡ የዋጋ ፡ ማናሪያ ፡ (x 60.22) ፡ 2 ፡ ወይም ፡ 3 ፡ እጅ ፡ በልጠዋል ። ለምሳሌ ፦

- የኩንታል ፡ ጤፍ ፡ ዋጋ ፥ በ 50 ፡ ዓመቱ ፡ አማካይ ፡ የዋጋ ፡ ማናሪያ ፡ (x 66.22) ፡ መሠረት ፥ በ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ ከነበረበት ፡ የ 25 ፡ ብር ፡ ዋጋ ፥ በ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ወደ ፡ 1,505.5 ፡ ብር ፡ ብቻ ፡ መድረስ ፡ ሲገባው ፥ በ 112 ፡ ተባዝቶ ፥ 2,800 ፡ ብር ፡ ደርሷል ፤
- የበግ ፡ ዋጋም ፡ እንደዚሁ ፥ በ 180 ፡ ተባዝቶ ፥ ከነበረበት ፡ 10 ፡ ብር ፡ ወደ ፡ 1,800 ፡ ብር ፡ ንሯል ፤

ምግብ–ነክ ፡ ያልኾኑ ፡ ያገልግሎት ፡ ዋጋዎች ፡ ደግሞ ፡ ካማካዩ ፡ የዋጋ ፡ ማናሪያ ፡ (x 60.22) ፡ ባነሰ ፡ መጠን ፡ አድገዋል ፦

- የቤት ፡ ኪራይ ፡ ባማካይ ፡ ከ 20 ፡ እስከ ፡ 50 ፡ ዕጥፍ ፡ ጨምሯል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ወረኃዊ ፡ ወጪ ፡ እስከ ፡ 80% ፡ ለምግብ ፡ የሚውል ፡ በመኾኑ ፥ የዋጋ ፡ ንረቱ ፡ በተለይ ፡ ድኻውን ፡ ኅብረተሰብ ፡ እንደጐዳው ፡ አኃዛዊው ፡ መረጃ ፡ ያረጋግጣል ። የጕዳቱን ፡ ልክ ፡ በትክክል ፡ ለማወቅ ፡ ዝርዝር ፡ የደመ ፡ ወዝ ፡ እድገት ፡ ልቅም ፡ ያሻን ፡ ነበር ። ዝርዝር ፡ ልቅሙ ፡ ስላልተገኘልን ፥ ለናሙና ፡ ያኽል ፡ የጥቂት ፡ የሚያ ፡ ክፍሎችን ፡ የ 50 ፡ ዓመታት ፡ የደመ ፡ ወዝ ፡ እድገት ፡ በግርድፉ ፡ ደርድረን ፥ ምን ፡ ያኽል ፡ ከዋጋ ፡ ንረት ፡ ጋራ ፡ እንደተገዳደሩ ፡ እንደሚከተለው ፡ እናያለን ፡ [ሰንጠረዥ–4] ።

ሰንጠረዥ–4 ፤
የጥቂት ፡ የሚያ ፡ ክፍሎች ፡ የ 50 ፡ ዓመት ፡ የደመ ፡ ወዝ ፡ እድገት ፡ ከዋጋ ፡ ንረት ፡ ጋራ ፡ ማገዳደሪያ ።

| ሚያ | አማካይ ፡ የወር ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ በ 1958 ፡ ዓ.ም. | አማካይ ፡ የወር ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ በ 2002 ፡ ዓ.ም. | አማካይ ፡ የወር ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ በ 2011 ፡ ዓ.ም. | በአማካይ ፡ ማናሪያ ፡ የተገኘ ፡ የደመ ፡ ወዝ ፡ መጠን ፡ (የ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ ዋጋ ፡ በ 60.22 ፡ ሲባዛ) | ጕዳት ፡ በ 2011 ፡ ዓ.ም. |
|---|---|---|---|---|---|
| ያ 1ኛ ፡ ደረጃ ፡ መምህር | 200 ፡ ብር | 1,400 ፡ ብር | 2,000 ፡ ብር | 12,044 ፡ ብር | −10,044 ፡ ብር |
| የቤት ፡ ሠራተኛ | 30 ፡ ብር | 400 ፡ ብር | 1,500 ፡ ብር | 1,806.6 ፡ ብር | −306.6 ፡ ብር |
| የዕለት ፡ ሚያተኛ | 60 ፡ ብር | 900 ፡ ብር | 1,600 ፡ ብር | 3,613.2 ፡ ብር | −2,013.2 ፡ ብር |
| ወረዳ ፡ አስተዳዳሪ | 350 ፡ ብር | 3,000 ፡ ብር | 8,500 ፡ ብር | 21,077 ፡ ብር | −12,577 ፡ ብር |


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

በሰንጠረዥ－4 ፡ ከደረደርናቸው ፡ የሚያ ፡ ዐይነቶች ፡ ውስጥ ፡ ያንደኛውም ፡ የደመ ፡ ወዝ ፡ እድገት ፡ ከዋጋ ፡ ንረት ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ አላደገ ፡፡ ለምሳሌ ፥ በ1958 ፡ ዓ.ም. ፡ ያ1ኛ ፡ ደረጃ ፡ መምህራን ፡ ደመ ፡ ወዝ ፥ ባማካይ ፥ በወር ፡ 200 ፡ ብር ፡ ነበር ፡፡ እንደ ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ባሉ ፡ ከተማዎች ፥ ያንድ ፡ ክፍል ፡ ቤት ፡ የወር ፡ ኪራይ ፡ በ50 ፡ ብር ፥ አንድ ፡ ኩንታል ፡ ጤፍ ፡ በ25 ፡ ብር ፥ አንድ ፡ በግ ፡ ባ10 ፡ ብር ፥ 3 ፡ ኪሎ ፡ ለጋ ፡ ቅቤ ፡ በ7.5 ፡ ብር ፥ 30 ፡ ዕንቍላል ፡ በ1.5 ፡ ብር ፥ በድምር ፡ 94 ፡ ብር ፡ ወጥቶ ፥ 106 ፡ ብር ፡ ይተርፋል ፡ (የደመ ፡ ወዙ ፡ 47%) ፡፡ በ2011 ፡ ዓ.ም. ፡ በመምህራን ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ ይህ ፡ ዅሉ ፡ የማይቀመስ ፡ ኾኗል ፡፡ አንድ ፡ ኩንታል ፡ ጤፍ ፡ የመምህሩን ፡ የወር ፡ ተኩል ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ ይፈጃል ፤ ቤት ፡ ኪራይ ፡ የደመ ፡ ወዙን ፡ ኹለት ፡ ሢሶ ፡ ይፈጃል ፤ ሌላውን ፡ እንተወውና ፥ 4ኪሎ ፡ ለጋ ፡ ቅቤ ፡ የወር ፡ ደመ ፡ ወዙን ፡ ሩብ ፡ ይፈጃል!

ሰንጠረዥ－5
የመምህራን ፡ አማካይ ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ በ1958 ፡ ዓ.ም. ፡ አንጻር ፡ በ2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ያለው ፡ እውናዊ ፡ የመግዛት ፡ ዐቅሙና ፡ ተገቢው ፡ እድገት ፡ ቢደረግለት ፡ የሚኖረው ፡ እውናዊ ፡ የመግዛት ፡ ዐቅም ፡ ለተወሰነ ፡ ወርኃዊ ፡ የወጪ ፡ ቅርጫት ፡፡

| የወጪ ፡ ዐይነት | የ1958 ፡ ዓ.ም. ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ 200 ፡ ብር/ወር | የ2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ 2000 ፡ ብር/ወር | ተገቢው ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ በ2011 ፡ ዓ.ም. 12,044 ፡ ብር |
|---|---|---|---|
| ነጭ ፡ ጤፍ ፡ (30 ፡ ኪሎ) | -8.3 ፡ ብር | -840 ፡ ብር | -840 ፡ ብር |
| በግ | -10 ፡ ብር | -1,800 ፡ ብር | -1,800 ፡ ብር |
| ለጋ ፡ ቅቤ ፡ (3 ፡ ኪሎግራም) | -7.5 ፡ ብር | -450 ፡ ብር | -450 ፡ ብር |
| ዕንቍላል ፡ (30) | -1.5 ፡ ብር | -120 ፡ ብር | -120 ፡ ብር |
| ቤት ፡ ኪራይ ፡ (1 ፡ ክፍል ፡ ቤት) | -50 ፡ ብር | -1,200 ፡ ብር | -1,200 ፡ ብር |
| ድምር | -77.3 ፡ ብር | -4410 ፡ ብር | -4410 ፡ ብር |
| ከወጪ ፡ ቀሪ | +122.7 ፡ ብር ፡ (61.4%) | -2410 ፡ ብር ፡ (-120.1%) | +7634 ፡ ብር ፡ (63.4%) |

እላይ ፡ እንዳመለከትነው ፥

**የእውን ፡ እድገት = የስም ፡ እድገት － የዋጋ ፡ ንረት**

በሚል ፡ ቀመር ፡ ይሰሳል ፡፡

ወደ ፡ ስሌቱ ፡ ከማምራታችን ፡ በፊት ፥ የኢትዮጵያ ፡ ጥርየት ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርት ፡ (ሀ.ው.ጠ.ም. ፡ ወይም ፡ G.D.P.) ፡ ላለፉት ፡ አርባ ፡ ዓመታት ፡ በምን ፡ መጠንና ፡ እድገት ፡ ተከታትሎ ፡ እንደ ፡ ተከሠተ ፡ የዓለም ፡ ባንክ ፡ የሰጠንን ፡ አኃዞች ፡ በሰንጠረዥ－6 ፡ አንዳፍታ ፡ እንመልከት ፡፡

ሰንጠረዥ－6
የኢትዮጵያ ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርት ፡ [ሀ.ው.ጠ.ም.] ፡ መጠንና ፡ ዓመታዊ ፡ እድገት ፡ ከ1973 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 2010 ፡ ዓ.ም.
[ምንጭ ፤ የዓለም ፡ ባንክ | Source: World Bank]

| ዓ.ም. (E.C.) | ሀ.ው.ጠ.ም. (በ2008 ፡ ዓ.ም. ፡ የብር ፡ ምንዛሪ) በቢልየን ፡ ብር GDP (constant Billion Br) | እድገት | ሀ.ው.ጠ.ም. (በእየዘመኑ ፡ የብር ፡ ምንዛሪ) በቢልየን ፡ ብር GDP (current Billion Br) | እድገት |
|---|---|---|---|---|
| 1980 | 286.64 | 1.00% | 22.58 | 4.00% |
| 1981 | 285.6 | 0.00% | 23.76 | 5.00% |
| 1982 | 293.39 | 3.00% | 25.2 | 6.00% |
| 1983 | 272.45 | -7.00% | 27.87 | 11.00% |
| 1984 | 248.82 | -9.00% | 29.41 | 6.00% |
| 1985 | 281.52 | 13.00% | 37.72 | 28.00% |
| 1986 | 290.5 | 3.00% | 40.07 | 6.00% |
| 1987 | 308.3 | 6.00% | 47.92 | 20.00% |
| 1988 | 346.61 | 12.00% | 54.01 | 13.00% |
| 1989 | 357.47 | 3.00% | 55.82 | 3.00% |
| 1990 | 345.11 | -3.00% | 53.81 | -4.00% |
| 1991 | 362.93 | 5.00% | 57.84 | 7.00% |
| 1992 | 384.97 | 6.00% | 67.16 | 16.00% |
| 1993 | 416.93 | 8.00% | 68.55 | 2.00% |
| 1994 | 423.24 | 2.00% | 67.07 | -2.00% |
| 1995 | 414.09 | -2.00% | 74 | 10.00% |
| 1996 | 470.3 | 14.00% | 87.33 | 18.00% |
| 1997 | 525.88 | 12.00% | 107.29 | 23.00% |
| 1998 | 582.86 | 11.00% | 132.65 | 24.00% |
| 1999 | 649.63 | 11.00% | 173.31 | 31.00% |
| 2000 | 719.72 | 11.00% | 250.21 | 44.00% |
| 2001 | 783.07 | 9.00% | 337.97 | 35.00% |
| 2002 | 881.35 | 13.00% | 385.88 | 14.00% |
| 2003 | 979.87 | 11.00% | 515.08 | 33.00% |
| 2004 | 1064.61 | 9.00% | 747.33 | 45.00% |
| 2005 | 1177.27 | 11.00% | 866.92 | 16.00% |
| 2006 | 1298.03 | 10.00% | 1060.81 | 22.00% |
| 2007 | 1432.92 | 10.00% | 1297.96 | 22.00% |
| 2008 | 1568.1 | 9.00% | 1568.1 | 21.00% |
| 2009 | 1717.13 | 10.00% | 1832.55 | 17.00% |
| 2010 | 1834.07 | 7.00% | 2202.37 | 20.00% |

የልቅሙን ፡ ጠቅላላ ፡ ይዘት ፡ በቢጋር ፡ መልክ ፡ የተሻለ ፡ እንደሚከተለው ፡ እናየዋለን ፡፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡፡

[ግጸሡ–2]

የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርት ፡ (ሀ.ው.ጠ.ም.) ፡ መጠንና ፡ ዓመታዊ ፡ እድገት ፡ ከ1980 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 2010 ፡ ዓ.ም.

(ምንጭ ፤ የዓለም ፡ ባንክ | Source: World Bank)




ታዲያ ፡ የ"ኹለት ፡ አኃዝ" ፡ ዋጋ ፡ ንረት ፡ በሚታይበት ፡ በዚህ ፡ ኹኔታ ፡ እንዴት ፡ ተደርጎ ፡ የ"ኹለት ፡ አኃዝ" ፡ የእውን ፡ እድገት ፡ (real growth) ፡ ይገኛል ፡- ብለን ፡ ልንጠይቅ ፡ እንገደዳለን ።

ለ 2003 ፡ ዓ.ም. ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ ልቅም ፡ 33.22% ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ አይተናል ። እንግዲህ ፥ ለዚሁ ፡ ለ 2003 ፡ ዓ.ም. ፡ የተሰጠን ፡ የሀ.ው.ጠ.ም. ፡ (G.D.P.) ፡ ወይም ፡ የሀገራዊ ፡ ምርት ፡ እድገት ፡ ልቅም ፡ የ 11% ፡ እውናዊ ፡ እድገት ፡ ልቅም ፡ ተብሎ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ የ 33.22% ፡ የዋጋ ፡ ንረቱ ፡ ተደምስሶ ፡ የ 11% ፡ እውናዊ ፡ እድገት ፡ እንዲገኝ ፡ የስም ፡ እድገቱ ፡ 33.22% + 11% = 43.33% ፡ ነበር ፡ ማለት ፡ ነው ።

እዚህ ፡ ላይ ፡ ለማመን ፡ ትንሽ ፡ የሚቸግር ፡ ነገር ፡ አለ ። ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ ከከፍተኛ ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ ጋራ ፡ ከፍተኛ ፡ የምርት ፡ እድገት ፡ የሚታዩባቸው ፡ ዓመታት ፡ ሊኖሩ ፡ ይችላሉ ። ለምሳሌ ፥ ያንድ ፡ ሀገር ፡ መንግሥት ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ጥሬ ፡ ገንዘብን ፡ እያተመ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ወጪዎቹ ፡ የገበያውን ፡ የመግዛት ፡ ዐቅም ፡ ድንገት ፡ ቢያሳድገው ፥ ይህ ፡ ተጨማሪ ፡ ዐቅም ፡ ተራውን ፡ የሸቀጣሸቀጥና ፡ ያገልግሎቶች ፡ ፍጆታዎችን ፡ በማሳደጉ ፥ ዕጥረት ፡ በሚታይባቸው ፡ ሸቀጣሸቀጦችና ፡ አገልግሎቶች ፡ ከተለመደው ፡ የባሰ ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ መታየቱ ፡ አይቀርም ። ይህ ፡ ግን ፡ በተከታታይ ፡ ዓመታት ፡ የሚደርስ ፡ ቢኾን ፥ ምጥራዩን ፡ ለመሠረታዊ ፡ መናጋት ፡ ስለሚዳርገው ፥ መጨረሻውን ፥ የዋጋ ፡ ንረቱ ፡ ለምርት ፡ እውናዊ ፡ እድገት ፡ መሟሸሽ ፡ ምክንያት ፡ ይኾናል ።

ከ 2003 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ድረስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ ካ 10% ፡ እስከ ፡ 33% ፡ ሲንር ፡ ቈይቷል ፤ የዚሁ ፡ ወቅት ፡ አማካይ ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ 17.3% ፡ ነበር ። ያ 10% ፡ እውናዊ ፡ እድገት ፡ ለ 9 ፡ ዓመታት ፡ በተከታታይ ፡ ለማየት ፡ የዋጋ ፡ ንረቱ ፡ በዝቅተኛ ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ (ማለት ፡ ከ 3% ፡ ያነሰ ፡ መጠን ፡ ላይ) ፡ መገኘት ፡ ይኖርበታል ። ይህ ፡ ያልኾነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግን ፥ ያለውን ፡ የእውን ፡ እድገት ፡ ከሂሎት ፡ (potential) ፡ ኹሉ ፡ የዋጋ ፡ ንረቱ ፡ አሟጦ ፡ ይበላዋል ። በመዠመሪያ ፡ ደረጃ ፥ የዋጋ ፡ ንረት ፡ የገንዘብን ፡ የመግዛት ፡ ዐቅም ፡ ስለሚቀንስ ፥ የገበያውን ፡ የፍጆታ ፡ መጠን ፡ ይቀንሰዋል ፤ ፍጆታ ፡ ሲቀንስ ፥ አምራቾች ፡ የወደፊት ፡ ሽልጋቸውን ፡ ከልሰው ፡ የምርታቸውን ፡ መጠን ፡ ሲቀንሱ ፡ የሠራተኛ ፡ ቅጥራቸውንም ፡ ያሳንሳሉ ። በኹለተኛ ፡ ደረጃ ፥ የዋጋ ፡ ንረቱ ፡ ባንክ ፡ ከሚሰጠው ፡ የወለድ ፡ መጠን ፡ በላይ ፡ ሲኾን ፥ የማጠራቀም ፡ ጥቅምን ፡ ይቀንሳል ፤ በዚያኑ ፡ መጠን ፥ ለብድር ፡ የሚውል ፡ ገንዘብ ፡ ይታጣል ፥ ይህም ፡ የመዋዕለ ፡ ንዋይ ፡ እንሻን ፡ ያስከትላል ። በመጨረሻ ፥ እነዚህና ፡ ሌሎች ፡ መዘዞች ፡ ተደምረው ፡ እድገቱን ፡ ይገቱታል ።

በነዚህ ፡ ምክንያቶች ፡ ኹሉ ፥ የአኃዛዊ ፡ ልቅሙን ፡ ታማኝነት ፡ ከመጠርጠርም ፡ ዐልፈን ፡ ልንገፋው ፡ እንገደዳለን ። እንደ ፡ ቻይና ፡ ያሉ ፡ በፍጥነት ፡ የሚያድጉ ፡ ምጥራዮች ፥ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ምርታቸውን ፡ ባ 10 ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ለማጠፍ ፡ የቻሉት ፡ ዓመታዊው ፡ የዋጋ ፡ ንረታቸው ፡ ካ 5% ፡ በማነሱ ፡ ነው ። ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ ለተከታታይ ፡ ዓመታት ፡ የታየበት ፡ ምጥራይ ፡ ከመኰሰስ ፡ አያመልጥም ። የኢትዮጵያ ፡ ምጥራይ ፥ ባለፉት ፡ 10 ፡ ዓመታት ፡ የ 156% ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ ቢታይበትም ፥ ይህን ፡ የዋጋ ፡ ንረት ፡ በ 87% ፡ የላቀ ፡ እውናዊ ፡ እድገት ፡ አድጓል ፡ ተብለናል ። የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሚያዎችን ፡ ወርኃዊ ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ እድገት ፡ ስንመለከት ፡ ግን ፥ ውጤቱ ፡ ይህን ፡ ፈጽሞ ፡ አያረጋግጥም ። የደመ ፡ ወዘተኞቹ ፡ የኑሮ ፡ ደረጃ ፡ እፍጹም ፡ ድኽነት ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ መነጠፉን ፡ ተመልክተናል ።

- አንድ ፡ መምህር ፥ ዛሬ ፡ በ 2011 ፡ ዓ.ም. ፥ በ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ የኑሮ ፡ ደረጃው ፡ እንዲኖር ፥ ወርኃዊ ፡ ደመ ፡ ወዙ ፡ ከ 2,000 ፡ ብር ፡ ይልቅ ፡ 12,000 ፡ ብር ፡ መኾን ፡ ነበረበት ።
- አንዲት ፡ የቤት ፡ ሠራተኛ ፥ ዛሬ ፡ በ 2011 ፡ ዓ.ም. ፥ በ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ የኑሮ ፡ ደረጃዋ ፡ እንድትኖር ፥ ወርኃዊ ፡ ደመ ፡ ወዟ ፡ ከ 1,500 ፡ ብር ፡ ይልቅ ፡ 1,800 ፡ ብር ፡ መኾን ፡ ነበረበት ።
- አንድ ፡ የዕለት ፡ ሚያተኛ ፥ ዛሬ ፡ በ 2011 ፡ ዓ.ም. ፥ በ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ የኑሮ ፡ ደረጃው ፡ እንዲኖር ፥ ወርኃዊ ፡ ደመ ፡ ወዙ ፡ ከ 1,600 ፡ ብር ፡ ይልቅ ፡ 3,600 ፡ ብር ፡ መኾን ፡ ነበረበት ።

ዛሬ ፥ ከዓመት ፡ ወደ ፡ ዓመት ፡ እያደገ ፡ በሚኼድ ፡ የተረጂ ፡ ሕዝብ ፡ ብዛት ፡ (በ 20 ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ከ 4 ፡ ሚልዮን ፡ ወደ ፡ 14 ፡ ሚልዮን ፡ አድጓል) ፡ "ሰለኹለት ፡ አኃዝ ፡ ንረት" ፡ እንጂ ፥ "ሰለኹለት ፡ አኃዝ ፡ እድገት" ፡ መለፈፍ ፡ ፍጹም ፡ ማጭበርበር ፡ ይባላል ።

**5 ፤ እድገቱ ፡ በዋጋ ፡ ንረት ፡ ተበልቷል ።**

የኢትዮጵያ ፡ ምጥራይ ፡ ፈጽሞ ፡ ተጐድቷል ፤ ትንሽ ፡ ነፍስ ፡ ያለበት ፡ ቢመስል ፡ ቅሉ ፥ ባለው ፡ መሠረታዊ ፡ ጥንካሬ ፡ እንጂ ፥ እንደ ፡ ደረሰበት ፡ ጕዳት ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፥ ዱሮ ፡ ገና ፡ ላጠቃላይ ፡ መደርባት ፡ በተዳረገ ፡ ነበር ።

ርግጥ ፡ ነው ፥ የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. ፡ ይዘት ፥ በ"ግብርና-መር" ፡ ልማታዊ ፡ ዐቅዱ ፥ ተጨማሪ ፡ አንዳች ፡ መሬት ፡ ሳያለማ ፥ ያለውን ፡ የዕርሻ ፡ መሬት ፥ ከውጭ ፡ በውድ ፡ በሚገዙ ፡ በማዳበሪያና ፡ በተባይ ፡ መከላከያ ፥ እንዲሁም ፡ በ"ምርጥ ፡ ዘር" ፡ እና ፡ በመስኖ ፡ ልማት ፥ የግብርናውን ፡ ምርት ፡ በ 27 ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ በ 2 ፡ ዕጥፍ ፡ አሳድጌዋለኹ ፡ ብሏል ። እውኑ ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ መልክት ፡ ይሰጠናል ፤ ከ 27 ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፥ ሀገሪቱ ፡ ራሷን ፡ መቀለብ ፡ አቅቷት ፥ ካመት ፡ ወዳመት ፡ የሚጨምር ፡ የስንዴና ፡ የበቆሎ ፣ የስኳርና ፡ የዘይት ፡ ጭነት ፡ ከቅርብና ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ታስመጣለች (14) ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፥ ወባውንና ፡ የዱር ፡ አራዊቱን ፣ ሽፍታውንና ፡ ቀማኛውን ፡ ተቋቁመው ፣ የሪያና ፡ የዝንጀሮ ፡ መሰምሪያ ፡ የነበረውን ፡ ጥሻና ፡ ደን ፡ መንጥረውና ፡ አልምተው ፥ ሀገር ፡ አድርገው ፥ ከተረጂነት ፡ ራሳቸውን ፡ አውጥተው ፡ በሰላም ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ በመቶ ፡ ሺሕ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ከቤንች ፣ ከማጂ ፣ ከአሶሳ ፣ ከጨርጨር ፡ ... ፡ እየተገደሉ ፡ ተፈናቅለዋል ። ይህ ፡ ኹሉ ፡ ግፍ ፡ ፍርዱን ፡ ማግኘት ፡ ይኖርበታል ።

ከደርግ ፡ ዘመን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፥ የውንብድና ፡ አገዛዝን ፡ በመጥላትና ፡ ተስፋን ፡ በመቍረጥ ፥ ወጣቱ ፡ ወደ ፡ ጐረቤት ፡ ሀገር ፥ ከዚያም ፡ ዐልፎ ፡ ወደ ፡ መካከለኛው ፡ ምሥራቅና ፡ አፍሪቃ ፣ ወዳውሮፓና ፡ አሜሪካ ፡ በገፍ ፡ ተሰዷል ። ያለቀው ፡ ዐልቆ ፥ የተረፈው ፥ ሀገር ፡ ወገኑን ፡ ሳይረሳ ፥ ዐሳሩን ፡ በልቶ ፡ ያተረፈውን ፡ ሀበት ፡ ወዳገር ፡ ቤት ፡ ሲልክ ፥ በመላ ፡ ዓለም ፡ በተዘረጋ ፡ የሐዋላ ፡ አገልግሎት ፡ መረብ ፥ የውጭ ፡ ምንዛሪው ፡ እየተጠለፈ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሀገር ፡ ሲወጣ ፥ ለኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ የሚበተንለት ፡ በምትኩ ፡ የታተመ ፡ "ብር" ፡ የተባለ ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ የወረቀት ፡ ገንዘብ ፡ ኾኗል ። የውጭ ፡ ምንዛሪው ፡ እንዲህ ፡ ባይጠለፍ ፡ ኖሮ ፥ ለሀገሪቱ ፡ የውጭ ፡ ንግድ ፡ ውሎ ፡ ለልማት ፡ ተፈላጊዎቹን ፡ መኪናዎችና ፡ ምንሃቦች ፡ ለማስመጣትም ፡ ለማስፋፋትም ፡ ትልቅ ፡ ድጋፍ ፡ በኾነ ፡ ነበር ። አኹን ፡ ግን ፥ በምትኩ ፡ የሚበተነው ፡ የወረቀት ፡ "ብር" ፡ ለዋጋ ፡ ንረቱ ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ ኾኗል ።

ርግጥ ፡ ነው ፥ እንደ ፡ ቻይና ፡ ያሉ ፡ ሀገሮች ፥ መንገድን ፣ ግድብን ፣ የኤሌትሪክ ፡ መሥመርን ፣

14 ለ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ብቻ ፥ ኢትዮጵያ ፡ 500 ፡ ሚልዮን ፡ ዶላር ፡ ወይም ፡ 12.5 ፡ ቢልዮን ፡ ብር ፡ አውጥታ ፡ የስንዴ ፡ ዱቄት ፡ ከዓለም ፡ ገበያ ፡ ገዝታ ፡ አስመጥታለች ። ይህ ፡ 12.5 ፡ ቢልዮን ፡ ብር ፡ ለስንዴ ፡ ማሳዎች ፡ ማስፋፊያ ፡ ቢውል ፥ ሀገሪቱ ፡ የስንዴ ፡ እኽል ፡ ፍላጎቷን ፡ ከማሟላትም ፡ ዐልፋ ፥ ባ 1950 ዎቹ ፡ ወደነበረችበት ፡ የስንዴ ፡ ላኪ ፡ ሀገርነት ፡ ተርታ ፡ ትሰለፍ ፡ ነበር ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

ምንዛባዊ ፡ ወጀድን ፡ (industrial park) ፡ የመሳሰሉ ፡ ታላላቅ ፡ የመሠረተ ፡ ልማት ፡ ሥራዎችን ፡ በሚመሰገን ፡ ጥራትና ፡ ፍጥነት ፡ በመሥራታቸው ፥ የውጭ ፡ ምንዛሪን ፡ ያገባሉ ፡ የተባሉ ፡ ዐዳዲስ ፡ ዐቅሞችን ፡ ሀገሪቱ ፡ አግኝታለች ። እነዚህ ፡ ግን ፡ ገና ፡ ዐዳዲስ ፡ ከመኾናቸው ፡ ጋራ ፥ ጥቂት ፡ የሥራ ፡ ዕድልን ፡ ለወጣቱ ፡ ቢፈጥሩም ፥ ሙሉ ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ሲዠምሩ ፡ ትርፋቸውን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ሀገር ፡ ስለመመለሳቸው ፡ ምንም ፡ የሚያስተማምን ፡ ነገር ፡ የለም ።

ላለፉት ፡ ሦስት ፡ ዓመታት ፡ በተከታታይ ፡ ይፋ ፡ የወጡት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የውጭ ፡ ንግድ ፡ ልቅሞች ፡ መኰሰስን ፡ እንጂ ፡ መዳበርን ፡ አላሳዩም ። ብዙ ፡ የተወራለት ፡ የግብርናው ፡ **ክፍለ ፡ ጥርየትም** ፡ ቢኾን ፥ በ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ያሳየው ፡ የ 4% ፡ እድገት ፡ ብቻ ፡ ነው ። ዋና ፡ የ"ዶላር" ፡ ምንጭ ፡ የተባለውም ፡ የማዕድን ፡ ክፍለ ፡ ጥርየት ፡ ምርት ፡ በሚያሠጋ ፡ ኹኔታ ፡ አሽቈልቍሏል ። ለሀገሪቱ ፡ በዓመት ፡ የ 500 ፡ ሚልዮን ፡ ዶላር ፡ የውጭ ፡ ምንዛሪ ፡ ያስገኝ ፡ የነበረው ፡ የወርቅ ፡ ምርት ፥ ዘንድሮ ፡ 39 ፡ ሚልዮን ፡ ዶላር ፡ ብቻ ፡ ማስገኘቱ ፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ይዘት ፡ ሹመኛዎች ፡ አፍ ፡ በ"ቍጭት" ፡ ሲለፈፍ ፡ ተሰምቷል ። የዚህኛው ፡ ጕዳይ ፡ ውስጠ ፡ ምስጢር ፡ ግን ፡ ለየት ፡ ያለ ፡ ምክንያትን ፡ ዐዝሏል ። አብዛኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወርቅ ፡ የሚመረተው ፡ በ"*ኦሮሚያ ፡ ክልል ፡ ተብዬው*" ፡ በመኾኑ ፥ ከ"*ማእከላዊ ፡ መንግሥት*" ፡ ቍጥጥር ፡ ውጪ ፥ በ"ክልሉ" ፡ የውንብድና ፡ ኀይሎች ፡ ቍጥጥር ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ በርከት ፡ ያሉ ፡ መረጃዎችና ፡ ምልክቶች ፡ ደርሰዋል ። በሰሜን-ምሥራቅ ፡ "*ዴሞክራቲክ ፡ ኮንጎ ፡ ሪፓብሊክ*" ፡ በሚልዮን ፡ የሚቈጠር ፡ ሕዝብን ፡ የፈጀውና ፡ ያፈናቀለው ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የማዕድን ፡ ንግድ ፥ በምዕራብና ፡ ደቡብ-ምዕራብ ፡ ኢትዮጵያም ፥ ከነጆ ፡ እስከ ፡ አዶላ ፣ ከጕጂ ፡ እስከ ፡ አሶሳ ፡ ተመሳሳይ ፡ ጕዳቶች ፡ ደርሰዋል ።

ከዚህ ፡ ወዲያ ፥ ከ 2007 ፡ ዓ.ም ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፥ በመላ ፡ ሀገሪቱ ፡ ሊባል ፡ በሚችል ፡ መልክ ፡ በደረሰ ፡ ሰፊ ፡ የሰላም ፡ ዕጦት ፡ ምክንያት ፥ በሺሕ ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰላማውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ያለቁበት ፣ በሚልዮን ፡ የሚቈጠሩ ፡ ሰላማውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከመኖሪያቸው ፡ የተፈናቀሉበት ፣ በደርዘን ፡ የሚቈጠሩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትና ፡ መስጊዶች ፡ የተቃጠሉበት ፣ የመገናኛ ፡ መሥመሮች ፡ ለሳምንታት ፡ የተዘጉበት ፣ በሺሕ ፡ የሚቈጠሩ ፡ የንግድ ፡ ድርጅቶች ፡ የወደሙበት ፣ በደርዘን ፡ የሚቈጠሩ ፡ ባንኮች ፡ የተዘረፉበት ፥ ለእድገት ፡ ፈጽሞ ፡ የማይስማማ ፡ አቈርቋዥ ፡ ዘመን ፡ ኾኖ ፡ ተጠናቋል ።

ከዚህ ፡ ኹሉ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ደግሞ ፥ ኾነ ፡ ተብሎ ፡ እጅግ ፡ በተለጠጠ ፡ "*የስኳር ፡ ልማት ፡ ሥራ*" ፥ ከ 70 ፡ ቢልዮን ፡ ብር ፡ ያላነሰ ፡ ወደወያኔ ፡ ካዝና ፡ መተላለፉ ፡ በይፋ ፡ ተነግሯል ። እንደዚሁ ፥ ለ"*ሕዳሴ*" ፡ ግድብ ፡ ከተሰበሰበው ፡ በቢልዮን ፡ ብር ፡ የሚገመት ፡ የድኻው ፡ መዋጮ ፥ ከፊሉ ፡ የገባበት ፡ እንዳልታወቀ ፡ ተነግሯል ። ዛሬ ፡ ወያኔ ፥ አላንዳች ፡ ሥጋት ፥ መቀሌ ፡ ቢመሽግ ፥ ፊቱ ፡ ምሽጉንና ፡ ሥንቁን ፡ ስለ ፡ ደረጀ ፡ መኾኑ ፡ ትንታኔ ፡ አያሻውም ።

ታዲያ ፥ እስካኹን ፡ በከፊል ፡ የተዘረዘረው ፡ ጥፋት ፡ "*በኢትዮጵያ ፡ ምጥራይ ፡ ላይ ፡ እዚህ ፡ ግባ ፡ የሚባል ፡ ጕዳት ፡ አላደረሰም*" ፡ በሚያሠኝ ፡ መልክ ፥ የዓለም ፡ ባንክም ፡ ኾነ ፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ፡ ሹመኛዎች ፡— *የ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ዓመታዊው ፡ ጥርየታዊ ፡ እድገት ፡ "ባለኹለት ፡ አኃዝ" ፡ ኾኖ ፡ ተጠናቋል* ፡ ብለውናል ። ለዚህ ፡ የጋራ ፡ አቋም ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ የጥርየትኛ ፡ ማስረጃ ፡ አይገኝለትም ፤ አንዳች ፡ ማስረጃ ፡ ቢገኝለት ፡ አለጥርጥር ፡ ከስያሳዊ ፡ አግጣጫ ፡ ብቻ ፡ ይመጣል ።

**6 ፤ ስያሳዊ ፡ ምክንያት ፡ ያለው ፡ ጥርየታዊ ፡ ስርጀታ ።**

*ለመምህራን ፣ ለመንግሥት ፡ ሠራተኛዎች ፣ ለወታደሮች ፣ ወዘተ...* ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ ሲውል ፡ የሚገባው ፡ ሀገራዊ ፡ ሀብት ፥ ለ"ክልሎች" ፡ የማፈንገጫ ፡ ዐቅም ፡ ግንባታ ፡ መዋሉ ፡ ግልጥ ፡ ያለ ፡ ሤራ ፡ ነውና ፥ በፍጥነት ፡ መቀጨት ፡ ይኖርበታል ።

ኢትዮጵያ ፡ ምቀኛን ፡ ያልነሣት ፡ ሀገር ፡ ናት ፤ አቀማመጧም ፣ የተፈጥሮ ፡ ሀብቷም ፣ ሥልጣኔዋም ፡ የሚያስቀኑትን ፡ ያኽል ፡ ስለሚያሠጉ ፥ ባላንጣዎቿ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። በዓለም ፡ ታሪክ ፥ በነጣቂነታቸው ፡ የታወቁና ፡ የገነኑ ፡ ኀይሎች ፥ ከሞላ ፡ ጐደል ፥ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ ሲቃጡ ፡ ኖረዋል ፤ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የተሳካለት ፡ አንድም ፡ አልነበረ ። ዛሬም ፡ ኢትዮጵያ ፥ በቀጥታም ፡ በተዘዋዋሪም ፥ ተዘምቶባታል ። እጅግ ፡ በተራቀቀ ፡ ስልት ፥ በብዙ ፡ ቢልዮን ፡ ዶላር ፡ በተደገፈ ፡ የረዥም ፡ ዘመን ፡ ዘመቻ ፥ ሀገሪቱን ፡ በአፍሪቃ ፡ ቀንድ ፡

ውስጥ ፡ **በድ<u>ሶ</u>ላ** ፡ (federation) ፡ ወይም ፡ **በተዳብሎ** ፡ (confederation) ፡ *ዐይነት* ፡ *ግዛታዊ* ፡ **ምሕቃፍ** ፡ **(framework)** ፥ ለብዙ ፡ *"ሪፓብሊኮች"* ፡ በታትኖ ፥ አንድ ፡ ባለቤት ፡ የኾነ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሕዝብ ፡ በሌለበት ፥ ርስ ፡ በርሱ ፡ በተለያየ ፤ በሚፎካከርና ፡ በሚራኰት ፡ ውጥን-ቅጥ ፡ የ*"ሕዝቦች"* ፡ ክፍለት ፡ መስጎና ፡ ሰንጎ ፡ በመያዝ ፥ እጅግ ፡ ዐቅዳዊ ፡ የኾነውን ፡ ብሔሯን ፡ (ምድሯን) ፡ ለመቈጣጠር ፤ ሀብቷን ፡ ለመበዝበዝና ፥ አፍሪቃንም ፡ ለመቀራመት ፡ ይሠራል ።

የኢትዮጵያ ፡ *"ልማት"* ፡ ወሬ ፡ የዚህ ፡ የጥፋት ፡ ተልእኮ ፡ መሸፈኛ ፡ ደበሎ ፤ ምትሀታዊ ፡ ትርክት ፡ ነው ። ዕለት ፡ በዕለት ፡ ውሃና ፡ ኤሌትሪክ ፡ የሚቋረጥበት ፤ ቤት ፡ ንብረቱ ፡ የሚቀማበት ፤ የወር ፡ ገቢው ፡ ከሳምንት ፡ የማያደርሰው ፥ *"ይህስ ፡ ለምን ፡ ይፈጸምብኛል"* ፡ ብሎ ፡ ሲቃወምም ፡ በጥይት ፡ የሚቈላው ፡ ሕዝቡስ ፡ በተጨባጭ ፡ ጕዳቱን ፡ ያውቀዋል ፤ ያጣው ፡ ይህን ፡ ስርጀታ ፡ የሚመሰክርለት ፡ የእውነት ፡ አንደበት ፡ ነው ። ካንደበትም ፡ በላይ ፡ ችግሩን ፡ የሚፈታለት ፡ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካሉ ፡ ነውና ፥ ራሱ ፡ ፈጥሮ ፡ ካላበረለትና ፡ ካላጸናው ፥ ሌላ ፡ ማንም ፡ አይታደገውም ❖

## ኣኌዛውያኚ ፡ ልቅሞች ።

statistical data | données statistiques | بيانات احصائية

| የኢትዮጵያ ፡ ኣኌዛውያኚ ፡ ልቅሞች ፡ ስለሃይማኖት ፡ ተከታዮች ፡ (2011 ፡ ዓ.ም.) ። | | |
|---|---|---|
| ክፍል | የሕዝብ ፡ ብዛት | ከጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ በመቶኛ ፡ (%) |
| ሃይማኖታዊ ፤ | ከ 110 ፡ ሚሊዮን | |
| ተዋሕዶ ፡ ክርስቲያን ፤ | 79.2 ፡ ሚሊዮን | 72.00% |
| መስልም ፤ | 18.7 ፡ ሚሊዮን | 17.00% |
| ፕሮቴስታንት ፤ | 5.5 ፡ ሚሊዮን | 5.00% |
| ካቶሊክ ፤ | 3.3 ፡ ሚሊዮን | 3.00% |
| የሌላ ፡ ሃይማኖት ፡ አማኝ ፤ | 3.3 ፡ ሚሊዮን | 3.00% |

## ማሳሰቢያ

notice | اشعر

ሠኔ ፡ 21 ፡ ቀኚ ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. | 28 June 2019 A.D. | 28 juin 2019 A.D.

### የኢንተርኔት ፡ አገልግሎት ፡ ክልከላው ፡ ለጊዜው ፡ ተወግዷል ፡ ...

ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ ላለፉት ፡ ወራት ፡ ከኢንተርኔት ፡ አገልግሎት ፡ በተደጋጋሚና ፡ አላግባብ ፡ በመወገዱ ፡ ምክንያት ፡ ሲቸገር ፡ ከርሟል ።

በብሪታንያ ፥ የኢንተርኔት ፡ ግንኙቱ ፡ መቋራረጡ ፡ ሠኔ ፡ 3 ፡ ቀን ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ተስተካክሎ ፥ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ መደበኛ ፡ አገልግሎቱን ፡ መስጠት ፡ ዠምሯል ።

ኾኖም ፥ ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ የሚገኘው ፡ መርበቢያችን ፡ slttunhzb.net ፥ ከሚያዝያ ፡ ወር ፡ 2019 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሐምሌ ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ ድረስ ፡ የ FTP ፡ ማዝለቂያ ፡ መሥመሩ ፡ ባከራዩው ፡ ፈረንሳዊ ፡ ኩባንያ ፡ አላግባብና ፡ አላንዳች ፡ ምክንያት ፡ ታግዶበት ፡ ከርሟል ። ደጋግመን ፡ ያቀረብናቸው ፡ የይስተካከል ፡ ጥያቄዎቻችን ፡ ኹሉ ፡ በማደናቈርና ፡ ጊዜን ፡ በማስጠፋት ፡ መክነው ፡ ቀርተዋል ። ይህ ፡ አሳዛኝ ፡ ድርስ ፥ ውልን ፡ የጣሰ ፡ ከመኾኑም ፡ የባሰ ፥ የስርጀታ ፡ ድርጊትም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ የፍራንስ ፡ ኩባንያዎችን ፡ መልካም ፡ ስም ፡ ያስጠፋልና ፥ ጕዳዩን ፡ ለፈረንሳይ ፡ የውጭ ፡ ጕዳይ ፡ ምጋቤ ፡ በእ-ጦማር ፡ አስታውቀናል ። ከፈረንሳዊው ፡ ድርጅት ፡ ጋራ ፡ የነበረንን ፡ የኪራይ ፡ ውል ፡ ሐምሌ ፡ 10 ፡ ቀን ፡ 2019 ፡ ዓ.ም. ፡ ሠርዘን ፥ ከሌላ ፡ ድርጅት ፡ ጋራ ፡ ልንዋዋል ፡ ተገደናል ።

መርበቢያችን ፡ slttunhzb.net ፡ ተቋርጦ ፡ የነበረውን ፡ መደበኛ ፡ አገልግሎቱን ፡ ከሐምሌ ፡ 19 ፡ ቀን ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ መቀጠሉን ፡ በደስታ ፡ እናስታውቃለን ።

የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ።

**The Internet Service Denial is stopped for now ...**

For the past several months, the ECDU has been severely

**Le Déni de Service Internet est stoppé pour le moment ...**

Durant les mois passés, l'UCDE a été sévèrement entravé dans


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

| | |
|---|---|
| hampered by illegitimate denials of Internet services. | son travail par des dénis injustifiés de service Internet. |
| The Internet connections, from our headquarters in the United Kingdom, which had been intermittently interrupted, have now been fully operational since the 10th of June 2019. | Les connections Internet, depuis son siège au Royaume Uni, qui étaient constamment entre-coupées, sont depuis le 10 juin 2019 entièrement opérationnelles. |
| Unfortunately, the web-hosting company based in France which hosts our web-site slttunhzb.net, has been denying us FTP-access since April 2019 for reasons unknown to us, in complete disregard of its contractual obligations, and despite our repeated calls. These regrettable acts constitute, beyond a breach of contract, pure and simple sabotage; both of which are detrimental to the good name of French businesses. This matter has been notified to the French Ministry of Foreign Affairs by e-mail. | Malheureusement, la société d'hébergement de notre site slttunhzb.net qui est basée en France, nous a refusé tout accès FTP depuis le mois d'avril 2019, pour des raisons qui nous sont inconnues, au mépris de ses obligations contractuelles, et en dépit de nos appels répétés. Ces actes regrettables constituent, par-delà une rupture de contrat, du sabotage pur et simple ; tous les deux au détriment du bon nom des sociétés françaises. Le ministère français des affaires étrangères a été notifié de la question par courriel. |
| We have on the 17th July 2019 terminated our web-hosting contract with the French company, and awarded it to another company. | Le 17 juillet 2019 nous avons résilié notre contrat d'hébergement avec cette société française, et l'avons attribué à une autre société. |
| We are pleased to inform you that our website slttunhzb.net is now back in service. | Nous avons le plaisir de vous informer que notre site slttunhzb.net a maintenant repris service. |
| *the Secretariat of the Provisional Executive Council, ECDU.* | *Le Secrétariat du Conseil Exécutif Provisoire, UCDE.* |

## የሰብኣውያን ፡ መብቶች ፡ ብሔራዊ ፡ ድንጋጌ ።

Universal Declaration of Human Rights | Déclaration universelle des droits de l'homme

### አንቀጽ ፡ 2 | Article 2

የዘር ፣ የቀለም ፣ የጾታ ፣ የቋንቋ ፣ የሃይማኖት ፣ የግዛት ፡ ወይም ፡ የሌላ ፡ አስተያየት ፣ የሀገራዊ ፡ ወይም ፡ የኅብረ ፡ ሰብኣዊ ፣ የሀብት ፣ የትውልድ ፡ ወይም ፡ የደረጃ ፡ አንዳች ፡ ልዩነት ፡ ሳይደረግ ፥ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ድንጋጌ ፡ በታወጁት ፡ መብቶችና ፡ ነጻነቶች ፡ ኹሉ ፡ ሊመካ ፡ ይችላል ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፥ አንድ ፡ ሰው ፡ አባል ፡ በኾነለት ፥ ሐራም ፡ ኾነ ፣ በዐደራነት ፡ የተሰጠ ፣ ራሱን ፡ የማይገዛም ፡ ኾነ ፣ አንዳች ፡ የእግዚእና ፡ እግድ ፡ ያለበት ፡ ሀገርም ፡ ኾነ ፡ ብሔር ፡ (ምድር) ፥ በግዛት ፣ ወይ ፡ በሥልጣን ፣ ወይም ፡ በአህጉራዊ ፡ ደረጃ ፡ መሠረት ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ልዩነት ፡ አይደረግበትም ።

| | |
|---|---|
| Everyone is entitled to all the rights and freedoms set forth in this Declaration, without distinction of any kind, such as race, colour, sex, language, religion, political or other opinion, national or social origin, property, birth or other status. Furthermore, no distinction shall be made on the basis of the political, jurisdictional or international status of the country or territory to which a person belongs, whether it be independent, trust, non-self-governing or under any other limitation of sovereignty. | Chacun peut se prévaloir de tous les droits et de toutes les libertés proclamés dans la présente Déclaration, sans distinction aucune, notamment de race, de couleur, de sexe, de langue, de religion, d'opinion politique ou de toute autre opinion, d'origine nationale ou sociale, de fortune, de naissance ou de toute autre situation. De plus, il ne sera fait aucune distinction fondée sur le statut politique, juridique ou international du pays ou du territoire dont une personne est ressortissante, que ce pays ou territoire soit indépendant, sous tutelle, non autonome ou soumis à une limitation quelconque de souveraineté. |

### አንቀጽ ፡ 19 | Article 19

ሰው ፡ ኹሉ ፥ ያስተያየትና ፡ አስተያየትን ፡ የመግለጽ ፡ ነጻነት ፡ አለለት ፤ ይህም ፡ መብት ፥

- ማንም ፡ ጣልቃ ፡ ሳይገባበት ፡ አስተያየትን ፡ ለራሱ ፡ የማብጀት ፡ መብትንና ፥
- ከማንኛውም ፡ ማወራኛ ፥ አንዳችም ፡ ጠረፍ ፡ ሳያግደው ፥ መረጃንና ፡ ሐሳብን ፡ የመቀባበል ፡ መብቱን ፡ ይጨምራል ።

| | |
|---|---|
| Everyone has the right to freedom of opinion and expression; this right includes freedom to hold opinions without interference and to seek, receive and impart information and ideas through any media and regardless of frontiers. | Tout individu a droit à la liberté d'opinion et d'expression, ce qui implique le droit de ne pas être inquiété pour ses opinions et celui de chercher, de recevoir et de répandre, sans considérations de frontières, les informations et les idées par quelque moyen d'expression que ce soit. |


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

# አስተያየት

## opinion | رأي

### ስላልሾምናቸው ፥ ናቁን!

ሥልጡንሕዝብና ፡ መዜንው ፥ እንኳን ፡ ደኅና ፡ መጣሽ! አዘጋጆቹም ፥ እግዚአብሔር ፡ እንኳን ፡ ድምፃችኹን ፡ ዳግም ፡ ለመስማት ፡ አበቃን!

ለሀገራዊ ፡ ቋንቋችን ፡ ለዐማርኛ ፡ በምታሳዩት ፡ ጥንቃቄ ፡ ለሕዝብ ፡ ያላችኹን ፡ አክብሮትና ፡ ፍቅር ፡ መጠን ፥ እንደ ፡ ወትሮው ፡ ኹሉ ፡ ስላሳየኸኝና ፡ ስላረጋገጠልኝ ፥ ተደስቼባችኋለኹ ።

የሕዝብ ፡ አገልጋይ ፡ ከችሎታ ፡ ጋራ ፡ ትሕትናን ፡ መላበስ ፡ ይገባዋል ። እኔ ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ተወልጄ ፡ በማደጌ ፡ እንጂ ፥ ከ 66 ፡ ወዲህ ፡ የተወለዱትስ ፡ ምናልባት ፡ ከሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፥ ከመንግሥት ፡ ሹመኛዎች ፡ ዘንድ ፡ ትሕትናን ፡ አይጠብቁም ። የዛሬዎቹ ፡ ሹመኛዎች ፡ ለሀገራዊ ፡ ቋንቋችን ፡ ተገቢውን ፡ ጥንቃቄ ፡ አያደርጉም ። ከጥቂት ፡ ሀገር ፡ አፍቃሪዎች ፡ በቀር ፥ ከበታች ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ከፍተኛው ፡ ሹመኛ ፥ እንግሊዝኛን ፡ ሳይጨምሩ ፡ አረፍተ ፡ ነገርን ፡ አይጨርሱም ። ከትምህርት ፡ ማነስ ፡ ይኾናል ፡ እንዳንል ፥ አንዳንዶቹ ፡ ባለ"ዲግሪ" ፡ ናቸው ። ሌላ ፡ ምክንያት ፡ ይኖር ፡ ይኾን ፤ ምናልባት ፥ ለዐማርኛ ፡ ንቀትን ፣ ለእንግሊዝኛ ፡ አክብሮትን ፡ ካላሳዩ ፥ በጧት ፡ እንዳይሻሩ ፡ ሠግተው ፡ ይኾን ፤ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፤ ምክንያቱም ፥ ሕዝብ ፡ አልሾማቸውምና ፡ ለምን ፡ ብለው ፡ ሕዝብን ፡ ያክብሩ ፤ እንዲያውም ፡ ዐማርኛን ፡ በሰባበሩት ፡ መጠን ፥ በማዕርግ ፡ ላይ ፡ ማዕርግ ፣ በሹመት ፡ ላይ ፡ ሹመት ፡ እየጨመሩ ፡ እስገነቱ ፡ ጫፍ ፡ መውጣትን ፡ የተማመመኑበት ፡ ይመስላል ።

ሕዝቤ ፡ ሆይ ፡ ራስኽን ፡ አስከብር! ላልሾምካቸውና ፡ ባልሾምካቸው ፡ አትገዛ!

አማረች ፥ ካዲስ ፡ አበባ ።

---

### የዓለም ፡ ነገር ፥ ጥንትም ፡ ተሻሻለ ፡ ሲሉት ፡ የሚባባስ ፡ ነው ።

[...] ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ በምዕራቡ ፡ ዓለም ፡ በደረሰበት ፡ የኢንተርኔት ፡ እገዳ ፡ ብዙ ፡ አልተገረምኩም ። የዓለም ፡ ነገር ፥ ጥንትም ፡ ተሻሻለ ፡ ሲሉት ፡ የሚባባስ ፡ ነው ። የጊዜን ፡ መንገድ ፡ አንድም ፡ በጽድቅ ፣ አንድም ፡ በጽናት ፡ ካልተጓዙት ፡ አይዘለቅምና ፥ በያዛችኹት ፡ ቀጥሉ ፤ ከጐናችኹ ፡ አንለያችኹም ።

ገብረየስ ፥ ከምዕራብ ፡ አውሮፓ ።

---

| የቃላት ፡ መተርጐሚያ | | | |
|---|---|---|---|
| ዐጪር ፡ ግስ (ዐማርኛ) | ፍች | short glossary (English) | bref glossaire (français) |
| አሀጉር | (ኹለት) ፡ ሀገሮች | (two) countries | (deux) pays |
| አሀጉራት | (ብዙ) ፡ ሀገሮች | (many) countries | (plusieurs) pays |
| አሀጉራዊ | ወለ ፡ አሀጉራዊ<br>በይነ ፡ አሀጉራዊ | international | international |
| አሀጉራዊ ፡ የገንዘብ ፡ ቋት ፡ (አ.ገ.ቋ.) | የዓለም ፡ ባንክ ፡ ዘርፍ ፡ ድርጅት | International Monetary Fund (I.M.F.) | Fond Monétaire International (F.M.I.) |
| አገዛዝ | ግዛት | government | gouvernement |
| እግዚእ | ገዢ | sovereign | souverain |
| እግዚእና | ገዢነት | sovereignty | souveraineté |
| እውን | | real, fact | réel, fait |
| እውነት | እውንነት | reality | réalité |
| አካባቢ | | environment | environnement |
| አምሳያ | ምስያ | synonym | synonyme |
| አንድያ | አንድ ፡ ብቻ | unique, sole | unique, seul |
| እንሻ | ማነስ ፥ መዶግዶግ | decrease | réduction |
| አስኳል | ውስጣውስጥ | core | noyau |
| ብውሕና | | diplomacy | diplomatie |
| በቀርታ | | exception | exception |
| በሐረ | መደረ ፥ ሰፋ ፥ ተንጣለለ ። | expand | s'étendre |
| ብሔር | ምድር ፡ (ሲወሰን)/ ስፋት ፣ ዓለም | territory / universe | territoire / univers |
| ብሔራዊ | የምድር) | territorial | territorial |
| ብሔራዊ | ዓለም ፡ ዐቀፍ | universal | universel |
| ብሔራዊ ፡ መረጣ | የጾታ ፣ የኑሮ ፡ ደረጃ ፣ ወዘተ. ፡ ልዩነት ፡ የማይደረግበት ፡ ምርጫ | universal suffrage | suffrage universel |
| ብቸ ፡ ሥሉጥ | ብቸ ፡ ገዥ | autocrat | autocrate |
| ጋዝ [15] | ንዛዥ | gas | gaz |
| ግዛት | አገዛዝ | government | gouvernement |
| ግለኛ | ባለግል ፥ ሰው | individual (n.) | individu (n.) |
| ግንኝት | ግንኙነት | connection | connexion |
| ግዑዝ | ያልወገነ ፥ ገለልተኛ | neutral | neutre |
| ግዑዝነት | አለመወገን | neutrality | neutralité |
| ግጽው | ሥዕል ፥ ግጻዌ | figure | figure |
| ግጽው | ልቅም | figure, statistics | figure, statistiques |
| | | | |
| ጎሳ | ነገድ | tribe | tribu |
| ጕልበት | ኀይል | energy | énergie |
| ድበላ | ድባሌ ፥ ደባል ፡ አድርጎ ፡ የሚይዝ ፡ ሥርዐት | federation | fédération |
| ደባይ | በደባልነት ፡ | federal | fédéral |

15 ጋዝ ፤ ከግሪክኛው ፡ "chaos" ፡ የወጣ ፡ ቃል ፤ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ንዛዥ ፡ ለማለት ፡ ሆላንዳዊ ፡ ጥበበኛ ፡ "ጋዝ" ፡ ብሎ ፡ በሆላንድኛ ፡ ላሕይ ፡ የሰመየው ። የ"chaos" ፡ ትርጕም ፡ ከዐማርኛው ፡ "ጋዝ" ፡ ወይም ፡ "ጠብ ፣ ጭቅጭቅ ፣ ውዝግብ" ፡ ጋራ ፡ በምስጢር ፡ ስለሚገጥም ፥ ባማርኛም ፡ "ጋዝ" ፡ ቢባል ፡ ተቃውሞ ፡ አይኖርም ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

| ዐጨር ፡ ግስ (ዐማርኛ) | ፎቾ | short glossary (English) | bref glossaire (français) |
|---|---|---|---|
| | የሚያሳድር | | |
| ድባሌ | ድቧላ ፥ ደቧል ፡ አድርጎ ፡ የሚይዝ ፡ ሥርዐት | federation | fédération |
| ተዳባይ | | con-federal | confédéral |
| ተዳብሎ | | confederation | confédération |
| ደፈር | | highest point | point culminant |
| ደረጃ | | degree | degré |
| ድርስ | | event | événement |
| ሀገራዊ ፡ (ቅጽል) | የሀገር ፡ | citizen | citoyen |
| ሀገራዊ ፡ (ስም) | ባለቤት ፣ ባላገር ፡ (በዓለ ፡ ሀገር) ፣ ዐማራ | citizen | citoyen |
| ሀገራዊ ፡ ሒሳብ | | national accounts | comptes nationaux |
| ሀገራዊ ፡ ሒሳብ ፡ አያያዝ | | national accounting | comptabilité nationale |
| ወገዳ | የማስወገድ ፡ ድርጊት | purge | purge |
| ወጀድ | ዐጸድ ፣ ግቢ | park | parc |
| ወገብጌ | | equator | équateur |
| ውልደት | ትውልድ | nation | nation |
| ውርኝት | ለፈፋ | broadcast | diffusion |
| ዜነኛ | "ጋዜጠኛ" | journalist | journaliste |
| ዞግ ፡ (ዘውግ) | | clan | clan |
| ተንኅባቢ | እንደ ፡ ምድር ፡ በፀሓይ ፡ ዙሪያ ፡ የሚንኅበብ ። | planet | planète |
| ሒጋጊ | ሒጋጊ ፡ ሥልጣን | legislative | législatif |
| ሐራ | | independent / free | indépendant / libre |
| ኅዋ | | space | espace |
| ኀይል | | power | puissance |
| ኀይል | | force | force |
| ኀሊ | | idea | idée |
| የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርት ፡ (ሀ.ው.ጠ.ም.) | | gross domestic product (G.D.P.) | produit intérieur brut (P.I.B.) |
| የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላላ ፡ ምርት ፡ በነፍስ-ወከፍ | | gross domestic product (G.D.P.) per capita | produit intérieur brut (P.I.B.) par habitant |
| ጠረየ | | economize | économiser |
| ጥሪት | ሀብት | wealth | richesse |
| ጥርየተኛ | የጥርየትኛ ፡ ባለሚያ | economist | économiste |
| ጥርየት | | economy | économie |
| ይዘት | ይዘታ | régime | régime |
| ክሂሎት | ክሂል ፥ ችሎት | potential | potentiel |
| ከዋኝ | | constituent | constituant |
| ከዋኝ ፡ ጉባኤ | | constituent assembly | assemblée constituante |
| ክዋኔ | ሕገ ፡ መንግሥት | constitution | constitution |
| ክዋኒት | ሐውልት | obelisk | obélisque |
| ኪ..ማ. | ኪሎሜትር ፡ ማእዘን | km² | km² |
| ኪን | | technique | technique |
| ኪነት | | technology | technologie |
| ካልኢት | የጊዜ ፡ መለኪያ ፤ 60 ፡ ካልኢት ፡ 1 ፡ ደቂቃ ፡ ይኾናል | second | seconde |
| ክፍለ ፡ ጥርየት | | economic sector | secteur économique |
| ክፍለት | አከፋፈል ፣ አለያየት | partition | partition |
| ኹለትዮ ፡ ንምራ | የኹለት ፡ ቤት ፡ አኃዝ ፡ (0 ፣ 1) | binary digit | chiffre binaire |
| ኹነት / ኩነት | መንግሥት ፥ የተከወነ ፣ ክዋኔ ፡ ያሰው | State | État |
| ልማት | ብልጽግና | development | développement |
| ልዕልና | የበላይነት | supremacy | suprématie |
| ልቅም | የአኃዝም ፡ ኾነ ፡ የማንኛውም ፡ መረጃ ፡ ልቅም | data | données |
| ምእትያ | ምእት ፡ ዓመት | century | siècle |
| መባሕት | | diplomat | diplomate |
| መባሕታዊ | | diplomatic | diplomatique |
| መግበር | መሣሪያ | tool | outil |
| መደብ | መነሻ | base | base |
| መደብ-ዓመት | መነሻ ፡ ዓመት | base year | année de base |
| ምድራስ | | university | université |
| መዜንው | | news media | médium d'information |
| ምሕዋር | መንገድ ፣ መኼጃ | circuit | circuit |
| ምንሃብ | የመሥሪያ ፡ ቦታውና ፡ ሥርዐቱ ፥ "ፋብሪቃ" | industry | industrie |
| ምንሃባዊ ፡ ወጀድ | የምንሃብ ፡ ተቋማት ፡ ሰፈር | industrial park | parc industriel |
| መነሻ | | starting point | point de départ |
| መነሻ | | paragraph | paragraphe |
| መረብ | | network | réseau |
| መርበቢያ | | web site | site internet |
| መርበብት | | internet | internet |
| መርሐ ፡ ሰሜን | | compass | boussole |
| ማወራኛ | መልፈፊያ ፣ ማገናኛ | media | média |
| ምሕቃፍ | ማቀፊያ | framework | cadre, structure |
| ምኅዳር | | ecosystem | écosystème |
| መጥሪ/መጥሪት | ጠራዪ/ት | economic agent | agent économique |
| መጥሪት | | capital | capital |
| ምጥራይ | የጥርየት ፡ ሥርዐት | economic system | système économique |
| መሳሊያ | | software | logiciel |
| ማስሊያ | | computer | ordinateur |
| ሟሸሻ | የዋጋ ፡ ሟሸሻ | deflation | déflation |
| ማሟሸሻ | | deflator | déflateur |
| ነጂ-አልቦ | | driver-less | sans-conducteur |
| ንዛኸር | ጋዝ ፣ የእንፋሎት ፡ ዐይነት | gas | gaz |
| ነኰርኳር | መገለባበጥ ፥ መለዋወጥ ፤ የሥርዐት ፡ ለውጥ ። | revolution | révolution |
| ንረት | የዋጋ ፡ ንረት | inflation | inflation |
| ሥልጡን | ሥሉጥ | democrat | démocrate |


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

| ዐጪር ፡ ግስ (ዐማርኛ) | ፍች | short glossary (English) | bref glossaire (français) |
|---|---|---|---|
| ሥሉጥ | ሥልጡን | civil, civic | civil, civique |
| ሥሉጥ ፡ ማኅበር | ሥልጡን ፡ ማኅበር | civil society | société civile |
| ሥልጡንሕዝባዊ | የሥልጡን ፡ ሕዝብ | democratic | démocratique |
| ሥልጡንሕዝብና | ሥልጡንሕዝብነት | democracy | démocratie |
| ሥርዐተ ፡ ፀሓይ | ፀሓይና ፡ ዘጠኙ ፡ ተንዟባቢዎች ፡ አንድ'ጋ | solar system | système solaire |
| ዑደት | ዙር | orbit | orbite |
| ዐማራ | ዐም ፡ ሐራ ፥ ነጻ ፡ ሕዝብ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ | Ethiopian citizenry | ensemble des citoyens éthiopiens |
| ዐማራ | ሀገራዊ | citizen | citoyen |
| ዐምሐራ | ዐማራ | citizen | citoyen |
| ፈጻሚ | ፈጻሚ ፡ ሥልጣን | executive | exécutif |
| ፈታሒ | ፈታሒ ፡ ሥልጣን | judiciary | judiciaire |
| ፍልቅ | የፈለቀ | | |
| ፍልቅ | ሥንጥቅ | | |
| ፍልቅ ፡ ሸለቆ | ሥንጥቅ ፡ ሸለቆ | Rift Valley | Vallée du Rift |
| ቀረባ | አቀራረብ ፥ ስልት | approach | approche |
| ርትዓዊ ፡ ኹነት | የርትዕ ፡ መንግሥት | State of Right | État de droit |
| ስሕበት | ስበት | gravity | pesanteur |
| ስያስ | ዘዴ | policy | politique |
| ስያሳ | ሥነ ፡ ግዛት ፥ "ፖለቲካ" | politics | politique |
| ስያሳዊ | የስያስ ፡ ወይም ፡ የስያሳ | political *(adj.)* | politique *(adj.)* |
| ስያስኛ | ነገረ ፡ ስያሳ | political science | science politique |
| ስያሰኛ | የነገረ ፡ ስያሳ ፡ አጥኚ | political scientist | politologue |
| ስያሰኛ | የስያሳ ፡ ሰው | politician | politicien |
| የአንከርት ፡ ስልክ ፡ ኪነት | | mobile phone technology | technologie de téléphonie mobile |
| ሸቦ-አልቦ ሸቦ-አልባ | ነፋስ ፡ ስልክ ፥ አለሸቦ ፡ የሚተላለፍ ፡ መልክት | wireless | sans fil |
| ተገቢነት | ሕጋዊነት | legitimacy | légitimité |
| የሥልጣን ፡ ተገቢነት | የሥልጣን ፡ ሕጋዊነት | legitimacy of power | légitimité du pouvoir |
| ትውፊት | ልማድ ፥ ባህል | tradition | tradition |
| ችርቻሮ ፡ ዋጋ ፡ ቋም | የገበያ ፡ ዋጋ ፡ መጠቈሚያ | retail price index | indice des prix à la consommation |

# ዕርማት

## corrections – اصلاح الخاطا

በቀ፦.2011-001 ፡ እና ፡ በቀ፦.2011-002 ፡ የሠጡንሕዝብና ፡ ዕትሞች ፥ በስሕተት ፡

- *"ዠባቢ"* ፡ ተብሎ ፡ የታተመው ፡ ቃል ፡ *"ተንዠባቢ"* ፡ ተብሎ ፡ መታረሙን ፥
- *"ተነሣሣሽነት"* ፡ ተብሎ ፡ የታተመው ፡ ቃል ፡ *"ተነሣሽነት"* ፡ ተብሎ ፡ መታረሙን ፥

ከይቅርታ ፡ ጋራ ፡ እናሳስባለን ❖

ኢ ሀ ሥ አ

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሠልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

Ethiopians' Citizen Democratic Union | Union Citoyenne Démocratique des Éthiopiens

ማንኛውንም ፡ መልእክት ፥ ለጥቀው ፡ በተዘረዘሩት ፡ የግንኙት ፡ ማማረጫዎች ፥ ለሚመለከተው ፡ ክፍል ፡ ማድረስ ፡ ይቻላል ።

መርበቢያ ፦
http://www.slttunhzb.net

የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እ-ጦማር ፦
sh1@ttomar.net

የሥልጡንሕዝብና ፡ መዜንው ፡ እ-ጦማር ፦
sh1@ttomar.net

ስልክ ፦
00 44 74 96 54 15 90 (ብሪታኒያ)

| We may be reached alternatively through our: | Nous sommes joignables alternativement par: |
|---|---|
| Web site: | Site Internet: |
| http://www.slttunhzb.net | |
| E-mail: sh1@ttomar.net | Courriel: sh1@ttomar.net |
| Tel: 00 44 7496541590 (U.K.) | Tel: 00 44 7496541590 (R.U.) |




©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።